በበጎ ፈቃዱ

በበጎ ፈቃዱ ሁሉ በእርሱ ሆነ/2/

ነገር ሁሉ በእርሱ ተከናወነ/2/

ሰማይና ምድር ክብሩን ተናገሩ

ፈጥሮአቸዋልና እንዲገለፅ ክብሩ

በፈጠረው ፍጥረት የሚታወቅ እርሱ

እግዚአብሔር ይመስገን ስሙን አወድሱ

አልሆነም ያለ እርሱ ፍፁም አንዳች ነገር

ብንመረምረው በሰማይ በምድር

ፈቃዱ ነውና መልካምና በጎ

ፈጥሮ አሳይቶናል ሁሉን ውብ አድርጎ

ክረምትና በጋ ሌሊትና ቀን

ሁሉን አሳይቶ ጌታ አስተማረን

ያደረገው ሁሉ እንከን የሌለው

ለዚህ ቅዱስ አምላክ ምሳሌም የለው

ያዘነውን ያውቃል ደስም ያለውን

ሁሉ በእርሱ ፈቃድ ስለሚከወን

ችግርና ደስታ ለበጎ ነውና

ይህን ያስተማረን ይድረሰው ምስጋና

ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን

ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን /2

ለታላቁ ክብር ለዚህ ላበቃን

ከሞት ወደ ሕይወት ላሸጋገረን

ኑ በእግዚአብሔር ኑ በድንግል ደስ ይበለን

የሰማዩን መንግስት እርስቱን ለሰጠን

ከጨለማ አውጥቶ ብርሃንን ላሳየን

ለዚህ ድንቅ ውለታው ምስጋና ያንሰዋል

በእርሱ ደስ ይበለን ክብር ይገበዋል

ከአለት የፈለቀ ውኃ ጠጥተናል

ሰማያዊ መና አምላክ መግቦናል

ፍቅርህ የበዛ ነው ምን እንበላህ ጌታ

ስምህን እናመስግን ከጠዋት እስከ ማታ

በቃዴስ በረሀ ምንም በሌለበት

በኤርትራ ባህር ወጀብ በበዛበት

ለእርሱ መንገድ አለው ከቶ ምን ተስኖት

ልባችሁ አይፍራ በፍፁም እመኑት

በጨለማ ሳለን በድቅድቅ ዓለም

ብርሃንን አገኘን በድንግል ማርያም

ያጣነውን ሰላም ዛሬ አገኘን

እጅግ ደስ ይበለን በአምላካችን

የሀና የእያቄም የእምነታቸው ፍሬ

በእግዚአብሔር ፈቃድ ተወለደች ዛሬ

የእያቄም ስዕለቱ የሀና እምነት

ለምኝልን ለእኛ ኪዳነ ምህረት

በከበረው ሰረገላ

በከበረው ሰረገላ ማን አኖረኝ ካንተ ሌላ
ትዝታዬ ነህ እላለሁ ስባርክህ እኖራለሁ

ይፈሳል እንደ ዘይት ይወርዳል እንደ ጅረት
በበረሀው ልቤ ላይ ደምህ ከጎንህ ክፋይ
ባፍህ መሳም የሳምከኝ ፍቅርህን ያጠጣህኝ
አይለካህ እስትንፋሴ ሕይወቷ ነህ ለነፍሴ
ሰው ያለኝን በምሽት ባላገኘው በንጋት
ነፍሴ የወደደችህ አንተ ንገረኝ አልኩህ
ማን አስነሳኝ ለዜማ መውደዱን እያሰማ
አሳልፈህ ክረምቱን አጠገብከኝ ውበቱን
ይሸበራል ከተማው እያለ ውድሽ ማነው
እኔም አዜመዋለሁ በቅኔ አመልሳለሁ
የቀላው ደም ተነክሮ ነጭ አጥንቱ ተቆጥሮ
ሞቶ ነፍሴን ያኖረው ውዴ መድኅኔ ይህ ነው
ከተማውን አስሼ ሁሉንም አዳርሼ
እልፍ ስል አየሁህ ናፍቆቱን አገኘሁህ
ሳላገባህ ከእልፍኜ አልተውህም ጨክኜ
መልከ መልካሙ ንጉሥ ስስቱ ነህ

እንበረታለን ገና

እንበረታለን ገና በፀጋው ተደግፈን/2/
ወልድ ዋህድ እያልን ዓለምን እንከድናለን
ጴጥሮስ የመሰከረው አለት ነው መሠረቱ
ያባቶቻችን አምላክ የዋጀን በስቅለቱ
ሲጠብቀን ይኖራል ከወጣንበት ቦታ
እናመልካለን እሱን በፍቅር በደስታ /2/
ሲገሉን ሲያሳድዱን በቁጥር እንበዛለን
ሲንቁን ሲያዋርዱን በስሙ እንከብራለን
የሲኦልም ደጆች አይችሉንም እኛን
የተክለ ሃይማኖት አምላክ ይችላል ሊያድነን/2/
ልፋታችንን ያያል የሰማይ አምላካችን
ብዙውን እየሰጠን ጥቂቱን እንወስዳለን
ፅኑ ነው ማእተባችን ሳይበጠስ ይኖራል
የምናመልከው አምላክ በልባችን ይሠራል/2/
ተመስገን አምላካችን ዛሬ በዛን በፊትህ
በአህዛብ ተራሮች ላይ ይመሰገናል ስምህ
እያለፍን በፍቅርህ ዓለምን ልናቀና
ጌታ ሆይ ቅደምልን ቃል ኪዳን አለንና /2/

እቴ ሙሽራዬ

እቴ ሙሽራዬ ሰሎሞን ያለሽ
እኔም ልበልሽ እናቴ ማርያም ግቢ ከቤቱ
ሁሉም ሰው ለራሱ ወንበር ሲዘረጋ
የክብርን ሽልማት ወደ እርሱ ሲያስጠጋ
ድንግል እንደ ባሪያ ውኃ ተሸከመች
ጌታን በትሕትና ታገለግላለች
ነይ በደመና/4/ አመቤታችን ርህርህተ ህሊና
ወርቀ ዘቦ ለብሰው በቤቱ ከኖሩት
በሀርና በእንቁ ከተንቆጠቆጡት
በሰው ፊት ያማሩ ብዙ ሆነው ሳለ
ጌታ ግን ወደደሽ እናቴ ነሽ አለ .... ነይ ...
አሳድጎሽ ሳለ መልአኩ መግቦ
ተሸልመሽ ሳለ በገዙልሽ ተውቦ
እጅግ በትሕትና ስላገለገልሽው
እንደ ኪሩብ መልአክ ጌታን ተሸከምሽው .... ነይ ...
የባሪያውን ውርደት ተመልክቶአልና
ለወለድሽው ንጉስ ይድረሰው ምስጋና
ከልብ የወጣ እንጂ ከንቱ ሆኖ አይደለም
ብፅዕት እንላለን እኛም ለዘላለም .... ነይ ...

አሸነፍን

አሸነፍን በእግዚአብሔር አሸነፍን በአማኑኤል
ጠላት ወድቆልናል እልል እንበል
ተሰቅሎ ሞትን የሰቀለ
ተወግቶ መርዙን የነቀለ
በሰይፍ አይደለም ጀግንነቱ
በፍቅር እንጂ በእስራቱ/በእትራቱ
ካፎቱ ፍቅርን የመዘዘ
በሞቱ ሞትን የገነዘ
አንበሳችን ነው የይሁዳ
ሁሌም አዲስ ነው በማለዳ
ጀርባው በጅራፍ ተነቀሰ
በሀር ፋንታ ደም ለበሰ
እንደ ሰው ልማድ አይዋጋ
ፍቅር ብቻ ነው የሱ አለንጋ
የአጥቢያ ኮከብ ነው የሚያበራ
በተፈሩት ዘንድ ተፈራ
ያሳዳጁን ጦር ነቅለን ጥለን
እንዘምራለን መስቀል ተክለን

አየኋት በአይኔ አሻግሬ

አየኋት በአይኔ አሻግሬ
የያሬድን ውብ ዝማሬ
ተቀኘሁ እንደ አባቶቹ
እጀን ለክብሯ ዘርግቹ

ድካምና እንቅልፍ እንደምን ሊረታኝ
ድንጋይ ብንተራስ ፍቅርሽ አያስተኛኝ
አይኔ ቢከደን አለሽ በምናቤ
አልተከለልሽም ነግሠሻል በልቤ

መረማመጃ የሎዛ መሰላል
የዜማ ቤቱ የመቅደስ ጸናጽል
የሰማይ ንጉሥ በበላይሽ ያለ
ድንኳን አድርጎ አንቺን የተከለ

ስምሽ በሁሉ ስለተወደደ
ድንግል ለክብርሽ ፍጥረት አረገደ
ካላመኑት ዘንድ ቢሆንም ዝምታ
ከገብርኤል ነው የስምሽ ሰላምታ

ሳደርስ ውዳሴ መጽሐፉን ገልጬ
ተመለከትኩሽ አይኔ እንባ እየረጨ
በገናን ዳዊት መሰንቆንም እገዘራ
ሰጡኝ ላነሳሽ በክብሩ ተራራ

ሰላሜ ባንተ ነው

ሰላሜ ባንተ ነው የኔ ጌታ
እረፍቴ ባንተ ነው የኔ ጌታ
አልከለከል ምስጋና አልከለከል ውዳሴ ላንተ ውለታ

ጨለማዬ ባንተ በራልኝ ከሰው ትከሻ ወረድኩኝ
የምመራበት ዱላዬ ባንተ ተጥሎአል ጌታዬ
አሁን በግላጭ አያለሁ ሙሉ ሰው ባንተ ሆኛለሁ

የመውገሪያው ድንጋይ ቀረልኝ ጠላቴ በፊቴ አፈረልኝ
በፊትህ አቆምከኝ በጸጋ ገዝተህኛልና በዋጋ
ለውለታህማ ምን እላለሁ ተመስገን ብዬ አልፈዋለሁ

ሰላላውን አጀን አቅንተሀል ሸባነቴንም ተርትረሀል
ደካማነቴ ተወገደ ያ ክፉ መንፈስ ተሰደደ
ታውጆልኛል ነፃነቴ አመልክሀለሁ በሕይወቴ

የአይኔ ላይ ቅርፊት ወደቀ ሸክሙም ከላዬ ወደቀ
በደማስቆ ብርሃን መታኸኝ የራስህ ምርጥ አቃ አደረከኝ
ያ ከንቱ ድካሜ አለፈ ልቤ ለፍቅርህ ተሸነፈ

ቅዱስ ሚካኤል

ቅዱስ ሚካኤል ወዳጅ ነህ ለሁሉ
ዛሬም ቆመሀል በኪዳንህ ላሉ
ክንፍህን ዘርጋ ሚካኤል ቅደም ከፊቴ
ምራኝ መንገዴን እያየሁ ፀንቷል ጉልበቴ
እንዴት ይገፋል ጎዳናው ያላንተ እርዳታ
ሸክሜን ቁረጠው በበትርህ ጭንጫውን ምታ
ተጠመጠመ ጠላቴ በሳት ሰንሰለት
የጌታ መልአክ ሚካኤል በሰይፍ ወርዶበት
የለም በቦታው ስመለስ አጥቼዋለሁ
የሚረዳኝን ተሾሞ አይቸዋለሁ
ከመቃብሩ ድግጋዩን አንከባለህል
ስለረዳኸው ዳንኤል እጅግ ወዶሀል
ይነዋወጣል ባህሩ አንተ ስትመጣ
እግዚአብሔር ይንገሥ ዲያብሎስ መድረሻ ይጣ
አለኝ ትዝታ በቤትህ ከልጅነቴ
ስትሳሳልኝ እያየሁ ፀንቶአል ጉልበቴ
ልዘምር እንጂ ላመስግን ታላቁን ጌታ
አንተን የሰጠኝ ጠባቂ በቀን በማታ

ያስከበርከኝ

ያስከበርከኝ ክበርልኝ
ከፍ ያረከኝ ከፍ በልልኝ
ልቤ አቅንቶአል ወደ ዙፋንህ
ጠዋት ማታ ሊያገለግልህ
ሞገስ ስለሆንከኝ ጉልበቴና ክብሬ
ካንተ ያገኘሁትን አልዘልቀው ዘርዝሬ
ቤትህ አድጌአለሁ ስጠይቅ ስሰማ
ከፍ ብያለሁኝ ስምህ ሆኖኝ ማማ
ሳትሰስት ሳትቆጥብ ጸጋን ሰጥተህኛል
የቀረብኝ የለም ፍቅርህ በዝቶልኛል
የልቤ ማጎደር ጽፎታል ሥራህን
መቼም አትጥልም ያገለገለህን
እድፍ የሌለብህ ስህተት የማያውቅህ
እውነት የከበበው ፍርድና ችሎትህ
መልክና ቁመና ባንተ ፊት ባዶ ነው
ልቦናን አይተህ ነው ምትሾመው ምትሽረው
በእኔ ሥራ ሳይሆን ጌታ ባንተ ጸጋ
ስለወደድከኝ ነው እንዲሁ ያለ ዋጋ
መቆሜ መኖሬ በፍቅርህ ነውና
ታሪኬ ነህ አንተ የእኔ ሁለንተና

ሮሆቦት እያልን

ሮሆቦት እያልን እንዘምር በእልልታ
ጌታ አብዝቶናል ውሎልናል ውለታ
የዝማሬ ነው የምስጋና ሰዓቱ
የእግዚአብሔር ልጆች ክንዳችሁን አበርቱ
ቃኝተንዋል በገና መሰንቆውን
ሳናቆርጥ በፊቱ ምስጋናውን
በእጣኑ ጢስ ታጅቦአል ውዳሴያችን
ይሰማናል ያበዛን አምላካችን
ለአገልግሎት ስንወጣ ጥቂት ነበርን
በረሀውን ስንጓዝ በዛ ዘመን
ለመለምን በፍቅሩ እንደዋዛ
ለዚህ ቀን አስቦናል ጌታ ለካ
ሁሉም ሆኖአል በጊዜው በፈቃዱ
እንቅፋቱም ተነሥቶአል ከመንገዱ
ያነሳሳል ያበረታናል ገና
ዓለምን እንከድናል በምስጋና
ስናመሰግን ውለን እናድራለን
ያለ ድካም በፊቱ እንቆማለን
እንኳን በምድር በሰማይ በበጉ ፊት
ዝማሬአችን ይሰማል እንደ ዳዊት

እንድንበዛ ጠራን

እንድንበዛ ጠራን ምድርን እንድንሞላ
ሌላ አምላክ የለንም እኛ ከእርሱ ሌላ
ሲገሉን አበዙን ከርስታችን ገብተው
ታላቅ አምላክ አለን ማንንም የማይተው
አሸነፍን ዛሬ እግዚአብሔር ተዋግቶ
በእልልታ ደመቀ መቅደሱ ተሞልቶ
አህዛብ ቢበዙ ከቁጥር ቢተርፉ
አንነዋወፅም የእግዚአብሔር ነው ሰልፉ
ከጭብጥ ላያልፉ በኛ ላይ ቢነሱ
በበትር ያስራቸዋል ኃይሉን ለሚረሱ
መሰማሪያው ጠቦአል አስወግዱት ዛሬ
በጎቹ ገብተዋል ተሞልተው ዝማሬ
ቅዱስ መንፈስ ቃኘው ማዳኑን ሊያወራ
ክርስትያኖች በዙ በእግዚአብሔር ሥራ
ጊዜው ክፉ ቢሆን ቢፎክር ጠላት
አምልጠናል እና አለን በሕይወት
የበገና ሥራ ለመደ ጣታችን
ሁሌም አዲስ መዝሙር ለእርሱ ለአምላካችን

ኮከብ ሲወጣ አየሁ

ኮከብ ሲወጣ አየሁ ከልዳው ሰማይ
ኃያሉ ጊዮርጊስ ቆሞአል ዘንዶ ላይ
ቤሩታዊት ተነሽ አትሞችም ተዕናኒ
አውራው ተሸንፎአል ባምላክሽ እመኚ
ሕዝቡን የሚያስጨንቅ ካልገበሩት ብሎ
ጊዮርጊስ አደቀቀው ከእግሮቹ ስር ጥሎ
የንጉሥ ልጅ ቤሩት እጣው ላንቺ ሆኖአል
ከግንዱ ሊፈታሽ ፈረሰኛው ቆሞአል
በጣአታት መንደር አዲስ ፀሐይ ወጣ
በጽድቅ እያበራ ጊዮርጊስ ታጥቆ መጣ
እንግዲህ አጽሎን አቴና ሆይ አፈር
ምድሪቱን ይገዛል ያምላካችን ክብር
ዱዲያኖስ መንግስቱን አልቻለም ሊያፀና
ታላቁ ሰማዕት ቅጥሩን ሰብሮአልና
ባነገበው መስቀል አምላኩን ገለፀ
የድል ወጣት እርሱ ጭፍሮቹን ገሰፀ
በኤድራስ ተራራ ቅኔን ያስተማረ
ድንቅ ነው አጥንቱ በኃይል የከበረ
ታምራቱ በዝቶ ገድሉን ደመደመ
በጸጋው ቃልኪዳን ትውልዱን ጠቀመ

እንደኔ የረዳኸው የለም

እንደኔ የረዳኸው የለም
እንደኔ ያነሳኸው የለም
የፍቅርህ ውለታ በዝቶብኝ
አልጠግብም ላንተ እየዘመርኩኝ

የኃጢአት ጠባሳዬን ሽሮ - ዘመኔ በአዲስ ተጀምሮ
በሞገስ አልኩኝ ቀና ቀና - ላንተማ ዘምራለሁ ገና
ከቃሌ ይቀድማል እንባዬ - ያንን ቀን ሳየው ዞር ብዬ
ስንቱ ሌት ስንቱ ማታ አለፈ - የእኔን ሰልፍ ጌታ አያሸነፈ

ፍቅር ነህ ወዳጄ ፍቅር ነህ
ፍቅር ነህ አንድዬ ፍቅር ነህ
ሰው አይረሳም ይራራል ውብ አይንህ

ሳይመታኝ የጨበጡት ድንጋይ - እጃቸው ተያዘ ከሰማይ
ሳለቅስ ለብቻዬ ቆሜ - መጣልኝ ኢየሱስ ሰላሜ
በልብስህ ከደንከው በደሌን - መስቀልህ ጥሎታል መስቀሌን
የሞቴ ጦማር ተቀደደ - አያፍርም አንተን የወደደ

የሞት ቃል ተሰዶአል ከቅጥሬ - ሰጥተኸኝ የሕይወትን ፍሬ
በአጥንትህ ግራ ጎኔ ሞላ - ካንተ ነው ትዳርና ተድላ
አየሁህ በመምሬ አድባር - ስትመጣ ቤቴን ልታከብር
ግባልኝ የማቀርበው አለኝ - ባሪያህን ጌታዬ አትለፈኝ

ሲመሽ ይመጣል ሲመሽ - ወዳጄ ያልከው ሲሸሽ
ሲመሽ ይመጣል በማታ - የእኔ የምትለው ስታጣ
ሲመሽ መጣልኝ ሲመሽ - ወዳጄ ያልኩት ሲሸሽ
ሲመሽ መጣልኝ በማታ - የእኔ የምለው ሰው ሳጣ

የማይሸረሸር አለቴ

የማይሸረሸር አለቴ የማይናጋ መሠረቴ
ኢየሱስ ክርስቶስ ሞገሴ አንተ ነህ የጽድቅ ልብሴ
ቀራንዮ ላይ የቆመ
በፍቅር የተተለመ
ከፊቴ ተነሰነሰ
ደምህ ሕይወቴን ወረሰ
አፎይ ልበል ልዘምር ሆነህኛል ጌታ ክብር
የሲና ምድር ህብስቴ
የተከተልከኝ አለቴ
መርገሜን ሰብሮ አለፈ
ሰላምህ ውስጤ ሳረፈ ... እፎይ ልበል ...
የማትደፈር ክልሌ
የድል አርማዬ አክሊሌ
ዓለምን ማሸነፊያዬ
አንተ ነህ ክንዴ ጌታዬ ... እፎይ ልበል ...
መዳፎችህን አይቼ
በእንባ እረጠቡ ጉንጮቼ
ትዝታዬ ነህ ዘወትር
የእጅህ ወለላ ያ ፍቅር ... እፎይ ልበል ...

ያንተን ያንተን

ያንተን ያንተን ብናወራ ብንናገር
ችሎታህን ቸርነትህን ብንዘረዝር
አንጠግብም አንረካም እግዚአብሔር
ተጠምተህ አጠጣህን ተርበህ አበላህን
ተወግተህ ተገርፈህ በቁስልህ ፈወስከን
መቃብር ስትወርድ ገነትን ወርሰናል
አቤት ያንተ ውለታ ማንስ ይከፍለዋል
ስምክን ተሸክመን ዞርን ሀገር ላገር
ዝናህን ክብርህን ላለም ልንመሰክር
ዘወትር ጉንጭ ይሰፋል ፍቅርህ ጉልበተኛ
ሳንጠራህ ሳንወድህ ውለንም አንተኛ
ቅዳሴ ቢቀደስ ቢቆም ማህሌቱ
ኪዳኑ ቢሰማ ሲደርስ ሳህታቱ
ቢሰበክ ቢዘመር ቢደለቅ አንድምታ
ሁሉም ለክብርህ ነው ስላንተ ውለታ
ስንቱን እንቁጠረው ስንቱን እንናገር
ቃላት አይገልፀውም የፍቅርህን ምስጢር
ያልረታኸው የለም ያላሸነፍከው
ሁሉም ተማርኮ ነው እጁን ያነሳው

ለጥርሳቸው ንክሻ

ለጥርሳቸው ንክሻ ያላረገን እግዚአብሔር ይመስገን/2/
እንዘምራለን እልል እያልን/2/

የዝማሬን ልብስ አውልቁ ካህናት
ጌታን ለናቀ አይሰምርም በገና
ከሚጠቡት አፍ ወጥቶአል ምስጋና
የእግዚአብሔር ሥራ ይወጣል ገና
የአምላኬ ዝና ይወጣል ገና

አልሞትንም እኛ አለን በሕይወት
የመስቀሉ ቃል ሆኖናል ጉልበት
የእግዚአብሔር ጸጋ ከእኛ ጋር ያለው
ታሪክ ሲለውጥ ለካ እንደዚህ ነው
ሲገሉን በዛን ሲገፉን ጸናን
ኃይሉ ወደቀ ወደረኛችን
ፀሐይ አትጠልቅም በልጆቹ ላይ
የሚጠብቀን አለ በሰማይ

ቀስቱም አለቀ የሚወረወረው
ነፍሰ ገዳዩን እግዚአብሔር አሰረው
እኛ አንመካም በሰረገላ
ጉልበትም የለን ከእግዚአብሔር ሌላ

አንተ ሳታሻግረው

አንተ ሳታሻግረው ያለፈ ሰው ማነው
ጌታ ሳትደግፈው የቆመ ሰው ማነው
እግዚአብሔር ታላቅ ነው አምላካችን ልዩ
በምድር መካከል ደግሞም በሰማዩ

ልቤ ባንተ ጸና በረታ በስምህ
ተራራውን ሜዳ ሲያደርግለት ክንድህ
እንደ ወንዝ ፈሰሰ ሰላምህ በዛና
ሃሌ ሃሌ ሉያ ይድረስህ ምስጋና /2

የተራበ አንበሳ ሰውን ይታገሳል
የዳነው ዳንኤል አንተን መች ይረሳል
ጠላቱን ለውጠህ ወዳጅ አደረከው
ክፉውን በመልካም በበጎ ቀየርከው /2

ህይወት ካንተ ጋራ ጣፋጭ ነው እንደ ወይን
እጅግ ማትረፊያ ነው የባረከው ዘመን
ስንወጣ ስንገባ ጠባቂ እረኛ
እጅግ በዝታ ታየች ቸርነት በእኛ /2

ኃይልን በሚሰጠኝ

ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁለን እችላለሁ
መከራም ቢገጥመኝ ለበጎ ነው ብዬ አልፈዋለሁ
በሰንሰለት አስረው በወኅኒ ቢጥለኝ
መከራን አብዝተው እጅግ ቢያስጨንቁኝ
ለበጎ ነው ብዬ ተስፋ አድርጌሃለሁ
ይሁን አንተ ያልከው እገዛልሃለሁ
ትናንትናም ዛሬም አንተ ያው አንተ ነህ
ፍቅርህ አይቀየር ወረትም የለብህ
ስምህን መጥራቴ ሞገስ ሆኖልኛል
ጠላቴ ቢፎክር መች ያሸንፈኛል
በመከራው መጽናት ጉልበቴ ደከመ
ትካዜ ከቦኛል ተስፋዬም ጨለመ
ነገር ቢሆን ባይሆን አንተን እንዳከብር
አድለኝ በፀጋህ ጌታ ያንተን ፍቅር
ከሀገር ወጥቼ በዱር መሰደዴ
ከባዕዳን ሀገር እርቄ መሄዴ
ለበጎ ነውና መቼ ይከፋኛል
ፈጽሞ እንዳልጠፋ ክንድህ ይይዘኛል

መልካም አደረገ

መልካም አደረገ ፈጣሪዬ ለኔ
ማዳንክን ዘወትር አይቻለሁ ባይኔ
የተነጣጠረው ቀስቱ መች ነደፈኝ
የጠላቴ ወጥመድ መቼ ጠላለፈኝ
የፈተና ወጀብ በላዬ ቢነሳ
ይመስገን አምላኬ እኔን የማይረሳ
ክንድህ ሲዘረጋ ከመስጠም ድኛለሁ
አስፈሪውን ባሕር በአንተ ቀዝፌያለሁ
ቆሞ መራመድ የሆንከኝ ጉልበት
ተመስገን አምላኬ በቀን በሌሊት
ለጥያቄዎቼ መልስ አለህ ዘወትር
ታሳምነኛለህ በጥበብ በፍቅር
ዘወትር መካሪዬ የነፍሴ ጠባቂ
እፁብ ነህ አምላኬ ልቤን አስደናቂ
በእንባ ሸለቆ በሐዘን ሳለሁ
የሚያፅናናኝም ድምፅህን ሰማሁ
ተናገር አምላኬ እኔም እሰማለሁ
እረኛዬን ትቼ ወዴት እሄዳለሁ

መረቤን በዓሣ የሞላ

መረቤን በዓሣ የሞላ
ማን አለ ከአምላክ ሌላ
ነገር ሁሉ ውብ የሚሆነው
በአንተ ነው ጌታ በአንተ ነው
በስምህ ስንጀምር ፍጻሜያችን ያምራል
እጅህ ከእኛ ጋራ በጥበብ ይሠራል
ከቶ ያላንተ ፈቃድ ማን ከዚህ ደረሰ
ደስ ብሎት ያደረ ተድላን የቀመሰ
ከብዙ ድንቢጦች እበልጥብሃለሁ
የማትዘነጋኝ ነህ ይዜንን ዐውቃለሁ
የግራው መንገዴን በቀኝ የምትመራ
እስተካከላለሁ ስሆን ካንተ ጋራ
አቤንኤዘር አለህ ሳሙኤል በቋንቋው
በጨለማው ዘመን ስለረዳኸው
አንተን የታመነ ሲሳዩ ይበዛል
ባዶውን የወጣ አፍሶ ይመለሳል
መኻታው ይሞቃል እንጀራህ ያጠግባል
እግዚአብሔር ካለበት ኑሮ ይደላል
ብዙ ብንበለጽግ እልፍ ቢኖረን
ጸጋው ከሌለበት አይደምቅም ድንኳን

መርከቤ

መርከቤ መጠለያዬ
ሞገደን መሻገሪያዬ
ፀጥታ ሰላምም ሰፍኗል
ከእንግዲህ ማን ያስፈራናል
ሲነደል ታላቁ ቀላይ
ተንሳፈፍን በሞት ጀርባ ላይ
መርከብ ሆኖን አምላካችን
ማምለጫ መሸሸጊያችን/2/
በሲና ህግን የሰራ
ሕዝቡንም በጽድቅ የመራ
የሰላም የምህረት ጌታ
ሕይወት ነው ማረፊያ ቦታ/2/
ርግቧ ተመልሳለች
ጥፋቱ ቆሟል እያለች
ቀጤማው ከእጃችን ገብቶአል
በረከት ሰላም ከቦናል/2/
ማዕበል ወጀብ ቢበዛ
አንተ ነህ የህይወቱ ቤዛ
በሞት መካከል ብሄዴም
ከእንግዳህ አልታወክም/2/

ማረከኝ ምስጋናሽ

ማረከኝ ምስጋናሽ ማርያም ውዳሴሽ
ማረከኝ ምስጋናሽ ድንግል ውዳሴሽ
ከልቤ ፈለቀ ምስጋና ለስምሽ ዘምራለሁ ገና
ከልቤ ፈለቀ ምስጋና ለክብርሽ እቀኛለሁ ገና

ከሰማዩ ደረት ተተክለው ዓይኖቹ
መቆሚያዬ ሲረጥብ ርሶ በእንባዎቹ
አየሽኝ በፍቅርሽ መዓዛሽ ቀረበኝ
ለካስ ናፍቆትሽ ነው እናቴ ያስለቀሰኝ

ያውርድ አንደበቴ መወድስ ዝማሬ
ይዝራ ምስጋናሽን ዘላለም ከንፈሬ
ካባውንም ይጣል ይራቆት ለዜማሽ
ይደርብ ከበሮ ትከሻዬም ያንሳሽ

ዝማሬሽ ከለየኝ ከነሜልኮል መንደር
ሰገነት ከሆነኝ የደጃፍሽ አፈር
ይጥቀሰው ቀሚሴ ጉልበቴም ይሳመው
ጽዮን መሃላዬ ዛሬም በቀኜ ነው

በአርያመ ፍሬ ዝናሬ ሲሞላ
መታጠቂያ የለኝ ከምስጋናሽ ሌላ
ይሸነፍ ለፍቅርሽ ይረታልኝ ክንዴ
በገናን ልይዝ ነው ከደርቡ መውረዴ

ማሪኝና ልሂድ

ማሪኝና ልሂድ ወደ ቤቴ ልግባ
ይበቃሻል በይኝ የማነባው እንባ
ደጅሽ ላይ ከወደቅሁ አለፉ ዘመናት
ፈውስን ተጠምቼ አቃተኝ መፅናናት/2/

ቆዩ ከተዘጉ የቤቴ መቃኖች
እጅግ ራቁብኝ የመዳኔ ቀኖች
ዛሬስ ይበቃኛል ልነሳ ካልጋዬ
በምልጃ ፀሎትሽ በሽታዬን ጥዬ/2/
አይነቀል እግሬ ዘላለም ከደጅሽ
ተማላለሽ ብሎ ካልዳሰሰኝ እጅሽ

ወገን ዘመድ የለኝ የሚረዳኝ ቀርቦ
ልቤ ተሰበረ በሀዘን ተከቦ
እንኳን የሚደግፍ የሚሰማኝ ጠፋ
አሳየኝ በዓይኔ ይህች ቀን አልፋ/2/
ያሰብኩት እስኪሆን አይኔ አያንቀላፋ
ምህረት ከሞላበት ከደጅሽ አልጥፋ

የሚያድንሽ የለም እያሉ ብዙዎች
ተግተው ቆጠሩብኝ የሞቴን ቀናቶች
በኃዘን አጎንብሼ እንባዬን ረጫለሁ
ድንግል ካልዳሰሽኝ መቼ ቀና እላለሁ/2/
እኖራለሁ በተስፋ አንቺን ተጠግቼ
አልቀርም ዘላለም እየተከፋሁኝ

የእግሮቼን ሠንሠለት ላውልቅ ተፈውሼ
አዲሱን ሰውነት በምልጃሽ ለብሼ
አትድንም ባለኝ ፊት ልቁም በምስጋና
ህመሜን መሸፈን ይቻልሻልና/2/
ማቃሰቴም ቆመ ብሞላ ዝማሬ
ድንግል በጸሎትሽ ታጥሮልኝ ድንበሬ

ማራናታ

ማራናታ ናልኝ ጌታ (2)
ናፍቆቱ ነህ ጠዋት ማታ
አሜን ክበር የድል ጌታ

ልጠጣ ከእጅህ ወለላ
ተጠማሁ ናፈቅሁ እንደ ዋላ
እረፍቱ ሰላሜ እንዲመለስ
ዘይትህ በቁስሌ ላይ ይፍሰስ

በያቦቅ ስታገልህ ባድርም
መውደድህ እኔ አይወጣልኝም
በጥልቁ በከፍታም ሆኜ
ናፈቅሁህ ኢየሱስ አዳኜ

ከፍቅርህ ውቅያኖስ ጠልቄ
ካንተ ጋር ልኖር መናፈቄ
በነፍሴ ተወራርጄ ነው
ክርስቶስ አንተን የማመልከው

በብሉይ ትናፈቅ ነበረ
ልደትህ እየተቆጠረ
መጥተህም ፍጥረት አልጠገበህ
ይኖራል ማራናታ እያለህ

ማራኪው

ማራኪው እየማረከ
ባራኪው እየባረከ
በፍቅሩ ስንቱን እረታ
ሰባሪው የድሉ ጌታ

የሞቴን ወጥመድ ሰባብሮ
በድምፁ ጥልቁን በርብሮ
ሰደደኝ ማተም አትሞ
የአርነት ግርማ ሸልሞ

ሰገባው ያዘንባል ፍቅር
ከአማልክት የለውም ወደር
ተሳስሯል ደሙ ከደሜ
በሞቱ ሰፍኗል ሰላሜ

ሰገባው ያዘንባል ፍቅር
ከአማልክት የለውም ወደር
ተሳስሯል ደሙ ከደሜ
በሞቱ ሰፍኗል ሰላሜ
የጓዳ የልፍኜ ልቀት
አንተ ነህ ክብሬ ሰገነት
ከቦኛል በመላእክቱ
ነጥቆኛል ስቦ ከእሳቱ

ማን አለን

ማን አለን ጌታ ሆይ ካንተ በቀር /2/
በሰማይ ሆነ በዚህ ምድር
ማን አለን ካንተ በቀር

ዛሬ ወዳጅ ነገ ጠላት
ይለወጣ የሰው ህይወት
ያመንናቸው ገፍተው ጣሉን
አንተ ብቻ አትተወን

ባይደላንም የምድር ኑሮ
ብናሰማ ለቅሶና ሮሮ
ባይሳካ ውጥናችን
ባንተ ያምራል ፍጻሜአችን

ሕይወታችን መልኩ ወይቦ
መንገዳችን ሾሕ ተከቦ
ጠላት መጥቶ ስንሰቃይ
ታገልክልን ነሕ ኤልሻዳይ

እንኳን ጮኽን ሣንለምን
አፍሮ አይገባም መረባችን
ስቦ ማውጣት እስኪያቅተን
በአሳ ይሞላል መረባችን

ምስጉን ነው

ምስጉን ነው የተመሰገነ
ባርያውን እኔን ይቅር ያለ
ይመስገን ይመስገንልኝ
ጎጆዬን አምላክ ሞላልኝ

እጅህ ሰፊ እንደሆነ አውቃለሁ ጌታዬ
የጎደለው ሞልቷል ይድረስ ምስጋናዬ
ያጣሁትን ካንተ አግኝቻለሁ
ሁለን ነገር ለበጎ ብያለሁ (2)

ማቄን የቀደደው ደስታ አስታጠቀኝ
ባዶ የነበርኩት ደስታ ተሰጠኝ
ሰጪም ነሺም እግዚአብሔር ብቻ ነው
የሰው ድርሻ በር ማንኳኳት ነው (2)

እገፋለሁ እንጂ እኔ አልጨነቅም
መሠረቴ አንተ ነህ ከቶ አልናወጥም
ስትሰጠኝ የሚታየውን
እንዳትነሳኝ የዘላለሙን (2)

ቢሰጥ አያልቅበት ለጋስ ክቡር ጌታ
ሁሉን ከወነልኝ በልዩ ችሮታ
ድሆች ስንሆን ሁሉ አለንና
አምላካችን ይድረሰው ምስጋና (2)

ምስጋና ለድንግል

ምስጋና ለድንግል ውዳሴ ለማርያም
በእርሷ ምክንያት ድኗልና ዓለም (2)

እናታችን ጽዮን ሰው ሁሉ ይላታል
አዳኝ ያጣው ዓለም ፍሬ አግኝቶባታል
መሰላል ሆኖልን ከሰማይ ደርሰናል
የናፈቅነውን ቀን በዐይናችን አይተናል

ከዘሯ የቀረነው ብፅዕት እንላለን
ከተለየው ትውልድ እንቆጠራለን
የስምሽ ወለላ ጣፍጧል አፋችን
ስንቱን ተሻግረናል እያልን እናታችን

ከከፍታ በላይ ከፍ በይልን
እኛም እንኮራለን እናት ስላለን
በልጅሽ ተጋድሎ ዲያቢሎስ ሲመታ
ዓለምን ከደነ የስምሽ ሰላምታ

የነፍሳችን ታሪክ መልኩ ሲቀየር
በአዳም በደል ምክንያት ሰፍቶ መቃብር
የተስፋችን ሰማይ ከኢያቄም ተወልዳ
ዓለም ተፈወሰ ክርስቶስን ወልዳ

ምስጋና በመቅደስህ

ምስጋና በመቅደስህ ዝማሬ በማደሪያህ
ልሰዋ ጠዋት ማታ ክብሬ ነህ የኔ ጌታ

ሰገነት አይመቸኝ
ካባዬም ክብር አይሆነኝ
ሁሉንም ንቄዋለሁ
ያንተን ቤት መርጫለሁ

ያረጃል የዓለም ዝና
ጥበብም ሆኖ መና
አንተ ግን ያው አንተ ነህ
በሁሉ ትፀናለህ

ከሰማይ በዐይንህ ታየሁ
በፍቅርህ ተጎበኘሁ
በባሕርይ ባለፀጋ
ፈወስከኝ በደም ዋጋ

ቃልህን ነፍሴ ሰምታ
ተዋበች በእልልታ
ወደ እግርህ መረገጫ
መስገዴ አለው ብልጫ

ምስጋና በሰማይ በምድር

ምስጋና በሰማይ በምድር
ውዳሴ በሰማይ በምድር
ሁሉን ቻይ ለሆነው እግዚአብሔር ምስጋና
ከእርሱ በፊት ከርሱም ኋላ ማንም የለም
የወደደን በንፁሕ ፍቅር ለዘላለም
ገና ብዙ እንሰራለን ከእርሱ ጋራ
ምስክር ነን የተመካን የማንፈራ
ረድዔትን እየላከ ከመቅደሱ
ያዘኑትን እያጽናና በመንፈሱ
በልዕልና ይመለካል ይከበራል
የማይሻር ንጉሣችን ነግሦ ይኖራል
ሰባራውን ይጠግናል በዘይቱ
ዘመናትን ያቀዳጃል በምህረቱ
ወድቆልናል ጠላታችን ላይነሣ
አንበሳ ነው እውነት ጽድቅን የሚያገሣ
የተሻለ የበረታ ቅኔ ዜማ
ሁለን በፍቅር ሳይጸየፍ ለሚሰማ
እስከሚያዩት የሰቀለት የወጉት
ይገለጣል እያበራ የእኛ አባት

ምስጋናዬን

ምስጋናዬን ለአምላኬ አቀርባለሁ
በማደሪያው ገብቼ እሰግድለታለሁ
ኤልሻዳይ ነው ጌታ ሁሉን ቻይ
ይፈጸማል አምናለሁ የሌቤ ጉዳይ
ዘንባባዬን ይዤ እንደ ህጻናቱ
ሆሳዕና ልበለው ሰግጄ በፊቱ
ምንም ባዶ ብሆን እውቀት ቢጎለኝ
ለሰሙ ልዘምር ከልካይም የለኝ
አምላኬ በፊትህ ቃል አለብኝ እኔ
ቋንቋዬ መዝሙር ነው ያንተ እንደመሆኔ
በአሚናዳብ ደጃፍ በቅድመ ታቦቱ
ያ የክብርህ ዑደት ጠራኝ ማህሌቱ
የሕይወት ትርጉሜ አንተ ነህ ደስታዬ
ስምህን ማገሌገሌ ክብሬ ነው ደስታዬ
ለታመነው ጌታ ምስክር የሆኑ
ክብረው ተመለሱ ለበረከት ሆኑ
መነሻዬ አንተ ነህ ጉሌበቴና ክብሬ
መድረሻዬም አንተ መደምደሚያ ቅጥሬ
በጽዮን ተራራ ስትገለጥ ያኔ
ነጩን ልብስ አልብሰህ አስነሳኝ ለቅኔ

ሞገድ ሲመታኝ

ሞገድ ሲመታኝ ማዕበሉ
ማን ያድነዋል ሁሉም ሲሉ
በሰላም አለፍኩ በፀጥታ
ሁሉ ተችሎ ባንተ ጌታ/2/

በአንተስ ቁስል ተፈወስኩኝ
ጌታ በፍቅርህ ተማረኩኝ
ሞቴን ሽረኸው ባንተ ሞት
ይኸው አቆምከኝ በሕይወት/2/

ደጅ ስጠና ስማፀንህ
መቼ ጨከነ ጌታ ልብህ
እንደቀራጩ አጎነበስኩ
ምህረት ጸጋህን ከጅህ ለበስኩ/2/

ዘወትር እልል ብል ብዘምር
ስለገባኝ ነው ያንተ ፍቅር
ጌታ ብጠራው ስምህን
ለውጠኸው ነው ታሪኬን/2/

ዓይኖቼ አያዩም ካንተ በቀር
የምትወደድ ምትፈቀር
ዘመድ ወገኔ ሆነኸኛል
እኔን የሚችል የት ይገኛል

ሰላምህ በዛልኝ

ሰላምህ በዛልኝ እንደ ወንዝ ፈሰሰ
በረሃው ሕይወቴ በፍቅርህ ራሰ

ሞቴን ክብሬ አድርጌ የኖርኩበት ሕይወት
በአንተ ተቆረጠ ስትጠራኝ በምሕረት
ዓይኖቼ ተከፍተው ሥራህን ስላዩ
ከጥፋቱ ስፍራ በፀጋህ ተለዩ

መከታ ድጋፌ አንተ በመሆንህ
ተመስገን አለሁኝ ሳልጠፋ ከቤትህ
በቃ ተዘግተዋል የሞት ደጆች ለኔ
ዘወትር ስላለህ ቤዛዬ ከጎኔ

ሰላሳና ስልሳ መቶ እንዳፈራ
እኔም ተመረጥኩኝ ከልጆችህ ጋራ
ለምን ዝም እላለሁ ማዳንህን
ላውራ በደሌ ተረስቶ ለዚህ ክብር ስጠራ

ደግሞም አለኝ ገና ሌላ ታላቅ ክብር
በሰማያዊው ቤት ለዘለዓለም መኖር
ከቅዱሳኑ ጋር በዚያ እንድደመር
የደሙ ዋጋ ነኝ አልፈራም ስናገር

ሰዎች

ሰዎች ፈረዱብኝ አንተ ግን አዳንከኝ
አምላኬ ሆይ ተመስገንልኝ/2 ሌላ ምን ቃል አለኝ
ሊያልፉኝ አልወደዱም ነውሬን ሊሰውሩ
ሰዎች ፈጠኑብኝ በደሌን ሊያወሩ
አንተ ግን ሰብስበህ በፍቅር ሸፈንከኝ
በመተላለፌ አዝነህ ሳትለየኝ
ይህ ፍቅርህ ሰበረኝ አጣበቀኝ ካንተ
ደጅህ ያመጣኛል ሁሌ እየጎተተ
መርከሴን አውጀው ሲያነሱብኝ ድንጋይ
ሰወረኝ ታምርህ ልጅህ ሳልሰቃይ
ወደህ ስለማርከኝ ክፉዎች ተከዙ
ይህ አይደለም ብለው የኃጢአት ደሞዙ
ካንተ በላይ ጌታ ማን ሊያውቀኝ ይችላል
የፍቅርህን ሚዛን ማንስ ያዛባዋል
ማዳንህ ይደንቃል ለወደቅሁት ልጅህ
ምህረትህ ይደፋል ሁሌም በሚዛንህ
እንደሰው አይታይ ፍርድህም ይለያል
ለባርያህ አርነት በምህረት ይፈርዳል
ፍቅር እየዘረዘርክ መንገዴን የጠረግህ
ስለልጅ ጽድቅን ለድኅነቴ ፈረድክ
እኔ አልፈርድብህ/ሽም በሰላም ሂድ/ጅ አልከኝ
ዳግም እንዳልበድል በፍቅር እያየኸኝ
ወደ ጽድቅህ ሕጎች ነፍሴን አፈሳለሁ
እንዲህ ከወደድከኝ ወዴት እሄዳለሁ
አልለይም ካንተ ከፍቅር መድረኬ
አመልካለሁ አንተን ፊትህ ተንበርክኬ

ሰረገላዎችህ

ሰረገላዎችህ የእሳት ናቸው
የሌጌዎን ጭፍሮች ማይችሏቸው
የገሃነም ደጆች ማይችሏቸው
አንተ ብቻ ቅዱስ ኃያል ጌታ
ሳመልክህ እኖራለሁ ጠዋት ማታ

በእሳት ሠረገላ ታጥሯል መንደራችን
ግያዝ ሆይ አትፍራ አለ ፈጣሪያችን
የጠላትን ምሽግ በቃሉ ይቆርጣል
ከእኛ ጋራ ያለው ከእነርሱ ይበልጣል

ከቴማን ተራራ ከፋራን ሲወርድ
ጠላት ይጨነቃል በድምፁ ሞገድ
ጦረኛ አያበዛም ሞአብን ሲመታ
በአህያ መንጋጋ ሺውን ጥሏል ጌታ

የጥልቁን መሠረት በነፋስ አስሮታል
ከሰማያት በላይ ዙፋኑን ዘርግቷል
ዘንባባ ይዛችሁ ግቡ ከመቅደሱ
በምስጋናው ስርዓት እንድትቀደሱ

ወደረኞቻችን ከቁጥር ቢበዙም
እንደ ቃየል ልጆች ሾተል አንመዝም
እንጀራን መግበን እንሰዳቸዋለን
በቀልና ፍርድን ለአምላካችን ትተን

ስለማይነገር ስጦታው

ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን
ቸል ያላለን አምላክ ስንጓዝ ማዕበለን አቋርጠን
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

የሕይወት እስትንፋስ ዘራብን ሕያው እንድንሆን
ይህን ያደረገ አምላካችን እግዚአብሔር ይመስገን
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

ነፋስን ገስፆ ማዕበል አቁሞ የሚያሻግር
የዓለም ፈተና ቢበዛ እርሱ መጠጊያችን
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

ዳግም እንዳንሞት በሞቱ ሞትን የረታልን
የምንመካበት ትንሣኤን ሰላምን የሰጠን
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

ከሲያል እስራት ተፈተን ነፃ የወጣንበት
መስቀሉን ለሰጠን ለአምላካችን እንዘምር በእውነት
ስለማይነገር ስጦታው እግዚአብሔር ይመስገን

ስለምን ወደድከኝ

ስለምን ወደድከኝ ከኔ ምንሸተሃል
በኃጢአት ከምኖር ባርያህ ምን ይገኛል
በበደል ውስጥ ሁኜ ትከተለኛለህ
በፍቅር አይኖችህ በምህረት እያየህ /2/

ሸሸሁ ከመቅደስህ ትቼ ወጥቻለሁ
በባቢሎን መኖር ምኞት ነው ብያለሁ
ያንተ ሀገር አይደለም ብለህ ተከተልከኝ
በምን ስራዬ ነው እንዲህ የወደድከኝ /2/

ከደሊላ ጋር ቢሆንም ውሎዬ
እንደጠፋ ይቅር አላልክም ጌታዬ
ልትፈልገኝ ወረድክ በአህዛብ መንደር
ኃይሌንም አደስከው ዳግም እንደ ንስር /2 /

አይኔ ስትማረክ ስታይ ተሰሎንቄን
ርኩሰት ስትገዛኝ በኃጢአት ወድቄ
ለበደሌ ዋጋ ፍቅር መለስክልኝ
የወደድከኝ ጌታ ክበር ንገስልኝ /2/

ስታነክስ ነፍሴ ግራ ስትጋባ
ፈጥነህ ተቀበልከኝ የፀሎቴን ዕንባ
የዚህን አለም መንፈስ ነቀልከው ከልቤ
መንገዴ ነህ አንተ እውቀቴ ጥበቤ /2/

ስመ ከስም ሁሉ በላይ

ስመ ከስም ሁሉ በላይ
ክብሩ ከክብር ሁሉ በላይ
ሰገደ ፍጥረት ተንበረከከ
በፍቅሩ ልብን እየማረከ /2/

ሸለቆ መቃብር አሸነፈ
ድል ነስቶ በሰማያት አረፈ
ከደነ አለምን አዳረሰ
ከጥልቁ ሙታንን ቀሰቀሰ

ሊሰራ ከተራራው ይዘላል
ለምፃሙን ሸባውን ይፈውሳል
ክርስቶስ ኢየሱስ የተባለው
ልዩ ነው ከስም ሁሉ በላይ ነው

የገነት የሲኦል መክፈቻ አለው
የሚገድል የሚያድንም እርሱ ነው
ሞትና መቃብር አልያዘውም
የምድር ስበት አላስቀረውም

ይድናል ታላቅ ስሙን ሚፈራ
ያመልጣል ከፍፃሜው መከራ
የአውሬው ቁጥር ይደመሰሳል
ኢየሱስ በትውልዱ ይነግሳል

ስመሰክር ዓይኔን እንዳበራ

ስመሰክር ዓይኔን እንዳበራ
ከለከሉኝ ስሙን እንዳሌጠራ
ሙሉ ሰው ነኝ መቼም ዝም
አልልም ያለኝ ኢየሱስ ነው ለዘላለም

በራሳቸው ፈቃድ ጠይቀው መዳኔን
ማመን ተስኗቸው የበራው ዓይኔን
ማዳኑን አውጄ ከመክራብ ቢያስወጡኝ
የማይጥለው ንጉሥ ኢየሱስ አቀፈኝ

ኃጢአተኛ ቢሉም በሙሉ ልባችው
ክብሩን ባይቀበል ጎዶልነታቸው
ለእኔ ግን አምላክ ነው ፈዋሽ መድኃኒት
ጨለማ ማይረታው የላሉት መብራት

የዋህ ወላጆቼን ከቶ አታስጨንቁ
ሙሉ ሰው ነኝና እኔኑ ጠይቁ
ለመሆን ካሻችሁ ደቀመዛሙርቱ
የልባችሁን በር ለጌታ ክፈቱ

ይጣፍጣል መኖር ከክርስቶስ ጋራ
መፍትሄ ስላለው ለሃዘን ለመከራ
ሞትም ጥቅም ሆኗል በጌታ ከሆነ
ዳግመኛ አይሞትም አንዴ እርሱን ያመነ

ስምሽን ለልጅ ልጅ

ስምሽን ለልጅ ልጅ እነግራለሁ
እናቴ በምልጃሽ ሰው ሆኛለሁ
እመቤቴ ስልሽ ነይልኝ
ማዕበል ሳይነቅለኝ

እመቤቴ ብዬ ስምሽን መጥራቴ
ቢራቆትብኝ ነው ባዶ ቢሆን ቤቴ
ዓይኖቼን ከእንባ ከለቅሶ ከልክይ
ልብሽ ይራራልኝ ወደ እኔ አዘንብይ

ባሕሩም ቢሞላ አምናለሁ በልጅሽ
አንገት አያስደፋም እናቴ ጸሎትሽ
ስምሽን ስጠራ እጆቼን ዘርግቼ
ቀስታቸውን ሁለ ጣሉ ጠላቶቼ

ሰላም አለኝ አሁን ይህንን አውቃለሁ
እጅግ ብዙ ነገር በአንቺ አግኝቻለሁ
ማድጋዬ ሞልቶ አለም ተመልክቷል
ምድረ በዳ ልቤ በጸሎትሽ ረክቷል

ስምሽን ጠርቼ

ስምሽን ጠርሼ መቼ አፍራለሁ
ማርያም ብዬ መች እወድቃለሁ
የምጽናናበት ስምሽ ነውና
ድንግል ሆይ ላቅርብ ላንቺ ምስጋና

ጨለማ ውጦኝ በጠላት ሀገር ለዘመናትም ስረገጥ ስኖር
ዲያብሎስ ማርኮ ሲያሰቃየኝ የዓለሙን መድኀን ወለድሽልኝ
ከአባቶቼ ርስት ከሀገር ወጥቼ በአሕዛብ ሀገር ስኖር ተሸጬ
ደርሰሽ አጽናንተሽ አከበርሽኝ ብቸኝነቴን አስረሳሽኝ

ድንኳኑ ሞልቶ ሰው ታድሞ አስተናባሪው በጭንቀት ቆሞ
ምን አቀርባለሁ ብዬ ስቸገር
ምልጃሽ ደርሶልኝ ዳንኩኝ ከማፈር
ያሰብኩት ሀሳብ ደመና ሆኖ ቢበተንብኝ እንደ ጉም ተኖ
ይሆናል ያልኩት ሳይሆን ቢቀርም
በእመ አምላክ እኔስ ተስፋ አልቆርጥም

እናት አባቴ ባያስታውሱኝ ይህች ዓለም ንቃ ገፍታ ብትተወኝ
አንቺ ካለሽኝ ምን እሆናለሁ አውሎ ነፋሱን ባህሩን አልፋለሁ
ጠላቴ ደርሶ ቢያንገላታኝ መከራ አብዝቶ ቢያስጨንቀኝ
አላቋርጥም ያንቺን ምስጋና ውለታሽ ድንግል አለብኝና

ክፉዎች ደርሰው ቢዝቱብኝ አንቺን መውደዴን አያስተውኝ
በአሕዛብ መሀል ስምሽን ስጠራ መከታ ሁኚኝ እናቴ አደራ
ጠላቴ ደርሶ ቢያንገላታኝ መከራ አብዝቶ ቢያስጨንቀኝ
አላቋርጥም ያንቺን ምስጋና ውለታሽ ድንግል አለብኝና

ሥራህ ትክክል ነው አምላኬ

ሥራህ ትክክል ነው አምላኬ ፍቅርህ እጅግ ትልቅ ነው አምላኬ
ቀን የጣለውን ሰው አምላኬ ያላሰብከው ማነው
ሚዛን የሚደፋ ሥራ ሳይኖረኝ
ፍትሃዊ ችሎታህ ሳትመረምረኝ
አይተህ እንዳላየህ እያለፍክ ሁለን
እንድንኖር ፈቀድክ ይህንን ዘመን
ሰው ሮጦ ደክሞ በራሱ መንገድ
ማረፊያ አላገኘም ልቡ እንደሚፈቅድ
አንተን ይዘነጋል በተድላ ዘመኑ
ሲቸገር አትጨክን እንዲህ በመሆኑ
እጁን በአፉ ይጫን አያጉረምርም ሰው
የሰማዩን ጌታ ማን ነው የሚከሰው
አንዳች ሳታጎድል ጨክነህ ሳትፈርድ
እግዚአብሔር አንተ ነህ ሁሉን የምትወድ
ዓለም ብትዘምር የፍቅር መዝሙር
ሰውን ብትሰበስብ አንድ ጥላ ሥር
ሁሉ ይሸሸዋል አንደኛው ሲቸገር
የጌታ ፍቅር ግን የለውም ዳር ድንበር

ሺውን በአህያ መንጋጋ

ሺውን በአህያ መንጋጋ
ውዴ ስላለህ ከእኔ ጋ
ሶምሶም ጉልበታሙ ተባልኩ
አንተን ከፊቴ እያስቀደምኩ
ወንጭፍም የለኝ ሰረገላ
ትምክት አላውቅም ከአንተ ሌላ
በፀጉሬ መሐል ሞገስ ሆነህ
የሆነው ሁሉ በአንተ ሆነ
በኤሽታኦል ላይ መንፈስህን
በእስራኤል መንደር ሰላምህን
ፈጥነህ ላክልኝ እንደገና
ጠላት ጨርሶ መች ጠፋና
የኮሬብ ዋሻ እርጉም ይሁን
አሁን ይጣለሁ ምሶሶውን
ደሊላም ይብቃሽ ያ ሽንገላ
አልመለስም ወደ ኋላ
ግዙፉን ዓለም በአንተ ዋጥነው
የእልልታ መንደር አደረግነው
ፊታችን ዛሬ አብለጭልጭል
ብንሞትስ ታዲያ ምን ይቆጫል

ቀስተ ደመና

ቀስተ ደመና የኖህ ቃልኪዳን መተማመኛ
ቃል ገብቷል ባንቺ እንዳያጠፋን በሞት ዳግመኛ
መድኃኒት ወልደሽ ለጠፋው ዓለም ደስታ የሆንሽ
ሰንደቃችን ነሽ ለዓለም ምንጠቁምሽ
ጌታ ምልክት ይሰጣችኋል
የድንግል ፍሬ ያድናችኋል
የአዳም ታሪክ ተገለበጠ
ሞት በልጅሽ ሞት ስለተዋጠ/2/
አሰልፎናል ለክብርሽ ዜማ
የመማፀኛ የድል ከተማ
ሞልቶ ይፈሳል ፀጋ ምልጃሽ
ክብራችን በዝቷል ስናከብርሽ/2/
መልአክ ነገረን ታላቁን ነገር
እንደምትወልጂው ያለ ወንድ ዘር
ጌታ በልቡ ስለሳለሽ
ይህ ሁሉ ፍጥረት ብፅዕት አለሽ /2/
ፍቅር ነውና ዓላማው ለኛ
የእግዚአብሔር አብ ልጅ ታማኙ እረኛ
በነቹን ሊያድን ሲገለጥ በዓለም
ሐረግ የሆነው እንዳንቺ የለም/2/

ቀርንዮ

ቀራንዮ/2/ጎልጎታ
አልረሳውም የርሱን ፍቅር ያን ውለታ
እርጥብ መስቀል ተሸክመህ
ዳገት ወጥተህ ቁልቁል ወርደህ
ሰው ያረከኝ ክርስቶስ ነህ
ይታየኛል ያገጽህ
የከበደው መከራህ
አቤት ስቃይ አቤት ፍቅር
ማን ይከፍላል ይህን ብድር/2/
ደምና እንባህ ተቀላቅሎ
በአይሁድ ጅራፍ ጀርባህ ቆስሎ
ተዘርግተው እጆችህ
ነፃ ወጣን ባሮችህ/2/
በምራቁ ዓይን የሰራ
ዕውራንን የሚያበራ
ተተፋበት ተገረፈ
ስለ ፍቅር ተሸነፈ/2/
ልቡ በጥም ተቃጠለ
ሲጮህ ሰሙት ውሃ እያለ
ውሃ አፍልቆ ለሰጣቸው
ሀሞት ሰጡት የግፋቸው/2/
ልብሱን ገፈው ተካፍለው
እጅና እግሩን ችንክረው
እንዳጠፋ ወንጀለኛ
ተሰቀለ ደጉ እረኛ/2/

ቀኑ መሸቷል

ቀኑ መሸቷል ጌታ ሆይ
አትሂድ ከኛ ዘንድ ቆይ
እደር ከኛ ጋራ ኤማሁስ
ባንተ ነፍሳችን ትቀደስ /2/

ሲቀላቀለን መሃላችን
አልመሰለንም አምላካችን
ለካስ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነው
አብሮን ከእኛ ጋራ ያለው /2/

አብሮን ተጓዘ ደሃ መስሎ
መጣ ልጆቹን ተከትሎ
አሜን ሞትን አሸንፏል
መቃብሩ ባዶ ሆኗል/2/

ባርከህ ስትሰጠን ማዕዱን
ሁሉን ተረዳን ምስጢሩን
አገኘን የልብን ሰላም
መልሰን ኢየሩሳሌም/2/

ወደ ኢየሩሳሌም እንመለስ
ከሞት ተነስቷል ጌታ ኢየሱስ
ይውጣ ኤማሁስ ከልባችን
አብረን እንኑር ከአምላካችን/2/

ቅዱስ ነህ

ቅዱስ ነህ ጌታ ቅዱስ ነህ
ንጉሥ ነህ ዛሬም ንጉሥ ነህ
ለታረድከው ክብር ይገባሃል
በዕፀ መስቀል ስለ እኛ ሞተሃል

ንጉሥ ሆይ ውበትህ ያማረ -- ዝናህም በዓለም ተነገረ
በጽድቅህ ፍርድን ትፈርዳለህ -ከአማልክት ማነው የሚመስልህ
ሁሉንም የምትገዛ ጌታ -- ለአንተ ነው ውዳሴና እልልታ
ለስምህ ይገባል ክብር -- በሰማይና በምድር (2)

ቅደስ ነህ ለሰው የምትራራ -- ንጉሥ ነህ በጽዮን ተራራ
ታርደሃል ክብር ይገባሃል-- መጽሐፉን በኃይል ገልጠሃል
ለበጉ ይሁን አዱስ ቅኔ -- ማዳኑን አይቻለሁ ባይኔ
በፊትህ አሕዛብ ሰገዱ -- ልማት ነው አንተን ለሚወዱ

ማን ይሆን አንተን የማይፈራ -- ያላየ በምድር ስትሠራ
ምሕረትህ የደረሰላቸው -- ሊያመልኩህ ወጡ ከቤታቸው
ለበጉ ይሁን አዱስ ቅኔ -- ማዳኑን አይቻለሁ ባይኔ
በፊትህ አሕዛብ ሰገዱ -- ልማት ነው አንተን ለሚወዱ

ቋንቋዬ ነሽ

ቋንቋዬ ነሽ ድንግል መግባቢያዬ
መልስ የማገኝብሽ ከጌታዬ (2)
በአንቺ ቀርቤአለሁ ከአምላኬ ፊት
ቤቴን ሞልቶልኛል በበረከት (2)

በምን ሥራዬ ነው በፊቱ የቆምኩት
መቼ በቅቼ ነው ስሙን የጠራሁት
አስታራቂ እናት አንቺን ስለሰጠኝ
ስለ ቃልኪዳንሽ አቤት ልጄ አለኝ

ቅድስና ሕይወት ከኔ ተሰውሮ
በውሸት በሀሜት አንደበቴ ታስሮ
በእመ አምላክ ምልጃ ሰው ሆኛለሁ
እንደ መላዕክቱ ይኸው ዘምራለሁ

ስለ እመ አምላክ ብሎ ያፈረ የለም
በአንቺ ያልከበረ ሰው አይገኝም
እንደ ባለ ማዕረግ እኔም ሰው መባሌ
አንቺን አግኝቼ ነው ድንግል መሰላሌ

ሰላም ለኪ ብዬ ስጀምር ጸሎቴን
ሀሴት ይሞላዋል መላ ሰውነቴን
እንደ ቅዱስ ኤፍሬም በምስጋናሽ ልጽና
በእጆችሽ ያለው አምላኬ ነውና

በሃዘኔ በጭንቀቴ

በሃዘኔ በጭንቀቴ መፅናኛዬ ነሽ እረዳቴ
እመ አምላክ አደረ ድንግል እመቤቴ/2/

ለዓለም ተዘርግቶ እጇ ባዶ ሆኗል
የራሴ ላይ አክሊል ተሸቀንጥሮ ወድቋል
ከኤልዛቤል ሸሽቼ መጣሁኝ ወዳንቺ
የጎሰቆልኩትን እኔን ተመልከቺ

የእግሬ መሰናከል ለዓለም ደስታ ነው
ተስፋ ቢስ መሆን ለጣለቴ ድል ነው
የደስታ መፍሰሻ የኤልዛቤጥ ዘመድ
እንዳልሰናከል ምሪኝ በመንገድ

ምድር ትለኛለች ተስፋ ቢስ ብቸኛ
ሳለቅስ ሳነባ አይታኛለችና
ከቤተ መቅደሱ ለኔስ እናት አለኝ
በሃዘኔ ሰዓት አለሁ የምትለኝ

ከአመድ የወደቀ ትንሽ ገንዘብ አለሽ
ልብሽ ራርቶልኝ ፈልጊኝ አጥብቀሽ
አምነቴ እንዳይጠፋ እንዳልደክም ልጅሽ
አድኔአለሁና ከደጀ ሰላምሽ

በማኅፀን ቅኔ

በማኅፀን ቅኔ ለማርያም ተሰማ
በተራራማ አገር በኤፍሬም ከተማ
ዮሐንስ ይናገር በረሃ ያደገው
ድንግል ስትናገር ምን እንዳዘለለው

የእናቱ ማኅፀን የቅኔ ርስት ሆነች
ድንግል የአምላክ እናት ፊቱ ስለቆመች
በሃሴት ዘለለ ዘመረ በደስታ
ከድንግል ሲወጣ ታላቁ ሰላምታ

በድንግል ማኅፀን ስላየ ጌታውን
ከመወለድ ቀድሞ ሰማነው መዝሙሩን
ትንቢቱ ሊፈፀም በሆድዋ ሲነግስ
ሰገደ ለአምላኩ የስድስት ወር ፅንስ

ጀመረ ስብከቱን ገና ሳይወለድ
ተፈጥሮ መች ቻለ ነቢዩን ለማገድ
አፉ ተከፈተ በታላቅ ምስጋና
በእናቱ ማኅፀን ድምፅን አሰማና

የዮሐንስ እናት ኤልሳቤጥ ገረማት
ልጇ በማኅፀን ቅኔ ሲቀኝባት
ድምጿን ከፍ አረገች ዓለም እንዲሰማ
ሞላት መንፈስ ቅዱስ ለመዝሙር ለዜማ

በልቤ ከተማ

በልቤ ከተማ ተመላለስበት
ይረጋል ሕይወቱ አንተ ስታልፍበት /2/
ወደልፍኜ ግባ እረፍ በምንጣፌ
እንዳመልክህ ጌታ እንባዬን አርግፌ /2/

ባለፀጋ ስትሆን ድሆች ከበውሃል
ለንግስና ዙፋን አህያን መርጠሃል
አጀብ አትፈልግም አውቅሃለሁ ጌታ
ብቻህን ነበርህ ደጀን ስትመታ

ለጠላት አሰራር ዋሻ የሆንኩትን
ስራኝ እንደገና ቤተ መቅደስህን

ድንግዝግዝ ኑሮዬ በምራቅህ ይብራ
ጨለማ አይዝህም አንተ ስትሰራ
ማረኝ ያሉህ እጆች ሲያጨበጭቡልህ
ሰምቼ አልቀረሁም በብርሃን አየሁህ -- **ለጠላት** --

ከያዕቆብ ጉድጓድ ብቀዳም አብዝቼ
ዛሬም በጥማት ነኝ ከቶ መች ረክቼ
የህይወት ውሃ ምንጭ ነፍስን የምትመልስ
በበረሃው ልቤ ለዘላለም ፍሰስ -- **ለጠላት** --

በማንም የማልቀይርህ

በማንም የማልቀይርህ
በምንም የማልወጥህ
ኢየሱስ ለእኔ ልዩ ነህ
አባቴ ለእኔ ልዩ ነህ
ከማዳን ይበልጣል ማዳኑ
አዲስ ነው ሥራው በየቀኑ
ሕመሜ ተወግዷል ሞቴ
ፈውሴ ነህ ቤዛ መድኃኒቴ
መስቀል ላይ ሆነህ ስትጮኽ
ቀስቅሶኝ የፍቅር ሲቃህ
ከዓለም መጣሁኝ ኮብልዬ
አባቴ ወዳጄ ነህ ብዬ
ይሞቃል እቅፍህ ምቹ ነው
ልቤ አርፏል ማንም አያደክመው
የዛሬ የነገም ታሪኬ
ተጽፏል ባንተ ተማርኬ
ውድ ነው ከቀይ ዕንቁ በላይ
ማደሪያው ጫፍ የሌለው ሰማይ
አልወጣም ከፍቅርህ እልፍኝ
የቱ ነው ከአንተ የሚለየኝ
አርቆ ነገን ያይልኛል
አምናለሁ እጅግ ይወደኛል
ሰማልኝ ጠላት ሲመክርብኝ
ምሕረቱን አላጎደለብኝ

በምህረት በይቅርታ

በምህረት በይቅርታ -- ያሰባሰበን ጌታ
ፍቅር ነው ለዘለዓለም -- እንደ አምላካችን የለም
የጠላትን ክንድ ሰብሮ -- ባሕር ከፍሎ አሻግሮ
ምድረ ርስትን ሰጥቶናል -- በማዕረግ አቁሞናል
ሰይጣን አንገቱን ደፋ -- ርስታችንም ሰፋ
አስገባን ክንፉ ሥር -- ሰበሰበን በፍቅር
ሰርክአዲስ ነው አዋቂ -- ማለዳ ተናፋቂ
ነጋ ጠባ ስለእኛ -- የማይደክም የማይተኛ
ስንወድቅ እያነሳ -- በደልን እየረሳ
አባት ሆኖናል በግልጥ -- ሳይከፋ ሳይለወጥ
የሲና ንዳድ ግለት -- ከቶ አልሰጠንም ለሞት
ዝለትና ቸነፈር -- አላስቀረንም በዱር
መዓልቱን በደመና -- ሌሊት በብርሃን ፋና
ወደ እቅፉ ሳበን -- እየመገበን መና
ከሰፈር አውጥቶናል -- ድንኳኑን ተክሎልናል
በመንፈስ እንሰግዳለን -- በስሙ እንገዛለን
ለሞት እንዳንተኛ -- ዓይናችንን አበራ
ይኸው ተሰብስበናል -- ወደ ሕይወት ተራራ

በምስጋናህ

በምስጋናህ ተማርኳል ልባችን
በውዳሴህ ረክቷል ነፍሳችን
ስለወደድክ ስላፈቀርከን
ስለ ክብርህ እንዘምራለን

ለዘላለም የማትረሳን የማትተወን
ቸርነትህን ምህረትህን ያረክልን
እንሰዋለን የምስጋናን መስዋዕት --
በቀንና በሌሊት

የሰራኸውን በጎነት ስናስብ
በመገረም በመደነቅ አልን እፁብ
ለአንተ ክብር ቅኔና ውዳሴ --
እንደ አሮን እንደ ሙሴ

ተቀኘልህ በመሰንቆ በበገና
ሕዝብህ ቆሞ ለውዳሴ ለምስጋና
አይቷልና ቀራንዮ ፍቅርህን --
ሊያከብር ወጣ ስምህን

በስራህ ተገርመናል ተደንቀናል
ንፁህ ፍቅርን ቀራንዮ ላይ አይተናል
ስናመልክህ እንኖራለን እስከ ሞት --
አግኝተናል በአንተ እረፍት

በምን ደስ ላሰኝህ

በምን ደስ ላሰኝህ ጌታዬ ሆይ
በምን ደስ ላሰኝህ አምላኬ ሆይ
ዓለምና መላው ያንተው አይደለም ወይ
የፈጠርከው ሁሉ ያንተው አይደለም ወይ

ኪሩቤል ሱራፌል ቅዱስ ስሉስ ያሉህ
መላዕክት በራማ የሚያመሰግኑህ
ድንቅ መካር አምላክ ኤሌሻዳይ ነህና
ትቢያ ነኝ ምን ልስጥህ ምንስ አለኝና

ቅደሱን መሥዋዕት ልዑል ስለሚወድ
ምን ይገፍ ልምጣና በአምላኬ ፊት ልስገድ
ወደ ላይ በሰማይ ወደ ታች በጥልቀት
አምላኬ የት አለ የማትገኝበት

በኪዳን በጸሎት ቅዳሴ ሰዓታት
አንተ የሰጠኸን የመንፈስ ቅዱስ ሀብት
መልሰን ወዳንተ ብንሰጥ ምንድነው
ተወው ጉዳችንን ስስታችን ይኸው

ሀብትና ንብረቱስ ጉልበቱስ ምንድነው
ጤናዬን የሰጠኝ ካንተ በቀር ማን ነው
በሰጠኸኝ ዕድሜ በሕይወት ዘመኔ
ከገላዬስ ቢሆን የትኛው ነው የኔ
ከአካላቱስ ቢሆን የትኛው ነው የኔ

አበረታኝ ፍቅርህ

አበረታኝ ፍቅርህ ጌታዬ
አበረታኝ ክንድህ አምላኬ
በስምህ ድኛለሁ በፀጋህ
በማደሪያህ ሆኜ ስጠራህ

ሰዶም ስትቃጠል መርገሟ ሲበዛ
ሊተወኝ አይሻም ልጁን እንደዋዛ
ሕጉን በማሰቤ አምላክ ፈረደልኝ
ጎትቶ የሚያወጣ መልአክ ሰደደልኝ

በገናን መደርደር አያቆምም ጣቴ
የወንጭፌ ድንጋይ አንተ ነህ ጉልበቴ
የሳያልን ካባ አውልቀህ ጣልክልኝ
የፍልስጥኤሙን ሰው ክንድህ ሰበረልኝ

ሦስት ጊዜ ስክድህ አላውቅህም ብዬ
ዶሮ ስለጮኸ ትዝ አልከኝ ጌታዬ
መጣሁኝ በዕንባ ከአይሁድ እሳት ስር
ከሃዲ ሳትለኝ አኖርከኝ በፍቅር

ሳምራዊት ናት ሳትል ክብርን የሰጠሽኝ
እንዳንተ ከአይሁድ ፍቅርን ማን አሳየኝ
ምስጢራን በሙሉ ነገርከኝ ጌታዬ
የፍቅር ውሃ ቀዳሁ እንስራዬን ጥዬ

በሰማይ ለእግዚአብሔር ምስጋና

በሰማይ ለእግዚአብሔር ምስጋና
በምድርም ለሰው ልጅ ሰላም/2/
ተወልዷልና መድኃኔአለም /2/

የሞቱ ዘመን ማብቂያው ሲቃረብ
መቋጫው ሲደርስ አስፈሪው ወጀብ
ከድንግል ማርያም ጌታ ተወለደ
የጠብ ግድግዳ በክንዱ ተናደ

ሰላም ታውጇል ነፃነት ህይወት
ተወልዷና የዓለም መድኃኒት
የሰማይ ዜማ ተሰማ በምድር
በአፈ መላእክት ለእግዚአብሔር

ቃሉን አልረሳም የምህረት ኪዳኑን
የማዳኑን ቀን ከአፉ የወጣውን
መሃላው ጽኑ ፀፀት የሌለበት
ላዳነን አምላክ እልል እንበልለት

አጽናኙን ድምጹን ሰማን በኤፍራታ
በዱር አየነው የፍጥረትን ጌታ
በሚቆምበት በሚያድርበት ስፍራ
እንሰግዳለን በጽዮን ተራራ

ክብረ ቅዱሳን

ክብረ ቅዱሳን ይዕቲ ክብረ ቅዱሳን
ሙዳየ መና ግሩም (2) ሙዳየ መና

የቅዱሳኑ ክብር ነሽና
እንሰጥሻለን ቅኔ ምስጋና
የወለድሽልን የሕይወት መና
ዝናብ ያለብሽ ታናሽ ደመና

ትህትና ልብስሽ ፍቅር ውበትሽ
ጽንስ ያዘልላል ሰላምታ ድምጽሽ
እሳትን ወልደሽ እሳት ታቅፈሻል
ሳንዘምርልሽ መቼ ይመሻል

ሰአሊ ለነ ሰላም ለኪ
ተማጎጸነ በኪዳንኪ
ንዒ ርግብየ ምስለ ወልድኪ
ሰማይ ወምድር ይዌድሱኪ

የፀሐይ መውጫ ምሥራቅ ሆነሽ
ታላቁን ብርሃን አየንብሽ
አትጨልምም ሕይወታችን
ልጅሽ ስላለ ፀሐያችን

በቤተ መቅደስህ

በቤተ መቅደስህ ያሳደከኝ
ለአፌ ጥበብን ያስተማርከኝ
የልጅነቴ አምላክ ወዴት አለ
በዚህ ዓለም ሃሳብ ክንዴ ዛለ

የአሸዋ ላይ ሕንፃ ሆኗል ቤቱ
ያረገርጋል መሠረቱ
ጠላት ሰልጥኖብኝ ደክሜአለሁ
ዛሬ ብቻዬን ቀርቻለሁ

አባካኝ ሆኛለሁ አመፀኛ
ለዚህ ዓለም ኃጢአት የማልተኛ
ነፍሴ ተንገላታች በመከራ
ማን ያገናኛናት ካንተ ጋራ

ሰላሜ አንተ ነህ አንተ ትዝታዬ
ጽፌ ያኖርኩህ በእንባዬ
ዓለም ወስዳኛለች በዘፈኗ
እባክህ ስራኝ እንደገና

አመጸኞች ሁሉ ቤትህ ገቡ
ምህረት ፍቅርህን እያሰቡ
እጅህን ዘርግተህ አቀፍካቸው
በአንተ ቀለጠ ልቡናቸው

በንጹህ ደሙ

በንጹህ ደሙ ያዳነን -- ከወደቅንበት ያነሳን (2)
ብዙ ነው የእርሱ ውለታ -- እንዘምራለን ለጌታ
ቀና ብለናል በክብር
አንገቱን ደፍቶ በፍቅር
ስለኛ ብዙ ሆኖልን
የብርሃን አክሊል ደፋልን
የዓለም መድኃኒት ጌታ ነው --
ጠላታችንን ያሰረው
እርቃኑን ሆኖ ሸለመን
እየደከመ አቆመን
እርሱ በመስቀል ሲሞት
እኛ ተጻፍን በሕይወት
የዓለም መድኃኒት ጌታ ነው --
ጠላታችንን ያሰረው
እስከ ሺህ ትውልድ ይምራል
ፍቅር ነውና ይራራል
አይዝልም የእርሱ ትከሻው
መጨረሻ ነው መድረሻው
የዓለም መድኃኒት ጌታ ነው --
ጠላታችንን ያሰረው
በደም ያጌጠ ልብስ አለው
ከአማልክት ማንም አይመስለው
ትውልዱ ማዳኑን ይስማ
ነግሷል በጽዮን ከተማ
የዓለም መድኃኒት ጌታ ነው -- ጠላታችንን ያሰረው

በዕፀ መስቀል

በዕፀ መስቀል ላይ በዚያ አደባባይ
አምላክ ሆይ ጌታ ሆይ ተንገላታህ ወይ
አምላክ ሆይ ጌታ ሆይ መከራ አየህ ወይ
መስቀል አስይዘው ኪርያላይሶን
ወደ ጎልጎታ "
ሲገርፉህ ሲያዳፉህ "
ስትንገላታ "
ያንን አቀበት ኪርያላይሶ
ያንን ዳገት "
ጀርባህ ተገርፎ "
ስትቃትት "
አንተን እያዩ ኪርያላይሶን
ሴቶች ሲያለቅሱ "
እናቶች ቀርበው "
ላብክን ዳበሱ "
መስቀል አስይዘው ኪርያላይሶን
እንዲያ ሲያዳፉህ "
የቀሬናው ሰው "
ስምዖን አገዘህ "

በዋጋ ገዝተኸኛልና

በዋጋ ገዝተኸኛልና
ስለኔ ደም ከፍለሃልና
ልሳኔ ያውጃል ክብርህን
አልረሳም ጌታ ውለታህን

ሕይወት ሰላሜን ትቼ የማይታይ አይቼ
ላንተ ብሰጥ ጀርባዬን ልተዋወቅ ጠላቴን
የጠበቀኝ ውጊያ ነው የተረፈኝ ፀፀት ነው
የሻረልኝ ቁስለቴን ተሰቅለህ ነው አባቴ

እንዛለሁ በምናብ ወደሰላሜ ወደብ
እጀን በአፌ እጭናለሁ ዛሬም እፁብ እላለሁ
ለክብርህ መሠለፌ በለመለሙ ማረፌ
ዋጋ ከፍለህ ነው ጌታ ያኖርከኝ በፀጥታ

ከውሃና ከመንፈስ ተወልጀ ከመቅደስ
ልጅህ ሆንኩኝ ዳግመኛ የመስቀልህ ሙርከኛ
ባንተ ሰለመዳኔ ምስክርህ ነኝ እኔ
ላይታጠፍ ምላሴ እቀናለሁ በነፍሴ

በዘመናት የሸመገለ

በዘመናት የሸመገለ
ክብርን ሁሉ የጠቀለለ
እንደ ጌታ እረ ማን አለ
እንደ እግዚአብሔር እረ ማን አለ

ጥሎብኛል መጮናጸፊያ
ለይቶኛል ከሥጋ ጥድፊያ
በሰው ሚዛን ክብር የማይለካ
እውነተኛ ጌታ ነው ለካ

ቀን ዘመናት ሁሉ ሲያረጁ
አዲሶቹ ዘምነው ሲጃጁ
ጌታ አዲስ ነው ሁሌ ማለዳ
ፍቅር ያዘንባል ከልብ ጓዳ

መካኒቱን በልጅ ባረከ
ሀይለኞቹን አንበረከከ
ለምሲኪኖች ስለሚራራ
በኢየሱስ ልባችን ኮራ

ደመና ነው መንኮራኩሩ
ነበልባል ነው ዙፋን መንበሩ
በሰው ሚዛን አይከለስም
በማንም ሞት አይወቀስም

በዘባነ ኪሩብ

በዘባነ ኪሩብ ለሚቀመጠው
በእሳት ድንጋዮች ቅጥሩን ላጠረው
ዘምሩ ለእግዚአብሔር ለጌታ ዘምሩ
የተከበረ ነው በሰማይ በምድሩ (2)

ኢሳይያስ ሲያየው እጅግ አፈረ
የተፈራ ነው የተከበረ
የሰማይ ደጆች ተንቀጠቀጡ
ለቅዱስ ስሙ ክብርን ሊሰጡ

ያልተቀደሰ ለምፅ ያነደደው
እንዴት ይችላል ሊያመሰግነው
በል ፍቀድልኝ ፍቅር ነህና
ልግባ መቅደስህ ላቅርብ ምስጋና

ዙፋንህ ታየኝ ትምክህቴ ሆይ
ስትመሰገን በሰማይ ላይ
ሲያመሰግንህ የተደሰተ
ባይተዋር አልሁን አልውጣ ካንተ

ቅኔ የሞላበት ያንን ሰገነት
ልቀላቀለው ተመኘሁ በእውነት
ልዘምርልህ ባይገባኝም
ዝም የሚል ልሳን አልሰጠኸኝም

በድል ቆመናል

በድል ቆመናል በአሸናፊነት
ስምህን ይዘን ወጣን ሰገነት
ተሠባበረ አሳዳጃችን
ከበርን በአምላካችን

በገና አንስተን ፊቱ ቆመናል
የክብሩ ዜማ በአፋችን ሞልቷል
እልፍ አሳልፈን ታጥቀን በስሙ
ስንቀኝለት ሰማን ዓለሙ

ካሳዳችን እልፍ ሠራዊት
አለን በጌታ የማይዝል ጉልበት
የእግዚአብሔር ጸጋ ከኛጋር ያለው
ታሪክ ሲለውጥ ለካ እንደዚህ ነው

ከበኩራችው ጋር ግብጽን የመታ
የፀናው ክንዱ አይዝልም ላፍታ
ማን ይችለዋል ይህን ተግዳሮት
አትፍራ ሳያል በቂ ነው ዳዊት

ንጹህ የሆነ ነውር የሌለበት
በደሙ አገኘን ታላቅ ነፃነት
ሰይጣን ራደ አንገቱን ደፋ
ተዋጊው ጌታ ሲሆነን ተስፋ

ፈርዖን በከንቱ ደከመ ኃይሉ
የተከተለን ግብፆች የታሉ
በድል ያቆመን ሁሉን ሲከወን
ከዚህ የሚበልጥ ገና እናያለን

በገና አንስተን

በገና አንስተን መሰንቆን
እናመስግነው ስምህን
እንደ አምላካችን ማንም የለም
ይክበር ይመስገን ለዘላለም (2)

ዓለም ሞኝነት ይመስለዋል
ለአንተ መንበርከክ ይከብደዋል
ፍቅርህን ቀምሰን ዝም አንልም
እንዘምራለን ለዘላለም (2)

ሞኝነት ለኔ መች ሆነና
ፊትህ ያቆመኝ ለምስጋና
እንድቀኝልህ ግድ የሚለኝ
ፍቅርህ ብቻ ነው የማረከኝ

ፈውስን ስትሰጠን ስትባርከን
ፍቅርህን ልከህ ስትጎበኘን
ጉልበት ይጸናል በአንተ ጸጋ
ማነው የሚከፍልህ የአንተን ጸጋ

ስንዘምርልህ የሚስቁ
ብዙ ሜልኮሎች ዛሬም አሉ
የእኛ የሆነ ምንም የለም
አምላክ ስላንተ ዝም አንልም

በጎ ስጦታዬ

በጎ ስጦታዬ ፍጹም በረከቱ
ከአጠገቤ አትራቂ ድንግል እመቤቱ

አልታክትም እኔ ሁሌ ጠራሻለሁ
የኃዘኔ መርሻ አንቺን አግኝቻለሁ
እንዴት አልፈው ነበር ያን ሁሉ መከራ
ከጎኔ ባትቆሚ ድንግል ከኔ ጋራ

ቢታጠር መንገዴ ቅጥር ቢበዘበት
ይበረታል እግሬ አንቺ ካለሸበት
የእሳቱ ግርማ ቢበዛ ፉጨቱ
ልቤን አሳረፍኩት ባንቺ ባዛኙቱ

የቀደመው እባብ አውሬው አያድነኝ
ፍጻሜዬ እንዲያምር ድንግል ለምኝልኝ
የቆምኩ ሲመስለኝ ተንገዳግጃለሁ
የዛሬውን እንጂ የነገን መች አየሁ

ዞሬ ተመልሼ አየሁት ደግሜ
ምንም አላተረፍኩ በዚህች ዓለም ዕድሜ
ልጅሽን አምኜ አንቺን እይዛለሁ
የላላው ጉልበቴን አበረታዋለሁ

ጎዶሎዬ ሞልቷል ቤቴ ሰላም ለብሷል
የጭንቅ አማላጂን አንቺን ጠግቷልት
ጠላቴ ቢጽፍም የዕዳዬን ጦማር
አልሞት በጭራሽ ሳለሁ ካንቺ ጋር

ባለውለታዬ

ባለውለታዬ (2)
ከአመድ ያነሳኸኝ ከትቢያ ተጥዬ
ተመስገን ጌታዬ

በሩን ቢዘጋብኝ ስምያን ጨክኖ
ዝቅ አድርጎ ቢያየኝ ከአይሁድ ጋር ሆኖ
እንድቀርብ ወደሱ አዘዘ ጌታዬ
እግሩን አጥበዋለሁ ወድቄ በዕንባዬ

የቀራጭ አለቃ ቢሆንም ሥራዬ
እንድወርድ ከዛፉ አዘዘ ጌታዬ
ማዕረጌን መሸከም እስኪያቅተኝ ድረስ
ቤቱ ተባረክ በኢየሱስ ክርስቶስ

ድንጋይ የጨበጡ ፈራጆች ከበውኝ
ነውሬን ዘርዝረው ጌታ ፊት አቆሙኝ
ፈረደችባቸው ኃጢአም በእነርሱ
በሰላም ሂጅ ብሎ ምሮ ኖል ንጉሡ

የማምነውን አምላክ አውቀዋለሁ እኔ
በሰራልኝ ሥራ በዕድሜ በዘመኔ
ፍቅሩን ተሸክሚል የልቤ ትከሻ
ልለየው አልችልም እስከመጨረሻ

ባለፀጋ እመቤት

ባለፀጋ እመቤት ባለፀጋ እናት
አፍሰናል ከደጅሽ ብዙ በረከት
ወጀቡን ቀዝፈናል ብለን ማርያም
እንዘምራለን እስከዘለዓለም

ሰው በሌለበት ከተማ ሞት በከበበው ጨለማ
ሞገስ ገንዘቤ ዘመዴ በምልጃሽ ቀንቷል መንገዴ
ፋና ሆነሽን መብራቴ በክብርሽ ደምቆልኝ ቤቴ
ሐሴት አረኩኝ ደስታ ያዘነው ገዜ ተፈታ

እንደ እኔ ኃጢአት በደል ይገባኝ ነበር መስቀል
ጽኑ ኪዳኗ ጋረደኝ ዕንባ ፀሎቷ ታደገኝ
እስኪ ልናገር ስራዋን የምህረት እናት መሆኗን
ጽዮን እጆቿን ዘርግታ አስታርቃኛለች ከጌታ

የክብር ሰንደቅ አርማዬ ወደ መቅደሱ መግቢያዬ
አንቺን ይገፍአለሁ ጠበቃ የሞቴ ታሪክ አበቃ
እልል እላለሁ ከልቤ ለቅሶዬ ሰምሮ ሃሳቤ
ድንግል ፍቅር ናት ሰላም ለክብሯ ይስገድ ዓለም

የእልፍኜ ማማር ውበቴ ትሩፋቴ ነሽ ሙላቴ
ስምሽ መቀነት ሁኖኛል የዛለው ክንዴ በርትቷል
ባማረው ቤትሽ አድጌ በልጅሽ ፀጋ በልፅጌ
በእናትነትሽ በረከት ይኸው ቁሚያለሁ በሕይወት

በአንተ ነው ጌታ

በአንተ ነው ጌታ እዚህ መድረሴ
ጸጋህ በዝቶልኝ ሆነህ ሞገሴ
ፍቅርህ ታትሚል በስንክሳሬ
አንድምታዬ ነህ ለዛሬው ክብሬ

ሐብታም ነህ ስትለኝ ከዓለም ድሆች መርጠህ
መች እንደሌሎቹ ደምግባቴን አየህ
የዓለም ብልጽግና በሰማዩ ሚዛን ድህነት ነው ለካ
በሚታይ አይደለም ዐይን በሚሞላ አንተ ስትለካ

በትሕሻህ ሆኜ በእንባዬ አጥብሃለሁ
እንደተሸከምከኝ መቼ እዘነጋለሁ
አደረሰኝ እንጂ ደረስኩኝ አልልም እኔ አፌን ሞልቼ
በዘመኔ ሁሉ እጆችህ ሲሰሩ ስላየሁ በዐይኖቼ

ጥልቅ ነው ለሰዎች የባርያህ ከፍታ
ምስጢር ነው ያላንተ በሥጋ አይፈታ
እንዲህ ሠራ ብሎ የሠራኝን ረስቶ ሰው በእኔ ይደነቃል
ይህ ሁሉ ግን ከአንተ ያንተና ስላንተ ጌታ በአንተ ሆኗል

ብርሃን የለበሰ

ብርሃን የለበሰ በሰማያት ያለ (2)
እንደ እግዚአብሔር ከቶ ማንም የለ (2)
ውሆችን በእፍኙ የሰፈረ
ተራሮችን በሚዛን የመዘነ
ሰማይን በስንዝር የሚለካ
ዘመንን በዘመን የሚተካ (2)
ከዓለም በፊት የነበረ
ፍጥረታትን ሁሉ የፈጠረ
በምድር ክበብ የሚቀመጥ
ሁሉ ሲለወጥ የማይለወጥ (2)
ከሁሉ ሁሉ ሁሉንም የሚያውቅ
ፈታሔ በጽድቅ ሥራው ረቂቅ
ዓለምን በመላ ፈጥሮ የሚገዛ
መአቱ የራቀ ምህረቱ የበዛ (2)
ዙፋኑ የፀና በሰማይ
ሁሉ የሚቻለው አዶናይ
ለዘመኑ ፍጻሜ የሌለው
አልፋ ኦሜጋ አምላክ ነው (2)

ተመስገን ተመስገን

ተመስገን (3) ጌታዬ (3)

ባይሣካልኝ ባይሞላም ጓዳዬ

ባንተ ተሸፍኗል ጉድፍ ገበናዬ

ኑሮዬ ቢሆንም እጅጉን መራራ

ሕይወት ለኔ ከብዳ ብትሆንም ግራ

ሁሉን ነገር አንተ ለበጐ አድርገሃል

አምላክ ለስጦታህ ምን ይከፈልሃል

ያሰበኩት ባይሞላ ባይሣካልኝም

ተመስገን እላላሁ አልጐደለብኝም

አላፍርም ጠርቼህ አምናለሁ ጌታዬ

ሁሉ ባንተ ሆኗል ይድረስ ምስጋናዬ

ደመና ባይታይ ንፋስም ባይነፍስ

ኤልሻዳይ እግዚአብሔር ስሙ ይወደስ

የጓዳዬን ምስጢር የሚያውቀው እርሱ ነው

በጐደለልኝ ሁሉ የሚሞላው አለው

ተራሮችን ሁሉ

ተራሮችን ሁሉ ያንቀጠቀጥንበት የተፈራ ስም ነው

አልፋና ኦሜጋ ዘላለም የሚኖር ዛሬም ገናና ነው

ኢየሱስ ክርስቶስ/2/ ስሙ ምግባችን ነው

ከሰማይ የመጣ እንጀራ ነው እርሱ

ብዙ በሽተኞች ፈውሷል ቀሚሱ

አንጠረጥረውም ዛሬም ገናና ነው

ሞትን አሸንፎ በአባቱ ቀኝ ያለው

ያጽናናል መንፈሴ እየደጋገመ

ልቤ ለምስጋና ለዝማሬ ቆመ

ብር እና ወርቅ እንኳን ባያኖረኝም ቤቱ

ሃብታም ነኝ በፀጋ አለልኝ አባቱ

ከማር ይጣፍጣል ስሙ ለአንደበቱ

ከእርሱ ጋራ ካለሁ አይደክምም ጉልበቱ

የሰው ፍቅር ሆኖ መውደድ ያበዛልኝ

እርሱን አውቃለሁ ሌላ ማንም የለኝ

አምነነው ወጥተናል እናሸንፋለን

በምስጋና ገና ምድርን እንከድናለን

ቢዋጋንም ጠላት መች ይቋቋመናል

የማይሞተውን ስም ከፍ አርገን ይዘናል

ተናገር ባርያህ ይሰማል

ተናገር ባርያህ ይሰማል
ሳሙኤል በለኝ ድምጽህ ይገርማል
ታናሽ ነኝ የማልበረታ
እስኪ ተናገር ላድምጥህ ጌታ /2/

በሚያስፈራው በመቅደስህ
ልኑር ጌታ በመንፈስህ
ደካማ ነኝ ብላቴና
ባንተ ልቁም ባንተ ልፅና
አያሳድደኝ ጠላት አልውጣ ካንተ
ከእቅፍህ ልግባ ሳበኝ እልፍኙን ከፍተህ

ፈቅደህ ወደህ ጠርተኸኛል
ቸርነትህ አቁሞኛል
ፍቅርህ አስሮ ያኖረኝ
ብትወደኝ ነው ብትምረኝ
እንዴት አድርጌ ልቻል ይህንን ሸክም
የታሪክ ጠባሳ ነው እስከ ዘለዓለም

በድንኳኑ በማደሪያህ
ሳውጅ ልኑር ያንተን ስራ
ቅድስናህ ይብዛልኝ
በመንግስትህ አስበኝ
ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ለስምህ ልቅና
የእስራኤል ቅዱስ አንተ ታላቅ ነህና

ትህትና ልብስሽ ሆኗል

ትህትና ልብስሽ ሆኗል
ማህፀንሽ መቅደስ ሆኗል/2/
ያከበረሽ ኤልሻዳይ ነው
መመረጥሽ ከሰማይ ነው/2/

ተባርከሻል በባራኪው ቃልን ወልደሽ እንድታቅፊው
ድንቅ ነገር ሆኖልሻል እናት ድንግል ተብለሻል
አቤት ፍቅር አቤት ፅናት ስለልጅሽ ወጣሽ ስደት
አብነቱ ሁኝኝና በኢየሱስ እኔም ልፅና

ማጎንበስ ይልመድ ራሴ ከፍ እንድትል ምስኪን ነፍሴ
ትህትና ካንቺ ልማር እንድስማማ ከቃሉ ጋር
መስቀል አለኝ ምሸከመው ከወደድኩኝ ልከተለው
ክርስትና ትርጓሜው ተሸንፎ ማሸነፍ ነው

ያመንሽውን ግብርሽ ሰብኳል ብፅዕናሽ ተተርኳል
ቤቱልሄም እንደነበርሽ ቀራኒዮም መስቀል ስር ነሽ
ልብሽ ታስሮል በኃያል ፍቅሩ እንባ አይኖችሽ እየዘሩ
ልጁ እያልሽው ተሰቀለ ሞቶ ሞትን ተበቀለ

ትላንትና ካንተ ጋር

ትላንትና ካንተ ጋር ዛሬ ደግሞ ከሌላ
ሰልችቶኛል አባቴ ሆይ ሁሌ መዜድ/መንገዘ ወደኋላ/2/
ሰዶምን አልተውኩም ወደኋላ አየኋት ደግሜ
ምንኛ ከንቱ ነኝ ሳልለወጥ ባለሁበት ቆሜ
ይነዳል ከተማው ይቃጠላል በቁጣ እሳት
እጄን ይዘህ አውጣኝ ዞአር ሳልደርስ ጌታዬ እንዳልሞት
ጨው አልጫ ቢሆን በምን ይጣፍጣል
አጣፍጠኝ በቃልህ ከእጅህ እንዳልጣል
ደማስን ሆኛለሁ ተሰሎንቄ አስራ ያስቀረችኝ
ስሸሽህ አግኝታ ከባህሩ ከጥልቁ የጣለችኝ
ወፎች ለቅመውታል ቅዱስ ቃልህ በውስጤ የታለ
አዘገየኝ እንጂ ያጠላቴ እየሸነገለ
መልሰኝ ልመለስ በለቅሶ በእንባ
አሳ እንበሪው ይትፋኝ ወደ ቤትህ ልግባ
አለቀ ገንዘቤ የሰጠኸኝ አፍስህ በችሮታህ
ራሴን አገኘሁት አመሻሽ ላይ በተናቀው ቦታ
ጨልሟል ዙሪያዬ የምይዘውን ነገር አጥቻለሁ
የድሮ አይደለሁም የኔ ጌታ ዛሬ ደክሚያለሁ
መንገድ ለጠፋው ሰው ክንድህ ወዴት አለ
ምንድነው ምሪትህ እራሱን ለጣለ
ማለዳ ስነቃ ዘምሬልህ ሲመሽ ግን ሌላ ነኝ
ቃልህ ያልለወጠኝ ያልቀየረኝ ጌታዬ እኔ ማነኝ
አይወስንም ልቤ ያመነታል ይሸሻል አጥብቆ
ዘላለም ላይደላው እስከመቼ ካንተ ተደብቆ
እንድወስን እርዳኝ ይበርታ ጉልበቴ
ጠላት ጭኑን ይጽፉ እቀፈኝ አባቴ

ትናንትናም ቅዱስ

ትናትናም ቅዱስ ዛሬም ቅዱስ ነህ
በመምሬ አድባር ላይ ጌታዬ ያየሁህ
እጅን አነሣለሁ አትለፈኝ ብዬ
የአባቶቼ አምላክ ግባ ከጎጆዬ
ሰባራው ልቤ ሸሸ እያነከሰ
ጌታዬ ጥራው ሰምቶ ከተመለሰ
በዚያ ሞት አለ በዚያ ብዙ መከራ
እንዴት ይሞታል አምኖ አንተን የጠራ
የተጣለ ሰው ወጥቶ የተሰደደ
ምን ተስፋ አለው ባንተ ካልተወደደ
አባብለኝና ልምጣ ልግባ ከእቅፍህ
አስረህ አኑረኝ ሁሌ ከማስነቅፍህ
የክረምቱ ዶፍ ወንዙ ውሃው ሳይሞላ
ልውጣ ልሻገር ልሩጥ ካንተ በኋላ
ካራን ምኔ ናት አንተ ካልተቀበልካት
ምድሪቱን ልውረስ ልሂድ ሕይወቴን ባርካት
ድንኳኔን ልትከል ቤቴን መንገድ ላይ ልሥራ
እንግዳ አለብኝ ልቡ አንተን ሚፈራ
ጠላት አውርቷል ክፉ የአመፃ ወሬ
ወዳጅ ሁነኝ ግባ ይከፈት በሬ

ትውልድ የማይዘነጋው

ትውልድ የማይዘነጋው ትውልድ የሚዘክረው
ሕያው ነው በዘመናት የጌታችን ጌትነት
ጥንት የለው ለዘመኑ
ልክ የለው ለመጠኑ
የሰው ሥርዓት አይደርሰው
እርሱማ ያው እርሱ ነው
ሕያው ነው ይህ ምስጋና
ይነግሣል ጌታ ገና
ይህንን የደም ሐውልት
ሚነቅለው ማነው ታግሎት
በትውልዱ ልቦና
ፍቅሩ ተተክሏልና
ሕያው ነው ይህ ምስጋና
ይነግሣል ጌታ ገና
አይሁድ አልሸፈኑትም
ጸሐፍት አልከደኑትም
ፍጥረት ታጥቧል በደሙ
አልተነቀለም ስሙ
ሕያው ነው ይህ ምስጋና ይነግሣል ጌታ ገና

ቸርነትህ ነው

ቸርነትህ ነው ያደረሰኝ እስከዛሬ
ቸርነትህ ነው የጠበቀኝ እስከዛሬ
ላመስግንህ የኔ ጌታ በዝማሬ
መክሊቴን ቀብሬ ባሳዝንህ
መብራቴንም ይገፍ ባልጠብቅህ
በታላቅ ይቅርታህ እንዳትረሳኝ
በፍቅርህ ጎብኝተህ ከሞት አውጣኝ
ከቤትህ ርቄ መች ጠገብኩኝ
በረሃብ በርሃት ተቸገርኩኝ
አምናለሁ አምላኬ እንድትምረኝ
ለይቅርታህ መጣሁ ተቀበለኝ
አንዳች እንደሌለኝ አውቀዋለሁ
በአንተ ቸርነት ግን እመካለሁ
የከበደው ሸክሜ ይቀለኛል
ይቅርታህ ለባሪያህ ይደርሰኛል
በመቅደስህ ቆሜ ለመዘመር
ስራህን ለትውልድ ለመመስከር
እኔ ማነኝ ብዬ አስባለሁ
አምላክ ቸርነትህን አደንቃለሁ
በሰው እጅ መመካት አቁሜአለሁ
ረዳቴ አንተ ነህ አውቄአለሁ
አንተ ከጠበቅከኝ በሕይወቴ
ቅጥሬ አይደፈርም መድኃኒቴ
የኔን ሥራ ተወው ተግባሬን
የመስቀሉን ነገር መርሳቴን
አዚሜን አንስተህ አንተን ልይህ
ኢየሱስ ክርስቶስ አምላኬ ነህ

ናታኒም ነኝ

ናታኒም ነኝ በአገልግሎቱ
አይከፋኝም ታናሽነቱ
እጠርጋለሁ ደጅህን ጌታ
ዝቅ ብዬ ለአንተ ውለታ

ከነገደ ሌዊ ባልሆን ባልሾምም እንደ አሮን
የዜማ እቃ ባልይዝ በገና ላመስግንህ በትህትና
ከደጅ ሆኜ ካንተ በር ተስፋ አድርጌህ ስዘምር
ቆጥረህልኝ እንደዋጋ አከበርከኝ ባንተ ፀጋ

ከእረኝነት ከታናሽ ስፍራ ለንግስና ምንም ብጠራ
ከቀንዲሉ ቀድሟል ሀሳቤ እንድቀኝልህ ተነጥፎ ልቤ

ሳይከብድብኝ የዓለም ዝና ተንበርክኬ ልስጥህ ምስጋና
ምክንያት አለኝ ለማዘንበሌ ናታኒም ነኝ ይህች ናት ቃሌ

እንኳን ልቆም በፍታን ለብሼ አፍርሃለሁ እኔ አጎንብሼ
የትምክህት ካባዬን ጥዬ ከመቅደስህ ልግባ ጌታዬ

አሁን ተረጋጋ

አሁን ተረጋጋ ተዕናና ልቤ
ከጎኔ ስትቆም ከአጠገቤ /2/
ውዳሴ ምስጋና ስራዬ ሁኗል
የአባትነት ፍቅርህ ውስጤ ታትሟል /2/

አንተ በቃ ስትል ሁለም ያበቃል
የመከራው ጅረት ምንጩ ይደርቃል
የምታስብልኝ አንተ ስላለኸኝ
መጨነቂ ቀርቶ ሰላምህ ከበበኝ

ነፍሴን ለማፅናናት ብለፋም ብደክምም
በኔ ጉልበት ብርታት አልተደሰትኩኝም
ከነግሳንግሷ አለምን ትቻለሁ
የሰላሜን ሚስጢር አንተን አግኝቻለሁ

አብረኸኝ ስትወጣ ይሞላል መረቡ
የተነዋወጠው ፀጥ ይላል ወጀቡ
የደስታ ምንጩ ነህ የሰላም አለቃ
ታሪኬን ለወጥከው ጭንቀቴም አበቃ

ከመቃብር በላይ ማኖር ትችላለህ
ጨለማውን ገፈህ ብርሃን ታለብሳለህ
የተመጻደቁ ያመፁብህ ጠፉ
የተዋጊው ጌታ ያንተ ሆኖ ሰልፉ

አለ ለእኔ የተሻለ ነገር

አለ ለእኔ የተሻለ ነገር (2)
ዛሬ ባዘን ለጊዜው ብቸገር
አለ ለእኔ የተሻለ ነገር
በእጇ የጨበጥኩት በድንገት ቢበተን
ዙሪያዬን ቢከበኝ ያላሰብኩት ኃዘን
እንባዬ በደስታ መቀየሩ አይቀርም
እተማመናለሁ በጌታዬ አላፍርም
ሀብቴን ልጇን ባጣ እርሱ እንደወደደ
የኢዮብ መከራ በእኔ ከወረደ
እራቁቴን መጣሁ እንዲሁ እሄዳለሁ
ከዚህ የላቀውን ከርሱ እጠብቃለሁ
መከራው ቢከብደኝ ከዙፋን ወርጄ
ከርስቴ ብሰደድ በአቤሰሎም ልጄ
ቀኑ እስከሚነጋ አልፈራም ጨለማ
ዳግም እለብሳለሁ የጽዮንን ግርማ
አሳዳጇ ቢያይል ጉልበቴ ቢጸና
ተግዳሮቱ በዝቶ ወደኔ ቢያቀና
የከበረው ድንጋይ አለ በወንጭፉ
እቋቋመዋለው እርሱን ተደግፌ
በናባው ተራራ ቢሆን መቃብሬ
ከነዓን ባልገባ ከሕዝቡ ጋር አብሬ
አለኝ በሰማይ ቤት እጅግ የከበረች
በጆሮ ያልተሰማች በዓይንም ያልታየች

አለልኝ አባቴ

አለልኝ አባቴ አለልኝ ጌታዬ
ዘመን የማይሽረው ባለውለታዬ
ዛሬ ሌላ ሆኖ ቢከፋም ዘመኑ
አልተለየም ከኔ ጌታ በማዳኑ
ምድርና ሰማዩ ቢጋጠም በላዬ
ሕይወት ብትምረኝ በዝቶ መከራዬ
አባት አለኝ እኔስ በሰማይ አገሩ
አይዞሽ ልጄ የሚለኝ የሚያጽናናኝ በፍቅሩ
የሚሟገትልኝ ባይቆምም ከጎኔ
ለሞት ቢሰጠኝም ስህተቴን ማመኔ
የኔ ተቆርቋሪ የኔ ፈራጅ ዳኛ
እንባዬን ያብሳል አልሆንም ብቸኛ
አልጋዬን አንጥፎ የሚያስታምመኝ
ስወጣ ስገባ በፍቅር የሚያየኝ
ጎኔን ለማሳረፍ ባርኬው ስተኛ
እርሱ እንቅልፍ የለውም የነፍሴ እረኛ
ገና ሳልናገር የልቤን መሻት
ፈጥኖ ያደርግልኛል ሊሞላኝ በሐሴት
እመካለሁ ዛሬም እተማመናለሁ
ዘለዓለም በክብር ከእርሱ ጋር እኖራለሁ

አለማመኔን እርዳው

አለማመኔን እርዳው ጌታዬ (2)

አንተ ነህና መሸሸጊያዬ

አለማመኔን እርዳው ጌታዬ

ፍሬ ያላዘልኩኝ ብሆንም ጎስቆላ

ነፍሴ አብራህ ትኑር በማደሪያህ ጥላ

አታውጣኝ ከቤት ባጣም ቅድስና

ይችን ዓመት ተወኝ ጉልበቴ እስኪፀና

ያልፀናው ሕይወቴ ቢያስቸግርህ ላልቶ

እስኪቆም ታገሰኝ ጉልበቴ በርትቶ

እንደ ቃልህ ባልኖር ደስም ባላሰኝህ

ዛሬም ከእኔ ጋር ሁን በፀናው ኪዳንህ

ለምዒ እጅግ በዝቶ ከሰዎች ብገለል

ልትዳስሰኝ ፍጠን ምህረትን ልታደል

ደባልቀኝ ከመንጋው ከበረታው ወገን

አዘንብል ወደኔ በፍቅርህ ልሸፈን

መዓዛዬን ለውጥ ጠረኔን ቀይረው

እንደ ናርዶስ ሽቶ የከበረ አድርገው

ቅረበኝ በፍቅርህ በደሌን ትተኸው

ሳበኝ በምሕረትህ ቤቱን ደስ አሰኘው

አለን አልጠፋንም

አለን አልጠፋንም አልወደቅንም እኛ

በቀንም በሌሊት ልዑል ስላልተኛ

ነገም እንኖራለን ስሙን ተደግፈን

ዘመን ይቆጥራል ፊቱ ተሠልፈን

ብንኖርም የርሱ ነን ብንሞትም የጌታ

አዲስ ነገር የለም ትጥቅን የሚያስፈታ

እንደ አይኑ ብሌን ተግቶ ይጠብቀናል

ሁሉን በርሱ ችለን ቀሎልናል

ይጠፋሉ ሲሉን በሀሠት ትንቢታቸው

በእግዚአብሔር አሠራር ቂም ቋጥሮ ልባቸው

አበዛን አሠፋን በመልካም ፈቃዱ

አይመረመርም የጌታ መንገዱ

ሞቶ የገደል ቆስሎ የፈወሠ

በልባችን መሃል ፍቅሩን የነቀሰ

አለቱን ሠንጥቀን አልፈን ያን ጨለማ

በድል እንኖራለን በበጉ ከተማ

አንጠራጠርም የማዳኑን ጉልበት

ለድል እንወጣለን ስሙን አምነንበት

ጠላት ጉድጓድ ገብቶ አፈር እስኪጫነው

ጊዜ አይፈጅበትም ኢየሱስ ጌታ ነው

አልፈራም

አልፈራም ጌታዬ ሞቶልኛል
አልሰጋም ክርስቶስ ሞቶልኛል
የማይደፈር የደም ነው ቅጥሬ
የማይሞት ቅኔ አለው ከንፈሬ

ጭንቀቱ ይሄው ተሰምቶት
ከቤገፍኝ ይኸው እስከሞት
በመስቀል ካለፈ ለኔ
ከንግዲህ ስጋት ለምኔ

በክንዱ በስሙ ኩራት
ታምኜ ወጣሁ ሰገነት
ካጸናኝ ማንም አይነቅለኝ
ኢየሱስ በአለቱ ተክሎኝ

ቢከቡኝ ድንጋይ የያዙ
ከሳሾቼ ቢበዙ
ትምክህቴ ፅናቴ እሱ ነው
አባቴ በሰማይ ያለ ነው

ዜማ እንጂ ዝምታ የለም
ከበደል ላጠበኝ በደም
ላይተኛ ከንፈር ልሳኔ
ዘላለም ቀንቷል ለቅኔ

አምላካችን ገናና ነው

አምላካችን ገናና ነው
ፍቅሩ ድንበር ወሰን የለው
አይጥለንም ለዘላለም አይተወንም ለዘላለም
ይወደናል መድኃኒዓለም (2)

ያንን ሁሉ ዋጋ ከፍሎ
ሸክማችንን አንከባሎ
እንደዘበት እንደዋዛ
አይጥለንም የእኛ ቤዛ (2)

ጎኑን ወግተው ደሙ ፈሶ
በግርፋት ጀርባው ታርሶ
መዳፉ ላይ ተቀርፀናል
እንዴት ብሎ ይረሳናል (2)

መከራችን ቢበረታ
ጥያቄያችን ባይፈታ
ለጊዜው ነው ዝምታው
በማዳኑ ታማኝ ነው (2)

የዳዊት ክብር የሳያል
የጌዴዎን የዳንኤል
ስንቱ በቃ ለክብር
እያገዘው እግዚአብሔር (2)

አቤቱ ላንተ

አቤቱ ላንተ ለስምህ አለኝ ምስጋና /2/

እንዳንተ ያለ እግዚአብሔር ማንስ አለና

አቤቱ ማዳንህ በኛ ላይ ተገልጧል

ግዙፉም ተራራ በፊታችን ቀልጧል

በግንብ የተሰሩ ብረት የለበሱ

የአሕዛብ ከተሞች በመዝሙር ፈረሱ

ስምንቱን ነፋሳት አንተ ስታዛቸው

ውቅያኖስ ባሕሩም ይዘላል ፊታቸው

ቤልፌጐር አልቻለም አንተን መገዳደር

የጥበብ ሃገሯ ታላቅ ነህ እግዚአብሔር

በብዙ መጽናናት ሕይወቴን መለስካት

በቃልህ ወይንጠጅ ነፍሴን አረካት

ለዝናም አይደለም ወይም ለሞቅታ

የምዘምርልህ ለአምልኮ ነው ጌታ

በጥብርያዶስ ባህር ድግስህ ናፍቆኛል

ከፈርያን እንጆራ ፍቅርህ ለይቶኛል

የቦኤዝን እርሻ አልቃርምም እኔ

ዋናውን አጭዳለሁ ጌታ ነው መድኅኔ

አምኜ ስወጣ

አምኜ ስወጣ አንተ አብረኸኝ ውጣ/2/

ላልተውህ በልቤ ሾሜሃለሁ ጌታ/2/

ያን ዓምድ ደመና የመንገዴን ፋና

ስለተከልክልኝ ጠላት አያስቀረኝ

ቅደምልኝ ውዴ ሁሌም በመንግዴ

ሳልወጣ ክርስቱ እንዳይረታኝ ሞቴ

ከፊቴ ኤርትራ ከኋላዬ ጭፍራ

ቢከበኝ አልፈራም አልፋለሁ ባንተ ስም

ቅደምልኝ ውዴ ሁሌም በመንግዴ

ሳልወጣ ክርስቱ እንዳይረታኝ ሞቴ

እርግማን አስማቱ ሰይፍና ስለቱ

አለፈ በክንድህ መች ታንቀላፋለህ

ቅደምልኝ ውዴ ሁሌም በመንግዴ

ሳልወጣ ክርስቱ እንዳይረታኝ ሞቴ

በለስ ባያፈራ ቢበዛም መከራ

መች ልቤ ሊደንቀው ያመንኩት አንተን ነው

ቅደምልኝ ውዴ ሁሌም በመንግዴ

ሳልወጣ ክርስቱ እንዳይረታኝ ሞቴ

ለቆኝ ያ ድካሜ ተራመድኩኝ ቆሜ

የሰማዩን መና አንተን በላሁና

ቅደምልኝ ውዴ ሁሌም በመንግዴ

ሳልወጣ ክርስቱ እንዳይረታኝ ሞቴ

አቤቱ ጉልበቴ ሆይ

አቤቱ ጉልበቴ ሆይ እወድሃለሁ (2)
አንተ ካሻገርከኝ ሁለን አልፋለሁ (2)

ክንድህን እንዳላየሁ ኃይልህን እንዳላየሁ
ሲመሸና ሲነጋ ዘወትር እጨነቃለሁ
አንተ ግን ለሰላሜ ለእረፍቴ ቆመሃል
ያዘነውን ልቤን ውስጤን አሳርፈሃል

ሁልጊዜ ጠያቂ ነኝ መልስ የለኝም ጌታዬ
አንተ ግን መፍትሄ ነህ ስደክም ለብቻዬ
አይዞህ ስትል ሰማሁህ ቃልህ ሲናገረኝ
ዘወትር አምላኬ ነህ የማትተወኝ

የብርቱዎች አምላክ ነህ አውቃለሁ የኔ ጌታ
ለደካማው አንተ ነህ ኃይሉን ምታበረታ
የተሸከመኝ ክንድህ ዝሎ አያውቅም ፍጹም
የማምለጫ አለት ነህ ለነፍሴ ዘለዓለም

በፈረሰው ግድግዳ ሙሉ ሆነህ ቆመሃል
ባነከስኩኝ ጊዜ ጉልበቴን አቅንተሃል
ልናገረው በሰው ፊት ሌላ ምን እከፍላለሁ
አይነስውር ነበርኩኝ ዛሬ ግን አይቻለሁ

አጥቷል ጎሎበታል

አጥቷል ጎሎበታል ብለህ ሳትንቀኝ
ለዚህ ያደረሰኝ ጌታዬ እኔ ማን ነኝ
ይሞላል አይቀርም በአንተ ሸለቆዬ
ጠብቃለሁና ቀንህን ጌታዬ

ገዘን ጽልመት ክፉ ዘመን ቢገጥመኝም እንኳ
ያልፋል ሁለም ታሪክ ሆኖ በፊትህ ሲለካ
ማን አፈረ ማን ጎደለ አንተን የጠበቀ
ፀና ልቤ በእግዚአብሄር ይህን እያወቀ

በዓለም ስፍራ ባይኖረኝም ብሆንም ጎስቋላ
አምላኬ ሆይ ካንተ በቀር አልሄድ ወደሌላ
ጌታዬ ሆይ በፍለጋህ ወጣሁ ከመቃብር
ስመሰክር እኖራለሁ ሥራህን ስናገር

ቀን ለክተህ ጊዜን አይተህ ሰውን የማትጎዳ
ያለወረት ትመጣለህ እኔን ልትረዳ
ከነኤልያብ ወንድሞቼ ባልስተካከልም
ማማ ሆነህ ከፍ አረከኝ አንተ ሰው አትንቅም

እንደ እናት ልጅ እንዳልቆጥርህ ከዚህ ትበልጣለህ
ካንተ በቀር ያፈቀረኝ በምድር ስለሌለ
ስለ ስምህ መነቀፌ ክብሬ ነው ማዕረጌ
በምን መንገድ ላስደስትህ እንደምን አድርጌ

አኑሮኛል ቸርነትህ

አኑሮኛል ቸርነትህ ልክ የሌለው ደግነትህ
እንዳንተ ዓይነት ከየት ይገኛል ሁለም ነገር ትዝ ይለኛል /2/

ያቺ ፈዋሽ አዳኝ እጅህ ዛሬም ለኔ ተዘርግታ
በኃጢአት ርቄ እንዳልጓዝ አስረኽኛል በውለታ
ደግሞስ ሕይወት ምርጫ ቢሆን ካንተ ወደ ማን ይኬዳል
አባቴ ፍቅርህ እኮ ጌታዬ ፍቅርህ እኮ ዓለምን ያስክዳል

ሞቼ ነበር ተቀብሬ ጌታ ወደኔ ባትመጣ
አንተ ሞቴን ባትሞትልኝ ወዴት ነበር የኔ ዕጣ
ከንቱ ነበር ማንነቴ ተሸናፊ ለዚች ዓለም
ግን አንተ የያዝከዉ አባቴ የያዝከው ይኖራል ዘላለም

መቅደስህን ተጠግቼ አይቻለሁ ብዙነገር
በልቤ ውስጥ ያስቀመጥኩት እንዲህ ለሰው ማይነገር
ግን የሆነው ሁለ ሆኖ የለም ዛሬ ያላረፈ
የመከራው እሳት የፈተራው እሳት ባንተ እየታለፈ

አይጠፋኝም ያ ፈገግታ ልጄ ብለህ ያሳየኸኝ
አመጸኛ መጥፎ ሁኜ በትከሻ ላይ ያኖርከኝ
እንዲህም ዓይነት ወዳጅ አለ እየጠለት የሚያፈቅር
ስሙም ኢየሱስ ነው /2/ የጽድቃችን ሚስጥር

ስነፈርቅ ሳለቅስብህ እሸ እያልከኝ ሁለም ሆነ
ማይሆንለት ነገር የለም ለካስ ባንተ የታመነ
መቸኮሌ መጣደፌ አምላኬ ሆይ በከንቱ ነው
መፈጸሙ ላይቀር /2/ ጌታዬ አንተ ያልከው

አናቋርጥም

አናቋርጥም ውዳሴ አናሳንስም ምስጋና (2
እግዚአብሔር ለኛ ያለውን ፈፅሟልና
እግዚአብሔር ርስታችንን አብዝቷልና

ተቀጣጠለ የምስጋናው ችቦ
መቅደሱ ደምቋል በእልልታ ታጅቦ
የደረሰለት ጸሎት ልመናው
ልቦናው ያርፋል ሲያመሰግነው

ዛሬን ላሳየን ውሎልን ውለታ
እየደገፈን በቀንም በማታ
በእድሜያችን ሙሉ ብንዘምርለት
ቢያንስበት እንጂ ለእርሱ አይበዛበት

ዛሬ ያልዘመሩ ነገ ይዘምራሉ
ፍቅሩን ሲቀምሱ ፊቱ ይዘላሉ
የሜልኮል ልጆች ከደርቡ ውረዱ
ትምክህት ትታችሁ ለእግዚአብሔር ስገዱ

ድምጹን ሰምተናል ከፀፍፀፍ ሰማይ
ሕዝቡን ሲያዕናና ሲያወጣ ፀሐይ
መንፈሱ ቃኝቶን ፋነነ ልባችን
ቅጥሩን አፍርሷል መዝሙር ዕልልታችን

አንተ ብቻ ንጉሥ

አንተ ብቻ ንጉሥ አንተ ብቻ ዳኛ
ተመስገን ኢየሱስ የነፍሴ መጽናኛ
ስለፍቅርህ ቆሜ ባነባ
በፈስልህ የቅኔ መባ
አልጠግብ እኔ አይሆንህ ካሳ
እስከ ሽበት ስምህን ባነሣ
ያስተማርከኝ የውዴ ፊደል
የተከልከው በልቤ ወለል
እያነቃኝ አመልክሃለሁ
ካንተ ወዲያ ማንን አውቃለሁ
ሰውነቴ ከግፍ ቢጸዳ
ጎሊናዬ አንተን ቢረዳ
ተጠየፈ የሰውን ምርኩዝ
ስታበራ በልቤ መቅረዝ
ከእንቅብ በታች በእጅህ ተነሳሁ
በተራራው እግሬን አጸናሁ
መገዛቴ ለፍቅርህ ቀንበር
ሰው አረገኝ አንስቶ ካፈር

አንተ ሳታሻግረው

አንተ ሳታሻግረው ያለፈ ሰው ማን ነው
ጌታ ሳትደግፈው የቆመ ሰው ማን ነው
እግዚአብሔር ታላቅ ነው አምላካችን ልዩ
በምድርም መካከል ደግሞም በሰማዩ
ልቤ ባንተ ጸና በረታ በስምህ
ተራራውን ሜዳ ሲያደርግለት ክንድህ
እንደወንዝ ፈሰሰ ሰላምህ በዛና
ሃሌ ሃሌ ሉያ ይድረስህ ምስጋና /2/
የተራበ አንበሳ ሰውን ይታገሳል
የዳነው ዳንኤል አንተን መች ይረሳል
ጠላቱን ለወጠህ ወዳጅ አደረግኸው
ክፉውን በመልካም በበጎ ቀየርከው /2/
ሕይወት ካንተ ጋራ ጣፋጭ ነው እንደወይን
እጅግ ማረፊያ ነው የባረክኸው ዘመን
ስንወጣ ስንገባ ጠባቂ እረኛ
እጅግ በዝታ ታየች ቸርነትህ በኛ /2/
ውሃ ላይ ቢንሳፈፍ መቼ ሞተ ሞሴ
ብርቱ መጠጊያ ነህ እግዜአብሔር ለነፍሴ
ታገለኝ ልባረክ በያዕቆብ ሸለቆ
ነፍሴ ወዳሃለች ሁናሃለች ምርኮ /2/

አከብርሃለሁ

አከብርሃለሁ ስላከበርከኝ
እወድሃለሁ ስለወደድከኝ
ኃጢአቴን ሸረህ ለዚህ ያደረስከኝ
አከብረሃለሁ ስለወደድከኝ

ልዩ ነህ ለኔ ጌታ ኤልሻዳይ
ማርኮኛል ፍቅርህ ሆኖ የበላይ
ገና ዘርፋለሁ የቅኔን አዝመራ
ያረክልኝ ያንተን ድንቅሥራ

ባልታመንም ጌታዬ ለቃልህ
ጠፍቼ ብሄድ ከመንጋው መሀል
እኔን ስትፈልግ ያንተን የፍቅር ድምጽ
ሰምቼዋለሁ አልገደበውም ዕጽ

ምሬቴ መሮህ ተሰምቶህ ጭንቀቴ
ሞቴን ልትሞተው ወርደሃል አባቴ
ቅዱስ ሥጋህን ከመስቀል ቆርሼ
ሕይወት ብዘራ አፈረ ከሳሼ

አብረኸኝ በልተህ ተገኝተህ በቤቴ
በዕንባም አጥቤህ አልወጣም ናፍቆቴ
በድል ስታርግ በስስት ያየሁህ
አሜን ጌታ ሆይ ናልኝ ተመልሰህ

አየኋት በአይኔ አሻግሬ

አየኋት በአይኔ አሻግሬ
የያሬድን ውብ ዝማሬ
ተቀኝሁ እንደ አባቶቼ
እጀን ለክብሯ ዘርግቼ

ድካምና እንቅልፍ እንደምን ሊነካኝ
ድንጋይ ብንተራስ ፍቅርሽ አያስተኛኝ
አይኔ ቢከደን አለሽ በምናቤ
አልተከለልሽም ነግሰሻል በልቤ

መረማመጃ የሎዛ መሰላል
የዜማ ቤቱ የመቅደስ ጽናጽል
የሰማይ ንጉስ በበላይሽ አለ
ድንኳን አድርጎ አንችን የተከለ

ስምሽ በሁሉ ስለተወደደ
ድንግል ለክብርሽ ፍጥረት አረገደ
ካላመኑት ዘንድ ቢሆንም ዝምታ
ከገብርኤል ነው የስምሽ ሰላምታ

ሳደርስ ውዳሴ መጽሀፉን ገልጬ
ተመለከትኩሽ አይኔ እንባ እየረጨ
በገናን ዳዊት መሰንቆንም እዝራ
ሰጡኝ ላነሳሳሽ በክብሩ ተራራ

አዳነኝ ጌታ

አዳነኝ ጌታ አዳነኝ ፈወሰኝ ጌታ ፈወሰኝ (2)
እግዚአብሔር አዳነኝ ኃጢአተኛውን ወደደኝ
ያልፋል ያላልኩት አልፎልኝ አይቼ
በእንባ ታጠብኩኝ ከድቅድቅ ወጥቼ
እንግዲህ ለአንተ ምስክር ሆኛለሁ
ሥራህን ለዓለም ሁሌም እነግራለሁ (2)
ክንድህ ብርቱ ነው ደካማን ለመርዳት
ታውቅበታለህ የዛለን ማበርታት
ዓይኔን ከሰዎች ማራቁ ጠቅሞኛል
ደጅህ ወድቄ መኖር ተሸሎኛል
የኃዘኔን ማቅ አውልቀህ ጣልክልኝ
ሞቴን ስጠብቅ እድሜ ጨመርክልኝ
ከአልጋዬ ላይ አነሱኝ እጆችህ
ተፈውሻለሁ ዛሬ በምህረትህ (2)
ቃልህ ጽኑ ነው ዳግም ይጠግናል
ጎባጣ አቅንቶ ሸባውን ተርትሯል
ሕይወቴ በአንተ ዛሬ አዲስ ሆናለች
በክብር መዝገብ በእጅህ ተጽፋለች
የሐሰትን ፍርድ ጌታ ቀለበስከው
ተጽናንቷል በአንተ ያ የተገፋ ሰው
የግፍን ጽዋ አራቅከው ከፊቱ
በእጁ ላይ የለም ዛሬ ሰንሰለቱ (2)
በሃማ መስቀል መርዶኪዮስ የለም
የናቡቴ ደም በከንቱ አልቀረም
የእውነት ዳኛ ጌታ ስትመጣ
የሐሰቱ ሰው ግፈኛው ተቀጣ

አጋጣሚ አይደለም

አጋጣሚ አይደለም መትረፌ መዳኔ
የጌታ ታምር ነው እረ ይገርማል የኔ
ሞት እንቅልፍ ሆኖልኝ ጭንቀቴም ቀለለ
የረዳኝ ጌታ ነው ውዴ እየተከተለ
ማነው በዚያ በረሃ ያበላኝ መና ያጠጣኝ ውሃ
ማነው ካጋጠመኝ ጥልቁን ሸለቆ ያሻገረኝ
አንተ ነህ ለእኔ እናት አባቴ
ፍጹም ወዳጄ ስጋ እና አጥንቴ
አይኔ አይነቀል ከዙፋንህ
ፊት አያዞርም ፍቅር አይንህ
ወሮኝ ድቅድቅ ጨለማ ተስፋዬ መክኖ ልቤ ሲደማ
አይቶ ሲፈስ እንባዬ ደመና ጠቅሶ መጣ ጌታዬ
ፀሐይ ነውና የብርሃን አምዴ
ኢየሱስ ለእኔ ህይወት መንገዴ
አልተሸነፈኩም ውዴ አግዞኛል
መቃብር ደፍኖ ህይወት ሰጥቶኛል
ሲለይ ነፍስ ከሥጋ በጨለማ ቀን በክፉ አደጋ
ዳንኩኝ ሞት እያየኝ የንስሐ እድሜ ጨመረልኝ
በጽድቁ አይደለም የተረፍኩት
በእርሱ ፍቅር ነው በእርሱ ምህረት
ብቻዬን ሆኜ ሁሌ ማለቅሰው
እየበደልኩት ስለ አዳነኝ ነው
ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ ከጥልቁ ጥሎሃል እየታገለ
ሲኦል ድል መንሳትህ ባዶ ቀርተሃል ተበዝብዘህ
ለራሱ መንግሥት ፈጥሮኝ በአላማ
የልጁን ህይወት ማንም አይቀማ
መቃብር ያልፋል አገልግሎቴ
ተከፍቶልኛል ደጁ የአባቴ

ኤልሮኢ

ኤልሮኢ እላለሁ እኔ (2)
የሚያየኝን አምላክ ስላየሁኝ ባይኔ
የቁርጥ ቀን ወዳጅ ቢሆናት ወገን
ኤልሮኢ አለችው አጋር አምላኳን
የደሃዋን ጩኸት ለቅሶ የሚሰማ
እግዚአብሔር መልካም ነው በቀን በጨለማ
ሚዳና ኮረብታ ዳገት ቁልቁለት
በአንተ ተሻገርኩት ሁሉን አለፍኩት
መልአክህን ልከህ ስላጽናናኸኝ
እኔስ ከአንተ ሌላ ዘመድም የለኝ
ጉድጓድ ውስጥ ተጥዬ ድንጋይ ተጭኖኝ
የአናብስቱ ጩኸት ጨለማው ከብዶኝ
የተዘጋን መክፈት የሚቻለው ጌታ
ከኔ ቆመልኝ ልቤን ሊያበረታ
ከሰማነው በላይ እጅጉን ድንቅ ነው
ካየነው በላይ አምላክ ከሀሊ ነው
ሰምቶኛል በጆሮው ምላሽ አግኝቻለሁ
አይቶኛል በዐይኖቹ ኤልሮኢ እላለሁ

ኤልሻዳይ ነህ

ኤልሻዳይ ነህ ኤልሻዳይ
ትዕግስትህ ብዙ ሁሉን ቻይ
በኃጢአት ብወድቅ ብቆሽሽ
ጌታ ሆይ ከእኔ አትሸሽ
ልጆች ሊያደርገን ሁሉን ችሎ
መራራ ሞትን ተቀብሎ
ገነትን ሰጠን በክንዱ አቅፎ
ትንሣኤ አወጀ ሞትን ዘልፎ
ራቁቴን ነኝ በኃጢአቴ
ልብሴ ነህ አንተ መድኃኒቴ
ምሕረትን ስጠኝ እጠበኝ
የቤቴም ራስ ሁንልኝ
ምሕረት ቸርነትህ ጥልቅ ነው
ውቅያኖስ ባሕር ማይመጥነው
ይህንን አውቀን እንቀኛለን
በዙፋንህ ፊት እንሰግዳለን
ፍቅርህ ልዩ ነው መሰጠኝ
ከዓለም ትቢያ አነሳኝ
ይህን ላረገ ቅዱስ ጌታ
ሰዎች እንዘምር በዕልልታ

ኤፍታህ በለኝ

ኤፍታህ በለኝ ጌታ ኤፍታህ በለኝ/2/

ያለአንተ ለእኔ ማንም የለኝ

አትጨህ የሚሉኝ ስምክን እንዳልጠራ

መውደቄን አይተው ነው ከተናቁት ጎራ

የዳዊት ልጅ ማረኝ ማለቴን አልተውም

ተፈታ እስክትለኝ እስከማገኝ ብርሃን

በምራቅህ ቀባኝ ዳስልኝ ዓይኔን

ስራህን እያየሁ እንዳመሰግን

እጅህን ጫንብኝ ጀሮዬ እንዲሰማ

የማዳንህን ኃይል የፍቅርህን ሸማ

አይሁዳዊው ርቋል ካህኑም አላየኝ

ዕርቃኔን ወድቄ ማንም አልጎበኘኝ

ሳምራዊ ጌታዬ አንተ ነህ ዕድሌ

የማትሰለቸኝ ቢበዛም በደሌ

በነገስታቱ ፊት ጽድቅ እንድመሰክር

ተሻግሬ እንዳልፈው የፍራትን ድንበር

ኤፍታህ በለኝ አንተ ልቤ እንዲበረታ

እንዳገለግልህ ሁሌም ጠዋት ማታ

እመቤታችን የአንድዬ እናት

እመቤታችን የአንድዬ እናት

በመንገዳችን ቅደሚ ከፊት

ስምሽ ስንቅ ነው በአንቺ ላመኑ

በመከራ ቀን የጠሩሽ ዳኑ

ፈታኞችን ቆሞ መንገዱን ዘግቶታል

በቁጣ ተሞልቶ እጅጉን ይዝታል

ከአንቺ ጋር ከወጣን ይቀናል መንገዱ

ማርያም ማርያም ስንል ፀጥ ይላል ሞገዱ

አንደክምም ስንጠራሽ እንበረታለን

በፀናው ኪዳንሽ እንታመናለን

መቅደስሽን ሞልተን ስምሽን ስንጠራ

ይድረሰን ፀሎትሽ እመ አምላክ አደራ

ፍቅር የተማርንብሽ የእግዚአብሔር ከተማ

መንፈስን ተመላን ድምፅሽን ስንሰማ

ልክ እንደ ኤልሣቤጥ ሀሴት አደረግን

የምስጋናን ቅኔ ልንቀኝ ወደድን

እመቤቴ ያምላክ እናት

እመቤቴ የአምላክ እናት
ላመስግንሽ ቀን ከሌሊት
ለልጅሽም ክብር ውዳሴ
ታቀርባለች ዘወትር ነፍሴ (2)

የለመለመች መስክ አምላክ የመረጣት
የጽላቱ ኪዳን ታቦቱ ድንግል ናት
የሰማይ የምድር ንግሥት ናትና
ክብር ይገባታል ዘወትር ጠዋት ማታ

ሌቤ ተነሣሣ ተቀኘ ለክብርሽ
በፍፁም ትህትና ሊያመሰግንሽ
ጽዮን መጠጊያ ነሽ የአብርሃም ድንኳን
የታጠረች ተክል እመ ብዙኃን

አደራሽን ማርያም የሁሉ እናት
በምልጃሽ አስቢኝ ኋላ ስራቆት
ያንን የእሳት ባሕር አሻግሪኝ ድንግል ሆይ
እንዳልወድቅ እንዳልሞት ከቶ እንዳላይ ስቃይ

እመቤቴ ስልሽ

እመቤቴ ስልሽ ነይልኝ ለልጅሽ
ቅረቢኝ በሕይወቴ እናቴ ስጠራሽ

ኑሮዬ ተዛብቶብኝ ደክሜያለው እናቴ
እኔን ቅረቢኝና ልፅናና በሕይወቴ
በደሳሳ ጎጆዬ በቤቴ ገብተሽልኝ
በእኔ የነገሰውን ኃዘኔን ለውጭልኝ

እሻለሁ ፍቅርሽን እናትነትሽን
ዘወትር ከጎንሽ/ህ ነኝ ብለሽ አነጋግሪኝ
ስምሽን ለዘላለም እጠራለሁኝ እኔ
ለመንገዴ መሪ ነሽ ለዐይኔ ብርሃኔ

በድቅድቁ ጨለማ እኔ እንዳልወድቅብሽ
ከቀኝና ከግራ ደግፊኝ እባክሽ
ኑሪ ከልጅሽ ጋራ እመ አምላክ በዘመኔ
አደራ አትራቂኝ ጠባቂ ሁኚኝ ለኔ

እረ እንዳንተ ያለ

እረ እንዳንተ ያለ ከወዴት አለ
የበደሌን ሸክም ያንከባለለ
ውዴ እንዳንተ ያለ ከወዴት አለ

ፃድቅ ጠፍቶ አንድስ እንኳ በሀጉ ፊት ሲመዘን/2/
አይደለም በደላችን ፅድቃችን መርገም ሲሆን/2/
የእግዚአብሐየር ልጅ ተገልጠህ የጠላት ምክሩ ፈርሷል/2/
ኢየሱስ እርቃን ሆነህ ትውልዱ ምህረት ለሷብሰል/2/

ባሪያዋን እንድታነግስ የባርያን መልክ ይዘሀል/2/
እንባየን የአይኔን ጅረት በደምህ ገድበሀል/2/
የልቤ ልብ አንተ ነህ ነፍሷ እኮ ነህ የነፍሴ/2/
መኖሬ ህልም ነበር ባትሆነኝ እስትንፋሴ/2/

ለፃድቅ ነፍሱን ሚሰጥ በጭንቅ ይገኝ ይሆናል/2/
ገና ደካማ ሳለሁ አንተ ግን ወደኸኛል/2/
በሞትህ እንደታረኩ በህይወት እድናለሁ/2/
የዘላለም መሥዋዕቱ ዘላለም አምንሀለሁ/2/

በኪዳን ነው ህይወቱ በኪዳን ነው ኑሮየ/2/
ደምህ ነው ማህተሜ ያጌጥኩብህ ድሪየ/2/
ሞትህን በሚመስል ሞት ካንተ ጋር ብተባበር/2/
በትንሳኤህ ታድሸ በራለሁ እንደ ንስር/2/

እርሱ ብቻ የማይሞት

እርሱ ብቻ የማይሞት ነው
በብርሃን የሚኖረው
በአባቱ ቀኝ አለ ነግሶ
አማኑኤል ክብርን ለብሶ

ትላንትናን ዛሬ ውጧል
ሁሉም ነገር ይለወጣል
ሳይደበዝዝ የሚያበራ
ሁሌም ጽኑ የርሱ ሥራ

የአይሁድ ትግል ያልነቀለው
ክፋታቸው ያልሸፈነው
የደም ሐውልት ምሰሶአችን
በርሱ ፀንቷል ከፍታችን

የዓለም ጀግኖች ተቀብረዋል
የበረቱ ተሰብረዋል
ገዳዩን ሞት የገደለ
እንደ ጌታ ወዴት አለ

መቃብርን የቀበረ
ኃይለኛውን የሰበረ
ኢየሱስ ነው ፅኑ ጌታ
ማይሸነፍ ማይረታ

እናመሰግንሃለን

እናመሰግንሃለን (2)
እንደ አባቶቻችን በማኅሌት እንደጠራሃለን
እንደ ቅደሳኑ ለክብርህ እንዘምራለን

ለአምላክ ውዳሴ ለፈጣሪ ክብር
ማለዳ ተነስተን ምስጋና ስንጀምር
የአባቶች ዝማሬ ቅኔ መወድሱ
ሲሰማ ደስ ይላል ከቤተ መቅደሱ

ሥርዓተ ሰማይ በምድር ተሠርቶ
በአባቶች ልቦና የአምላክ ጥበብ መልቶ
ዝማሬው ፈለቀ ከታላቁ መቅደስ
በጥዑመ ዜማ ፈጣሪ ሊወደስ

ድምፁ ቀሰቀሰን ከቅደስ ተራራው
የያሬድ ጽናጽን መሰንቆ በገናው
የጽዮን ደናግል ለመዝሙር ተነሱ
ሥሉስ ቅዱስ በሉ ስሙን አወድሱ

ማኅሌቱ ሲቆም ሰዓታት መዝሙሩ
ቅዱሳን መላእክት አብረው ሲዘምሩ
ፍፁም ተመሰጠች ነፍሳችን በደስታ
ለምስጋና ስትቆም ከቅዱሳን ተርታ

እኔ አላይም ካንተ ሌላ

እኔ አላይም ካንተ ሌላ
ዞር ብዬ ወደኋላ
ኪዳን ገባሁ ከራሴ ጋር
ይሻለኛል ቤትህ መኖር

ማራኪ ነህ እውነተኛ
የማትደክም የማትጥኛ
በችንካርህ ከበኸኛል
እንዳንተ ያለ የት ይገኛል

አመፀኛ ወንበዴ ነኝ
የአለም ውበት የማረከኝ
እንዴት ብለህ ወደድከኝ
አሸነፍከኝ ደነቀኝ

ድንጋይ ነበር የኔ ደሞዝ
በዚህ ዓለም ስቅበዘበዝ
ነፃ ወጣሁ በአንተ ፊት
እልሃለሁ መድኃኒት

ወንበር ስበህ አሳረፍከኝ
ቤትህ ገባሁ ስትፈልገኝ
አልገባኝም ገና ፍቅርህ
በዘመኔ የምማርህ

እኔስ አልፈራም

እኔስ አልፈራም ድንግልን ይገፍ
በህይወቱ ቢያልፍ ጭንቀት ትካዜ
የምመካበት ስሟ አጽናኝ ነው
እየወደድኳት እጠራታለሁ

እናቴ ስላት ልጄ እያለችኝ
በሀዘን በደስታዬ ቅርቤ የሆነችኝ
የማይጠፋ ነው የማይቀበር
የአደራ እናቴ ለእኔ ያላት ፍቅር

ቀስቱ ታጥፎልኝ ከእግሬ ሥር ወድቋል
ምልጃዋ ረድቶኝ ስሜ ታድሷል
በጨለማ ዓለም የእኔ ብርሃኔ
ትረዳኛለች በዕድሜ ዘመኔ

የተረሳውን ታስታውሻለች
ስሟን ለጠሩ መደገፊያ ነች
ጩኸቴን ሰምታ አትጨክንም
በዘንዶ አፍ ውስጥ አትተወኝም

የመስቀሉ ስር ድንቅ ስጦታ
የልቦና እረፍት በቀን በማታ
ድንግል ዋሴ ናት መሸሸጊያዬ
ጦር መመከቻ ጽኑ ጋሻዬ

እንሰዋለን ቅኔ

እንሰዋለን ቅኔ ቆመን ከደጅሽ /2/
የአምላክ እናት የጌታ እናት <u>ንጽህት ስለሆንሽ</u> /2/

ተስፋው ተቀጠል ሐሳቡ ተሳካ
የአዳም ሰላሙ ደስታው አይለካ
በልጅሽ ቤዛነት ፍጹም ስለዳነ
ታላቅነትሽን ክብርሽን አመነ

ስፍር ቁጥር የለው በረከትሽ ብዙ
ፍቅርሽ የበዛለት መች ያልቅና ወዙ
ይኸው እናታችን ቅኔና ምስጋና
ከሰማይ ከምድር ተመርጣሻልና

ከፍ ብሎ ይታያል የስምሽ አላማ
በብርሃንሽ ፈክቶ ድቅድቁ ጨለማ
እንዳንቺ ያለ ፀጋ እንዳንቺ ያለ ፍቅር
ለማንም የለውም ቃሉ ነው ምስክር

በእስራኤል ሞልተው ማርያም የሚባሉ
በውበት በሀብታቸው ክብር ተቀበሉ
አንቺን ብቻ ለየሽ እናቱ አደረገሽ
ፍቅርና ትህትና ስለተገኘብሽ

እንዘምራለን ለእግዚአብሔር

እንዘምራለን ለእግዚአብሔር እንዘምራለን ለጌታ
ስለደገፈን በክንዱ ስለዋለልን ውለታ
ጠፍቷል የፍርኦን መከራ
ሜዳ ነው የለም ተራራ
በፀጥታ ውስጥ መርቶናል
ዳግም ላይተወን ይዞናል/2/
የታመነ ነው ገናና
ፍቅሩ በዘመን የፀና
ባንታመንም ለቃሉ
ሁሌ ይታየናል መስቀሉ/2/
መልካም ነው ትሁት እረኛ
ማያንቀላፋ ማይተኛ
በምቹ ክንዱ ተንጋለን
ሌሊቱ ሰላም ነጋልን/2/
ፍቅር ነው ጌታ ዘላለም
ነፍሱን የሰጠ ለአለም
እናምነዋለን ጌታ ነው
ዙፋኑ የበላይ የሌለው/2/

እንደ ቅዱስ ዳዊት

እንደ ቅዱስ ዳዊት አንደበቴን ፍታ
የቅኔ የመዝሙር የይባቤ ጌታ
ይረፍልኝ ልቤ ላመስግንህና
ምህረትህ በኔ ላይ ዘላለም ነውና
ሄሮድያዳ ሆይ ዘፈንሽ ኃይል አጥቷል
የእግዚአብሔር ምስጋና ምድራችን ከድኗል
ዝም የማይል ልሣን ሰቶኛል ጌታዬ
ለስሙ ዘምሬ ቆምኩኝ ሰው ተብዬ
ከተጠራን ከተሰጠን ለስሙ ምስጋና
አሜን ይበል ምድር ሰማይ ዛሬም እንደገና
ግብረ ተልኮዬ ቅኔ ነው መዝሙር
በልቤ ነግሰሃል ቅዱስ እግዚአብሔር
ከወገኔ ጋራ ልጥራህ በእልልታ
ያሳደከኝ አምላክ ናፍቆቱ ነህ ጌታ
ከተጠራን ...
ጀርባህን አያለሁ ርቄም ብወጣ
ስለቀደምክልኝ ከፊት ስለወጣ
በየትኛው ቋንቋ ተመስገን ልበልህ
ዘምሬ ዘምሬ አልችልም ልጠግብህ
ከተጠራን ...
ምስክር አልሻም እንድዘምርልህ
ይቀሰቅሰኛል ፍቅርና ምህረትህ
እስካጣ እስክደክም እንቅልፍ በዓይኖቼ
ንሴብሆ ልበል መቅደስህ ገብቼ
ከተጠራን ...

እንደ እግዚአብሄር ያለ

እንደ እግዚአብሄር ያለ ማንም የለምና (2)
እልል በሉ ቁሙ ለምስጋና (2)

ባሕር ተከፈለ እስኪታይ መሬቱ
ፈርኦን ወደቀ አልሰራም ትምክህቱ
ደካሞችም ፀንተው ተራመዱ
ሃይለኞችም ይኸው ተዋረዱ

የኢያሪኮ ቅጥር የማይደፈረው
ይኸው ፈራረሰ የሰው እጅ ሣይነካው
ሃይለኞቹም ቢበረታቱብን
እንፀናል በእርሱ ተደግፈን

የተወረወረው የጠላታችን ጦር
ሜዳ ላይ ወደቀ ጋሻ ሆኖ እግዚአብሔር
ለሥላሴ ይድረስ ምስጋናችን
ተሸነፈ አዳኝ ጠላታችን

ባሕር ላይ ሲራመዱ ሞገስ አለው እርሱ
በግርማው ሲነሣ ፀጥ ይላል ነፋሱ
የድንግል ልጅ እኛ የምናመልከው
ከሃሊ ነው የለም የሚሣነው

እንደ ባለማዕረግ

እንደ ባለማዕረግ ተመለከትከኝ
ቀና ብዬ ሄድኩኝ ክንድህ ደግፎኝ (2)
በጉልበቱ ልስገድ ላቀርብ ምስጋና
ፍቅር ነህ ጌታዬ ክብርህ ገናና

አነሰኝ በዛብህ ብዬም ባማርርህ
ተሸክመኸኛል በሰፊው ትከሻህ
አምላኬ ሆይ ፍቅርህ ልቤን አሸነፈው
በዘመኔ ሁሉ ባሪያህ እሆናለሁ

አንተ ያየኸው እለት ሰውም ሰው ይሆናል
ከጥልቁ ተነስቶ ከላይ ይቀመጣል
ትጥቅን የሚያስፈታ ጉልበት አለው ፍቅርህ
መስቀልህን ይገፍ ጌታ ልከተልህ

አይቆረቁረኝም ይመቸኛል ክንድህ
ሰለቸኝ አላልክም ስኖር ከመቅደስህ
ዓለም ብትቸኩል ልትፈርድ በድክመቴ
ገመናዬን ሸፋኝ አለህ መድኃኒቴ

ሲታወክ ሲጨነቅ ሲናጥ ልቦናዬ
አዲስ ያረገኛል ሲነጋ ጌታዬ
በሕይወት ኖራለሁ ደግሜ በተስፋ
ፈጣሪዬ ለኔ ልቡን ስላሰፋ

እንደምወድህ

እንደምወድህ ጌታ ታውቃለህ
እንደማከብርህ አንተ ታውቃለህ
ለሞት አትስጠኝ ነፍሴን ለዓለም
እንዳንተ ያለ ማንም የለም

እንዳንተ ያለ ወዳጅ የለም በዓለም ላይ
ያውሩት ቸርነትህን ምድርና ሰማይ
ያንን የሞት ጎዳና ሁሉንም ትቼ
ወዳንተ መጣሁ እጄን አንስቼ

ሞት እጁን ሲዘረጋ አስጥለኸኛል
ክንድና ክንዴን ይዘህ አሻግረኸኛል
ማን አሁን ይህን ያምናል ይህን ይቅርታ
ንገሥ በልቤ የጌቶች ጌታ

ዝምታህ ያስፈራኛል ድምፅህን ልስማ
መብራቴን እንዳይዘጋው የዓለም ጨለማ
የማምለጫ አለቱ እጅህን ዘርጋ
መባዘን ይብቃኝ ልቤ በአንተ ይርጋ

እንዴት ወጣሁ ብዬ

እንዴት ወጣሁ ብዬ ከቶ አልደነቅም
አምንሃለሁ እና ትተኸኝ አታውቅም
ያሁሉም አለፈ ቀረ ወደኋላ
ማልቀስ ማንባት ይብቃኝ ከእንግዲህ በኋላ

ከእንግዲህ አይመጣም ያ ቀን ተመልሶ
ላያዳግም ሄዷል እንባዬን አፍስሶ
በመስቀል ላይ ሆነህ ችንካርህ ታይቶኛል
ያ ሁሉ መከራ በአንተ አልፎልኛል

እንደምን ተነሣ አልዓዛር አትበሉ
ይችላል እግዚአብሔር ይችላል ኃያሉ
ታሪክ ሆኖ አልፏል ያኔ ያስጨነቀን
ስንቱን ተሻግረናል ጌታ እየጠበቀን

ከዓሣ አንበሪው መዳፍ ከጥልቁ ወጥቼ
ዘምርለታለሁ ዳግም ተሠርቼ
የሸቶዬን ብልቃጥ ሰበርኩት በፊቱ
በጽድቅ እንዲያስበኝ ጌታ በምህረቱ

ቁስሌን ቆሰልክልኝ ጥሜንም ተጠማህ
መቼ ገባኝና የመስቀሉ ዓላማ
ለካስ ስለ ፍቅርህ የማይሆኑት የለም
አሳየኸኝ ጌታ ታላቅ ነህ ዘለዓለም

እኛ ግን የተሰቀለውን

እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን
እኛ ግን በድል ያረገውን ኢየሱስን እንሰብካለን
ጥላቻ ፀብ አይደለም ትጥቁ
ብቀላ ጦር አይደለም ስንቁ
ትህትና ፍቅር ነው በትሩ
ለአምልኮ የጣለን ከስሩ
ሊገዛን ደሙን መካዘረ
በሞቱ መውጊያውን ሰበረ
ቀሚሱ ዕጣ ሲጣልበት
ተገፎ ዓለም አጌጠበት
ያልያዘው ሞትና መቃብር
ያረገው በግርማ በክብር
በአባቱ ቀኝ የተቀመጠው
ኢየሱስ ለዘላለም ያው ነው
ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ሆኖ
በሞቱ ዓለማትን ከድኖ
ነፍሳትን ከሲያል ዘረፈ
በደሙ ህያው ታሪክ ፃፈ
ለእናቱ ለአባቱም አንድያ
ውድ ነው የሌለው መተኪያ
ለፍቅር ነፍሱን ያልሰሰተ
አንድ ሆኖ ስለሁሉ ሞተ

እውነተኛ ሰላም

እውነተኛ ሰላም ያለው ከቤትህ ነው (2)
እርዳኝ አልናወጽ እለምንሃለሁ (2)
ኃጢአቴን ሳስበው ልቤ ይጨነቃል
ከአንተ መለየቴ ነፍሴን አድክሟታል
ወደ አንተ መልሰኝ እኔ እመለሳለሁ
እውነተኛ ሰላም ያለው ከቤትህ ነው
ለቅዳሴው ጸሎት ዘወትር እንዳልተጋሁ
በአደባባይ ቆሜ ስምህን እንዳልጠራሁ
ተሰነካክዬ ወድቄአለሁና
እርዳኝ አማኑኤል በሃይማኖት ልጽና
ዐይኔ እንባ ያመነጫል ሳለቅስ ስለኃጢአቴ
የንስሐ ትሁን ቀሪዋ ሕይወቴ
በመዳኔ ሰአት በዛሬዋ እለት
ፍቅርህን አስቤ መጣሁ ከአንተ ፊት
ጌታ ሆይ ፀፀቴን እንባዬን ተቀበል
አባትሽ/ህ ነኝ በለኝ እኔም ልጅ ነኝ ልበል
ዘይት ሳላዘጋጅ ድንገት መጥተህብኝ
በርህን በመዝጋት ከደጅ አታስቀረኝ

እውነት ስለሆነ

እውነት ስለሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ
ዋለ ባደባባይ ሲሰደብ ሲከሰስ
የሐሰት ዳኝነት አምላክን ወቀሰው
ሕይወት ሰጠን እንጂ ጥፋቱ ምንድን ነው
ከቃሉ እብለትን ባያገኙበትም
ዝምታውን አይተው አላዘኑለትም
ባላወቁት መጠን ጠሉት አለበደል
ጥፋቱ ምን ይሆን የሚያደርስ ከመስቀል
የልቡን ትህትና ፍቅሩን ሳያስተውሉ
ቸሩ ጌታችንን አቻኩለው ሰቀሉ
ርኅርኁን ጌታ አቻኩለው ሰቀሉት
ሞትን አስወግዶ ቢሰጣቸው ሕይወት
ስለቸርነቱ ስድብን ከፈሉት
ስለ ርኅራሄው የሾህ አክሊል ሰጡት
ሀሞትና ከርቤ ሆምጣጤ ቀላቅለው
መራራ አስጎነጩት ጨክኖ ልባቸው
ፈውስን የሰጣቸው ልባቸውን ሞልተው
አሉት ወንበዴን ነው ስቀለው ስቀለው
ከእጁ በረከትን የተሻሙ ሁሉ
ይጮኹ ነበረ ይገደል እያሉ /2

እግሩ ለቆመበት

እግሩ ለቆመበት ስፍራ እንሰግዳለን
መዝሙረኛው ዳዊት በመጽሐፍ እንዳለን
በድንግል ማኅፀን ቆሞ ስላየነው
የጸጋ ስግደትን ለእናታችን ይኸው (2)
በሉቃስ ተጽፏል የገብርኤል ሰላምታ
የዮሐንስ እናት የኤልሳቤጥ ደስታ
ከሰማይ ከምድር ምስክር ይዘናል
በስሟ ብንዘምር ማን ይቃወመናል
ከቀስት ልናመልጥ ምልክት ተሰጠን
አለፈ ያ ዘመን መስቀሉን ጨብጠን
የመዳን ምክንያት ቀድሞ የተጻፈች
ድንግል የአምላክ እናት ምልክታችን ነች
ሰማያዊ ምስጢር ተአምር የታየባት
የሲና ዕፀ ጳጦስ ነበልባል ያልበላት
መአዛዋ የሚስብ ቀናንሞስ ሽቱ
ስግደት ዘበጸጋ ይገባል ለእናቱ
የወርቅ ማዕጠንት ዕጣን የሞላባት
የልባችን ተስፋ ምዕራገ ጸሎት ናት
የሕይወታችንን ወይን ያስሞላች በቃና
ለጌታችን እናት ይድረሳት ምስጋና

እግዚአብሔር ከኛ ጋር ባይሆን

እግዚአብሔር ከኛ ጋር ባይሆን ጠላት ምንኛ በናቀን
ግን ሁሉም በጌዜው አልፏል ቸርነቱ ሲጠብቀን
የነሐሱ መዝጊያ ብረቱን ባይቆርጠው
በራሱ ችሎታ ማን ነበር ሚያመልጠው
ግን ሁሉም አለፈ ቀስ እያለ ነጋ
ለካስ ወድቆ አይወድቅም አንተን የተጠጋ /2/
ያሻግራል ሲሉን ሰምተናል በዝና
ሌሊት በአምደ ብርሃን ቀኑን በደመና
ዛሬ ግን ተገልጧል ማዳኑ በላዬ
ወዳጄ እለዋለሁ ባለውለታዬ /2/
ፀጉራችን ተላጭቶ ናዝራዊነታችን
ጭፍራው እያፏጨ ነግሶ በላያችን
እግዚአብሔር ሲያስበን ጉልበታም ሆነናል
ምሶሶውም ይዘን ጠላትን ፈጅተናል/2/
አይችሉም እያለ ይፎክራል ጠላት
አሳላፊው ንጉሥ የት ሄዶ የኛ አባት
የማይወጣውን ወጣነው ታግሰን
እልል እንላለን ከእርሱ ጋር ነግሰን /2/

እግዚአብሔር ይመስገን

እግዚአብሔር ይመስገን ለዚህ ያበቃን
ካቀረቀርንበት ቀና ሊደረገን
ስንደነቃቀፍ ጨሊማ ውጦን
ጭጋጉን ገሊልጦ ብርሃን ሊሳየን
የግብፅ ከተሞች የገነባናቸው
የእኛ አይደለም ወጣና ትተናቸው
ደካሞች ብንሆንም አንተ ቀደምክልን
የመከራን ቋጥኝ አንከባለልክልን
ብትዘገይ እንኳ የሚቀድምህ የለም
ትደርስልናለህ አታሳፍረንም
ቃልህን ስታሰማን እንበረታለን
አስፈሪውን ባህር በአንተ እንቀዝፋለን
ጠፍተዋል ተብሎ መዝገቡ ሲዘጋ
ታሪካችን መክኖ ስንፈራ ስንሰጋ
እርሱ ግን መች ተወን ቀንበሩን አነሳ
ከወጥመዱ ተረፈን ዘለልን እንደ እንቦሳ
ሹመት አክሊላችን ማዕረጋችን ነህ
ህይወት አድሎናል መስቀልህ ሞትህ
ያንተ መንገላታት ማለት ደፋ ቀና
እኛን አቁሞናል ይድረስህ ምስጋና

እጠበኝ ቆሸሻለሁ

እጠበኝ ቆሸሻለሁ አምላኬ በድያለሁ
ያለእናት ያሳደከኝ ያለ አባት የጠበከኝ
ያን ሁሉ ዛሬ ረሳሁ እጠበኝ ቆሸሻለሁ

ከድንኳንህ ብታስገባኝ ሞገስ ሰጥተህ
የነ አፍኒንን ምግባር ይገፍ አስቀየምኩህ
ቅብዓ ሜሮን ያተምክበት ልጅነቴ
እንዳይጎድፍ ጠብቀልኝ ቸር አባቴ

ኃይል አኑረህ እንደ ሶምሶን በፀጉሬ
ጎልያድን አስጥለኸኝ በጠጠሬ
አቅም ቢያንሰኝ በሥጋ ጦር
ተሸንፌ ደጅህ መጣሁ የፅንባ መባ በዓይኔ አቅፌ

እንዳትረሳኝ በመዳፍህ ቀርጸኸኛል
እንዳትተወኝ ያለመጠን ወደኸኛል
ባትሰነዝር ልትቀጣኝ የሞት በትር
የትዕግሥትህ ሰሌዳ ነው ለኔ ክብር

ከከንፈሬ ጥበብ ጽፈህ ቅኔ ቢፈስ
በመታበይ አሳዘንኩት ያንተን መንፈስ
ፍቅር ግተህ ከእቅፍህ ስር ያሳደከኝ
እባክህን በበደሌ አትቅሰፈኝ

እፁብ ድንቅ ነው

እፁብ ድንቅ ነው ውለታው
እግዚአብሔር ለኛ ያረገው
ከቶ አይጥለንም ለዘላለም
እንደ አምላካችን ማንም የለም

ወድቀን ነበር ተነስተናል
ባሕር አቁሞ አሻግሮናል
ድንቅ አደረገ ታምር ሰራ
እያንሳፈፈ ያን ተራራ

የጠፋውን በግ የፈለገ
ራሱን ባዶ አደረገ
መስቀል ታቅፎ ክንዱ ዛለ
ምን ያልሆነልን ነገር አለ

ከአባትም በላይ አባት ነው
የልጆቹ እንባ ሚገደው
የጭንቀታችን ተካፋይ
አዛኝ ጌታ ነው ሁሉን ቻይ

ዳግም እንድንቆም በሕይወት
ጨክኖ ወደደን እስከ ሞት
ከእንግዲህ አንፈራም እንጸናለን
ለክፉ የማይሰጥ አባት አለን

ኦ እንዳንተ ያለ ወዳጅ

ኦ እንዳንተ ያለ ወዳጅ አላገኘሁም እኔ
ኦ ውለታህን ሳስበው በእንባ ይመላል ዐይኔ
ከእናቴም ልጆች በላይ አንተ ውድ ነህ ለኔ
ወዳጅና ዘመዴ ጌታ የክፉ ቀኔ
ምን አለኝና ልስጥህ የሚነገር የሚወራ
እኔስ ተሸንፌአለሁ በእንባ ስምህን ልጥራ
ተስደጄ ብወጣ ወጥተህል ከኔ ጋራ
ትላንትናን አለፍኩት ጠላቴን እያራራ
ደግሞ የነገውን ቀን አንተ ታውቃለህ ጌታ
ወጥመዴን ስበርና አፌን ሙላው በእልልታ
በእስረኞች መሀል ሆኜ ሰንሰለት ለብሻለሁ
ዓለም እውነት የላትም ፍትህ ካንተ
እሻለሁ መቼ ታዕናናኛለህ ወዳጅና ዘመዴ
አውጣኝ አውጣኝ ለሚልህ አንተ አታጣም ዘዴ
መመላለስ አይደክምህ እኔን ማስታመም አንተ
ደክመህ አልፈህልኛል እጆቼን አበርትተህ
ሁሌ በራ ላይ ቆመህ ደጃፌን የምትመታ
ግባ የክብር ንጉስ ብያለሁ ማራናታ /4/

ከጎሊና በላይ

ከጎሊና በላይ ነው ከመናገር በላይ ነው
አምላኬ ቸርነትህን በምን ቃል ልግለፀው
ምላሴ ተላቆ ክብርህን ሲያውጅ
እንባዬ ይፈሳል ከዐይኖቼ ደጅ
ከሰው አሳንሰህ አልተውከኝም እና
አቀርባለሁ ለአንተ ውዳሴ ምስጋና
ጌታ ባንተ ሥራ ደስታ ይሰማኛል
የአምላኬ ቸርነት ልቤን ይነካኛል
ብድራት ሳይኖረኝ እንዲሁ ወደኸኝ
በኑሮዬ ሁሉ የሞላኽልኝ
ልቤ ይደነቃል ጌታ ባንተ ሥራ
ከጣሪያዬ በታች ያረከው ሲወራ
ባዶ ማሰሮዬ ዘይትን ተሞልቶ
ተመስገን እላለሁ ልቤ ተደስቶ
ቀና ብሎ መሄድ ሰላም መተኛት
ፍቅርና ደስታ ብዙ በረከት
ተመስገን ለማለት ለማደር ረክቶ
ካንተ ካልተሰጠ ከየት ይገኛል ከቶ

ከሞት እንድንድን

ከሞት እንድንድን ቤዛ የሆንከን
ምን እንከፍልሃለን አምላክ ተመስገን
ትዕቢተኛውን ልብ ታዋርደዋለህ
የሚሳንህ የለም ሁለን ትችላለህ

ስምህም ድንቅ ነው እጅግ የተፈራ
ዝናህም በአሕዛብ በብዙ የተወራ
የአምላኬ ቸርነት ከእኔ ጋር ነውና
አልፈራም አልሰጋም በብዙ ፈተና

የፈርዖን እብሪት እልህ መጋባቱ
ከማይችለው ጋራ ለፀብ መነሳቱ
ፍጻሜው ሞት ሆነ ከባሕር መስጠም
የእስራኤል ታዳጊ ሚመስልህ የለም

ናቡከደነፆር ኃይሉ በጣም በዝቶ
ያለ ልክ ሲመካ በሥራው ተኩራርቶ
ከስልጣኑ ሽረህ በዱር አሳደድከው
ንግሥና ከሰማይ መሆኑን ነገርከው

ኃይልህ እጅግ ብርቱ የጸና ነውና
የሚገዳደርህ ማንም የለምና
ከኃያላን ሁሉ በእምነት እንበልጣለን
በመድኃኒዓለም በአንተ እንመካለን

ከሰማዩ ከፍታ

ከሰማዩ ከፍታ ከፍ ብላ ጽዮን በሰገነት ላይ ተቀምጣ
ድንግል በክብር በግርማ ትኖራለች አጊጣ

ዐይን ከሞላባቸው ከኪሩቤል
ክንፋቸው ከበዛ ከሱራፌል
ከሊቃናቱ ሁሉ ትበልጣለች
እሳተ መለኮትን በሆዷ ስለተሸከመች

ከንጉሡ በስተቀኝ ከዙፋኑ
ንግሥቲቱ ቆማለች በየቀኑ
የቃል ኪዳን ቀሚሷን ተጎናፅፋ
የምትማልድልን ድንግል ናት የሁላችን ተስፋ

በብርሃን ወንበር ላይ ተቀምጣለች
ጨረቃን ከእግሯ በታች ተጫምታለች
የቅድስናን ውበት ተሸልማ
የምታብረቀርቀው እርሷ ናት የልዑል ከተማ

ከዕብራውያን ሴቶች ተለይታ
ከሔዋን ዘሮች ሁሉ ታየች ጎልታ
ሰባቱን መቅረዝ ልጇ ያበራል
ሥጋዋን ተዋሕዶ በፍቅር እኛኑ መስሏል

ከራድዮን

ከራድዮን አማኑኤል ፀዓዳ ወፍ
ነፍሴ ወጣች በመስቀልህ ከሞት መዳፍ
ዐይንህ አይቶኝ እጆችህን ስትዘረጋ
ድኜ ቆምኩኝ ተነስቼ ከጭንቅ አልጋ

ተይዘሃል ቤተመንግሥት

ታስረህ ቆመህ በሸንጎ ፊት

አይተኸኛል በህመሜ

ተስፋዬ ነህ ለመቆሜ

ፊትህ መቼ ተመለሰ
ልብህ ፍቅርን አፈሰሰ
ዐይንህ በኔ ስላረፈ
ሞቴ ባንተ ተሸነፈ

አፍህን በአፌ ላይ አኑረህ

እስትንፋሴን ተቀብለህ

የኔን ደዌ ወስደኸዋል

ጌታ ሞቴን ሞተኸዋል

ፀአዳ ነጭ መልክን ትተህ
ስለክብሬ ክብርህን ጥለህ
ዝለህ ጠቁረህ በመስቀል ላይ
ገብተህ ወጣህ ከሞት ድንጋይ

ከክርስቶስ ፍቅር

ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየኝ ማነው
መከራ ችግር ስቃይ ወይስ መራቆት ነው /2/

አንፈራም አንሰጋም አንጠራጠርም
እግዚአብሔር ከእኛ ይኖራል ለዘላለም /2/

የሰማይ ቤታችን አማኑኤል የሰራው
ግንቡ ንጹህ ውሃ መሰረቱ ደም ነው /2/

ሳይነጋ ተሻግረን እንግባ በጠዋት
በደሙ መስርቶ ከሰራልን ቤት /2/

ከቶ የት ይገኛል እንዲህ ያለ ቤት
የውሃ ግድግዳ የደም መሠረት /2/

የውሃ ግድግዳ የደም መሠረት
ይኸው እዚህ አለ የአማኑኤል ቤት /2/

ከውለታ በላይ ነው

ከውለታ በላይ ነው ያንተ ውለታ
ከስጦታ በላይ ነው ያንተ ስጦታ
ሥራህ አስገረመኝ ከፍ በል ጌታ
እጅን ባፈ ጫንኩኝ ከፍ በል ጌታ

እንዳላጠፋ ሰው ከቶ እንዳልበደለህ
በሚያስደንቅ ፍቅር ሁሌ ታልፈኛለህ
ፀጋህ ተትረፍርፎ በዛና ሰላሜ
እጅን ባፈ ጫንኩኝ ዙፋንህ ስር ቆሜ

እግሮቼ ሲሮጡ ወደ ሞት ሸለቆ
ይቅርታህ መለሰኝ ከነበልባል ነጥቆ
በጥበብ በትዕግሥት ታሳድገኛለህ
ወይንህን ስጠብቅ መች ትሰለቻለህ

ቀና ብዬ ሳየው ሰማይ ማደሪያህን
እጅግ አደንቃለሁ ግርማ ጌትነትህን
ዝቅ ስል ከቤቱ ስትሠራ አይሃለሁ
ከመገረም በቀር ሌላ ምን እላለሁ

ያልታሰበ ነገር አድርገህልኛል
በጠላቶቼ ፊት አሞግሰኸኛል
መስዋዕትን ብሰዋ የከንፈሬን ፍሬ
ለውለታህማ አልጠግብም ዘምሬ

ኪዳነ ምሕረት ለእኔ

ኪዳነ ምሕረት ለእኔ መመኪያዬ
ለችግሬ ደራሽ ነሽ መጠለያዬ
ህይወቴ ጎስቁሎ በነፍሴ ብዝልም
በምልጃሽ ታምኜ በኪዳንሽ ልቁም/2/

ዲያቢሎስ እቅዱን በልቤ ቢያገባ
ተገፍቼ ባጌጥ በሰናያር ካባ
የኃጥአን ደመወዝ እንዳይከፈለኝ
በሞት እንዳልጠፋ ድንግል ተለመኚኝ

እጅግ ምስኪን ሆኜ ለሰዎች ብታይም
ሞልቶ የተረፈ ጥሪት ባይኖረኝም
አንቺ ካለሽልኝ ኑሮዬ ሙሉ ነው
አፍሮ እያውቅምና የተማፀነሽ ሰው

ወገን ዘመድ የለኝ ፍፁም ከአንቺ በቀር
እኔን የሚረዳ በዓለም ስቸገር
አይዞህ በይኝና ደግፊኝ እናቴ
የፀጋ ልብስ ሁኚኝ ሲራቆት ህይወቴ

ነፍሴ እንድትቀደስ ከርኩሰት አምልጣ
ከሴኬም ልሰደድ ወደ ቤቴል ልውጣ
ገሪዛን ልበልሽ ድንግል መሸሻዬ
እዩአታም ልጅሽ መጣሁ አንቺን ብዬ

ኪዳነ ምሕረት

ኪዳነ ምሕረት ኪዳነ ኮነ
ምህረት አግኝቷል በአንቺ የታመነ/2/
በምድር በሰማይ ቃልኪዳንሽ ፀንቷል
ማርያም እያለ እስረኛው ተፈትቷል
በረከቱ ነሽ ክብሬም ሽልማቱ
ኪዳነ ምሕረት ነይልኝ እናቴ/2/
የራቁት ነፍሳት ወዮ አንቺ ቀርበዋል
እናትነትሽ አሁን ገብቷቸዋል
የጠላት ቁጣ አንዳችም አልሰራም
ሲልሽ ሰምተናል ፍጥረት ሁሉ ማርያም
አዎን ይልሻል እናታችን ማርያም
ላንቺ ያለኝን ፍቅር አንቺው ታውቂዋለሽ
ባለጋራዬን ትረቺልኛለሽ
በእምነት እወጣለሁ በልጅሽ አምኜ
ምን ይገጥመኛል ከአንቺ ጋር ሆኜ
ማን ያገኘኛል ካንቺ ጋር ሆኜ
ለኢትዮጵያ ልጆች ፍቅርን ለምኝልን
ለዓለም/ለአፍሪካ ሰዎች ሰላምን ማልጅልን
አንፈላለግ በፀብ ለዘላለም
ትቶት ይሄዳል ሁሉም ይህንን ዓለም/2/

ካልባረከኝ አለቅህም

ካልባረከኝ አለቅህም
አምላኬ ነህ ለዘላለም
ጌታዬ ነህ ለዘላለም
ሊነጋ ሲጀምር ሰማዩ ሲቀላ
ወዴት እሄዳለሁ ነፍሴ እንዲህ ዝላ
እያነከስኩ ሁሉ እከተልሃለሁ
እጅህን ዘርጋልኝ በረከት እሻለሁ/2/
ለብቻዬ ልቅር ፈቃድህ ከሆነ
ሌላውን አሌሻም ሕይወቴ ከዳነ
ሲሆን እስከ ንጋት ልታገልህና
ስደደኝ ጌታዬ ሕይወቴን ባርክና/2/
ታግዬ ስላደኩ ሞሌቶኝ በረከት
አየሁህ ጌታዬ ዛሬስ ፊት ለፊት
ድምጼን አሰምቼ አልኩኝ ጽንኤል
ስሜም ተለወጠ ተባለ እስራኤል/2/
የሞቷን ከተማ ሴኬምን ትቻለሁ
ጌታ እንደቃልህ ቤቴል ወጥቻለሁ
ሁሉን ስለምትወድ ስለምትራራ
ዓለምን አስረሳኝ ልኑር ካንተጋራ/2/

ካንተ የሆነው

ካንተ የሆነው መልካም ነው /2/
ሁሉን በጊዜው ስትሰራው
ካንተ የሆነው መልካም ነው
የኑሃሚን ርስት ሞአብ አይደለችም
ለምለሙን ቁጤማ ስቡን ብታበቅልም
በሙላት ወጥታችሁ ባዶ አትመለሱ
የእስራኤልን ቅዱስ ቃል ኪዳን አስታውሱ
ሩት አትለፊ የቦኤዝን እርሻ
ጌታ ፈቅዶልሻል የእንጀራሽን ድርሻ
ያለኝ ይበቃኛል ብለው ለሚያምኑት
እጅግ አትርፈዋል ሰላም በረከት
እስማኤል አይደለም የእግዚአብሔር ስጦታ
አብርሃም ሆይ ጽና ባለህበት ቦታ
ሰላም እና ፍቅር ይዞ የሚመጣው
ይስሐቅ ይወለዳል ቢዘገይም ጊዜው
ሰዶም ብታበቅል ለምለሙን ቁጤማ
ለእግዚአብሔር ልጆች ነች የማትስማማ
ድንጋይ እንኳን ቢመስል የአብርሃም ርስት
ጠግበናል ልጆቹ ማርና ወተት

ክንድህን እጠፍ

ክንድህን እጠፍ የሚልህ ማነው
ማዳንህን ተው የሚልህ ማነው
ቢከፋቸውም አሳዳጆቼ
እስካሁን አለሁ ባንተ ፀንቼ
ማለፌ ሲቀር ሕይወት ስሞላ
ሲያልፍ ከላዬ የሞቴ ጥላ
ለምን አዘኑ ሰዱቃውያኑ
ስለከፋቸው ላይቀር ማዳኑ
በባሕሩ ዳር ሕመሜን ትቼ
አልጋዬን ባዝል ድኜ በርትቼ
በሰንበት ዳነ ማረው ብላችሁ
ያደነህ ይሙት ለምን አላችሁ
ስምዖን ዞር በል ይከፈት በሩ
ይብቃ ሲምረኝ ማንጎራጎሩ
ኃጢአቴን ፈቅዶ ጌታ ከተወው
ምንህ ተጎዳ በእንባዬ ባጥበው
በግንባሬ ላይ ዐይኔን ቢሠራ
ቢደባልቀኝ ከሚያዩት ጋራ
ፊታችሁ በኃዘን ለምን ጠቆረ
ሁሉን ቻይ ጌታ ስለከበረ
አትዝጉት ደጁን እንመላለስ
የተወደደው በእኛ ላይ ይንገሥ
የምናቀርበው ለጌትነቱ
የከበረውን ይዘናል ሸቱ

ወረት የሌለው

ወረት የሌለው ወረት
አዛኝ የድሆች አባት
በሰማይ ሆነ በምድር
የለም እንደ እግዚአብሔር
እንደወደደን ትናንትና
ዛሬም ፍቅር ነው እንደገና
እርሱ አይለወጥ እንደ ሰው
ፍቅር ነው ወረት የሌለው
ከስኬታችን በስተጀርባ
ተከፍሎልናል የደም እንባ
አቻ በሌለው ፍቅሩ ገዝቶ
ሕይወትን ሰጠን እርሱ ሞቶ
ሰንሰለት የለም በእርሱ ዘንድ
ፍጹም አያውቅም ማስገደድ
በፍቅር ስቦ ይማርካል
መልካምነቱ ይለውጣል
ሲጨክኑበት ወደዳቸው
እየገደሉት አዳናቸው
በክፉ ፈንታ መልካም ሆነ
አንዱ ተሰቅሎ ሁሉ ዳነ
ከነኃጢአታችን የወደደን
ከነውራችን ጋር ያቀረበን
ሳይበቀለን ሳያጠፋን
ይኸው ይኖራል እያሰፋን

ወድሰኒ

ወድሰኒ ካልሸኘማ አመስግነኝ ካልሸኘማ
በደመና ውረጂና የእሳት አትሮንስ ይዘርጋና
ላመስግንሽ እንደገና
ባርኪኝ እንግዲህ አሐዱ ልበል
ከንፈሬን ዳሽው በልጅሽ መስቀል
በሐዋን ምክንያት የተዘጋው ገነት
ባንቺ ተከፍቷል ድንግል የእኛ እመቤት
የአሚናዳብ ሰረገላ የአሚናዳብ
ልቤ ተሻገረ ከልጅሽ ወደብ
እናት ዓለሜ መብረሪያዬ ክንፌ
የፍቅር ዋጋ የመስቀል ስር ትርፌ
እመሰክራለሁ እንደምወድሽ
ከፍ አድርጎሻል ፍጥረት እንዲያይሽ
የአሚናዳብ ...
የናቁሽ ሁሉ ከእግሮችሽ በታች
ይሰግዱልሻል ንግስት እያሉሽ
ታሪክ ሰርተዋል ልጆችሽ በዓለም
ጠላትን ወጉ እያሉ ማርያም
የአሚናዳብ ....
እሳት ሳይፈራ ይሰግዳል ጉልበቱ
ወደ ምስራቅ ነው ዘላለም መስኮቱ
የአንበሳ ጉድጓድ በእምነት ተደፈነ
በጥልቁ አይቀርም በልጅሽ ያመነ
የአሚናዳብ ሰረገላ የአሚናዳብ
ልቤ ተሳፈረ ከልጅሽ ወደብ

ውለታህን

ውለታህን እንዴት እረሳለሁ
ስጦታህን እንዴት እረሳለሁ
የኔ ጌታ ገና እዘምራለሁ
የኔ ጌታ ገና እወድሃለሁ

በጠላቴ ደንደሱ ላይ ቆመህ
ሚመካበት ጉልበቱን ሰባብረህ
አወጣኸኝ እጆቼን ይዘህ
ሁሉ ያንተ ነው ምኔን ልክፈልህ

ለዘላለም ልቤን ይደንቀኛል
ጉልበተኛው ፍቅርህ ያስነባኛል
መውደድህን ገለጥከው በሥራ
እኔም ቆምኩኝ ክብርህን ላወራ

ቀስቱ ታጥፎ ጦሩ ተሰባብሮ
ተመለሰ ደመኛዬ አፍሮ
አረጋግጠህ አወጅከው ሰላሜን
እውን አርገህ የልጅነት ህልሜን

ማረፊያዬ የሕይወት ውሃዬ
ሙላቱ ነህ ጥጋብ እርካታዬ
ለመለምኩኝ ወንዝ ዳር ተክለከኝ
አይበርደኝም ስምክን አልብሰኸኝ

ከትቢያ ላይ ከአፈር ላይ አንስተህ
ከሸለቆው ከጥልቁ ጎትተህ
ከፍ አረግኸኝ በስምህ ዝማሬ
እኔ አልሻም ላንተ ይሁን ክብሬ

ውለታሽ ጠርቶኝ

ውለታሽ ጠርቶኝ ከፊትሽ ቆምኩኝ
ድንግል ለክብርሽ ተንበረከኩኝ
ወደር የሌለው ማርኮኛል ፍቅርሽ
እናቴ ማርያም አምላያም የለሽ

የማያስርብ ነው የማያስጠማ
ፍቅርሽ የሚለበስ የብርሃን ሸማ
አልከበደኝም የዓለም መከራ
አንቺ ስላለሽ ከልጅሽ ጋራ

ትርጉም አግኝቷል ኑሮዬ ዛሬ
መውጫ መግቢያዬ ተከፍቷል በሬ
ጽዋዬ ሞልቶ ተትረፈረፈ
አዛኙ ልቤ በአንቺ አረፈ

የግብጽ ስደት እንባሽ አጠበኝ
ምልጃሽ ረድቶኝ ከእሳቱ ዳንኩኝ
አላቀረቅር አልደፋ አንገቴን
ማርያምን ይገፍ ድንግል እናቴን

ጌታን ባቀፉት መልካም እጆችሽ
ዳሰሰሽ ፈውሰሽኝ በረታሁ ልጅሽ
የሴም ምሳሌ ገመናን ሸፋኝ
ክሴን አጠፋሽው ሥራሽ አጽናናኝ

ውዴ በኔ ላይ

ውዴ በኔ ላይ ዓላማው ፍቅር ነው
ኃጢአቴን ሸሮ ሕይወቴን ታደገው
ባይቻለኝም መመለስ ውለታ
ልዘምርለት ይክበር የኔ ጌታ

ሳበው ከሰማይ ፍቅሬ ማረከው
ግርግም አደረ በረት ሳይሸተው
እርቃኑን ሆነ በጸጋ ሊያለብሰኝ
ሞተ ስለ እኔ ከእቅፉ መለሰኝ (2)

በንፁሕ ደሙ ዋጀኝ ጌታዬ
ሌጌዎን የለም ወድቋል ከላዬ
አውልቆ ጣለው ቀንበሬን ካንገቴ
በእርሱ ሆነልኝ እስር ሰንሰለቴ (2)

በልቤ ፅፎ አኖረው ቃሉን
ሰጠኝ ለልጁ አዲስ ኪዳኑን
ተቀዳደደ የጥል መጋረጃ
ጠረገው ደሙ የጽድቁን መሄጃ (2)

ስሙ ኢየሱስ ከኃጢአት የሚያድን
ዋለ በመስቀል ሞቴን ሊከድን
ውድቀቴን ሻረው አነሳኝ በክንዱ
ተጣብቄያለሁ ከሕይወት መንገዱ (2)

ሚካኤል ስለው

ሚካኤል ስለው ስሙን ስጠራ
የአምላኬ ብርሃን በላዬ በራ
አዛኝነው በእውነት ፍጹም አዛኝ
የሚጠብቀኝ የሚያጽናናኝ

ከአለቆች ጋራ ሕዝቡን የመራ
የሚመላለስ በእሳት ተራራ
ባህሩም ሸሸ ከማደሪያው
የጌታ መልአክ ሲያናውጸው
ዘንዶውን አሸንፏል - ስሙን በክብር ጽፏል

ከባዱ ጋራ ሜዳ ሆኖኛል
የወጎኒው መዝጊያም ተከፍቶልኛል
አልናወጥም ከቶም አልፈራ
የጌታ መልአክ ነው ከኔ ጋራ
ዘንዶውን አሸንፏል - ስሙን በክብር ጽፏል

ትዕቢተኛውን አሸንፎታል
ዲያብሎስ አሁን ዝናሩን ፈትቷል
ታላቅ ጸጥታ በሰማይ ሆነ
እግዚአብሔር ብቻ ስሙ ገነነ
ዘንዶውን አሸንፏል - ስሙን በክብር ጽፏል

ሚካኤል ሲቆም ፈጥኖ ደራሹ
የሚቃወሙን አጥብቀው ሸሹ
ታላቁ መልአክ ከፊት ቀደመ
ታሪክ ተሰራ ዕንባችን ቆመ
ዘንዶውን አሸንፏል - ስሙን በክብር ጽፏል

ዝናርህ በይቅርታ

ዝናርህ በይቅርታ
በቸርነት ተመልታ
አሳዳጁ ተመታ
ጽኑ እጅህ ተዘርግታ -- ተባረክ የኔ ጌታ
ሰባሪው ጌታ - ለብሰህ ይቅርታ
ትህትና ታጥቀህ - በፍቅር ዘምተህ
ብትሰቀልም - የለብህ ድካም
ጠላቴን ጣልከው - ሞቴን ገደልከው
ዐይኔ ቢያማትር - በተስፋ ሳይኖር
ይገለጥ ባንተ - ይስበክ ስላንተ
ካንተማ ሌላ - የለ ከለላ
የፀሐዩን ኃይል - ሞቶ ሚከልል
ብዙ ብኖርም - ብዙ አልተማርኩም
ዘመኔ ይጥራ - ካመት ቆጠራ
ባንተው ይታደስ - ባርከው ኢየሱስ
ባዲሱ ስሜ - ልስበክህ ቋሜ
ተቀጣጠለ - አንተን እያለ
ልቤ በእምነት - ልብስህን ዳስሶት
ትላንትን ላላይ - ቁሜ ዛሬ ላይ
ማልኩኝ በቀኜ - ልኖር ባዳኜ

የለም ሌላ ስም

የለም ሌላ ስም ሌላ መዳኛ
ከሰማይ በታች መተማመኛ
ከመቃብርም ከሞት በላይ ነው
ክርስቶስ ዛሬም ነገም ሕያው ነው
ግዙፉን የሞት ጓዳ የጠላትን ወረዳ
በርብራል በጮም ክንዱ ሊዋጀን በመውጮዱ
ያቆመው ኃይል የታለ በፍቅሩ ስር ያልዋለ
ነፃ ወጣን በጮሙ ተፈቷል ማኅተሙ
ግንበኞች ንቀውታል ከመሬት ጥለውታል
ለእኛ ግን ውብ መኖሪያ ሆኖናል መጋጠሚያ
በጽዮን ያገኘነው በፍቅር ምናመልከው
አለት ነው የከበረ ያመነው መቼ አፈረ
ቢበዛብን ከልካዩ ከሳሽ እና አባዩ
ይህን ስም ሳንጠራ አንወርድም ከተራራ
ቆመናል በብርታቱ ድነናል በናዝሬቱ
ከስሞች በላይ ያለው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው
ምናውቀውን መናገር ያየነውን መመስከር
ይሄ ነው የእኛ ጥበብ ለሞተልን ማሸብሸብ
ዮርዳኖስ መኮብለሉ ኤርትራ መከፈሉ
ሁሉም ነገር የሆነው በሚችል በእርሱ ስም ነው

የሉም ከሳሾቼ

የሉም ከሳሾቼ እነሱም ተከሰው
ገመናዬን ሸፋኝ ከቶ እንዳንተ ማን ነው
ገና ሳልፈፅመው ኃጢአቴን ለሚያውቀው
ይነግሩት ጀመረ እንዳላዋቂ ሰው
ወድቀው ተማጽኑት በሞት እንድመታ
መስሏቸው ሞኝነት የፍቅሩ ዝምታ/2/
እያለ ተጋድሞ ምሰሶ በዓይናቸው
የኔን ጉድፍ ማየት እንዴት ተቻላቸው
በፈረዱበት ፍርድ እነርሱም ወደቁ
በኔ ላይ በመፍረድ ከቶ መች ጸደቁ/2/
በሰፈረው መጠን ከሳሽ ይሰፈራል
ከቁጣው እሳት ፊት መች ማምለጥ ይቻላል
የሁላችን ዋጋ በእጁ ላይ እያለን
በመንግሥቱ ስልጣን ማን ፈራጅ አረገን/2/
መዝገቡ በእጁ ነው አይመረመርም
ኃጢአቴን እንዲያውቀው ነጋሪ ይፈልግም
ከሳሾች እመኑ ጌታዬ ምሮኛል
እግዚአብሔር ሰው ነግሮት መቼ ፈርዶ ያውቃል/2/

የመስቀሉ ፍቅር

የመስቀሉ ፍቅር ቢገባን (2)
እመቤታችንን እንወዳታለን
የመስቀሉ ፍቅር የገባቸው (2)
እመቤታችን አለች ከጎናቸው

ነይ ነይ እምዬ ማርያም ነይ ነይ ቤዛዊት ዓለም
የክርስቶስ እናት የመድኃኒዓለም

አባሕርያቆስ አባታችን የመስቀሉ ፍቅር ቢገባው
ልቤ አፈለቀ አለ መልካም ነገር
ከእመቤቴ ጋር ሲነጋገር
ከድንግል ማርያም ጋር ሲነጋገር - ነይ ነይ ...

ቤተልሔም ስሄድ አይሻለሁ
ቀራኒዮም ስሄድ አይሻለሁ
ፍጹም አትለይም ከልጅሽ
የአንቺስ ልዩ ነው ፍቅርሽ (2) ... ነይ ነይ ...

የመናኙ ጸሎት ልዩ እጣን
የዋሻው ሻማ ነሽ እመ ብርሃን
መዓዛሽ ሸተተኝ ከግሸን
ትናፍቂኛለሽ ምን ልሁን
ትርቢኝማለሽ ምን ልሁን

የማይሸረሸር አለቴ

የማይሸረሸር አለቴ የማይናጋ መሠረቴ
ኢየሱስ ክርስቶስ ሞገሴ አንተነህ የፅድቅ ልብሴ

ቀራንዮ ላይ የቆመ

በፍቅር የተተለመ

ከፊቴ ተነሰነሰ

ደምህ ሕይወቴን ወረሰ

እፎይ ልበል ልዘምር

ሆነኸኛል ጌታ ክብር (2)

የሲና ምድር ህብስቴ
የተከተልከኝ አለቴ
መርገሜን ሰብሮ አለፈ
ሰላምህ ውስጤ ሳረፈ ... እፎይ ልበል ...

የማትደፈር ክልሌ

የድል አርማዬ አክሊሌ

ዓለምን ማሸነፊያዬ

አንተ ነህ ክንዴ ጌታዬ ... እፎይ ልበል ...

መዳፎችህን አይቼ
በእንባ ረጠቡ ጉንጮቼ
ትዝታዬ ነው ዘወትር
መስቀል ላይ ያየሁት ፍቅር ... እፎይ ልበል ...

የማይጠፋ ፋኖስ

የማይጠፋ ፋኖስ ለቅዱሳን የሚያበራ /2/
የእግዚአብሔር ልጅ የድንግል ማርያም ልጅ
ኢየሱስ ሆነ ከእኛ ጋራ/2/

ተጠቅልሎ ሄደ ጨለማ ከፊቱ

ሞትን አስደንግጧል ታላቅ ጌትነቱ

ምድር ተቀደሰች በከበረ ስሙ

ከመስቀሉ ወጣ ፈሰሰ ሰላሙ /2/

አምደ ብርሃን ነው ዓለምን ያበራ
የጽድቅን ደምግባት ውበትን የሠራ
እንደ ሰንፔር ድንጋይ ያበራል በልቤ
ናዝራዊው ኢየሱስ እውቀቴ ጥበቤ /2/

አይነጋም ያሉት ሌት ይኸው ዛሬ ነጋ

በጨለማ አይኖርም አንተን የተጠጋ

የባልቴቷ ዳኛ ምርኮህ አደረሰኝ

በሚያስደንቅ ቀለም መዳፍህ ላይ ጻፍከኝ /2/

የፍርድ ቀናችንን ለሚጠባበቁ
ታሳያቸዋለህ እውነቱን እንዲያውቁ
ወህኒው ባዶ ሆነ ጴጥሮስም ተፈታ
የእስራኤል ታዳጊ ልዩ እኮነህ ጌታ /2/

የተወደደ ቀን

የተወደደ ቀን የተወደደ አመት
ወደ አባቴ ፍቅር/መቅደስ የተመለስኩበት
አንባር ቀለበትን የተሸለምኩበት ... የተወደደ አመት
አምሽቶ የመጣ አይገባም አትበሉ
አባክኖ የመጣ አይገባም አትበሉ
ፍቅር ስለሆነ እግዚአብሔር ለሁሉ
ልጅ ቤቱን ይወርሳል እንደተስፋ ቃሉ
ከናዝሬት መልካም ሰው አይወጣም እያሉ
ፊልጶስ ናትናኤል ይነጋገራሉ
አድርጎታልና ውሃውን ወይን
ዛሬም ለውጦታል ወስዶታል ልቤን
እኔ ነኝ አላማው እኔ ነኝ አሳቡ
አባቴ ደግ ነው የሚራራ ልቡ
ዘጠና ዘጠኙ ታምነውት እያለ
አንዱን ይፈልጋል ወዴት ነው እያለ
ሁሉን አይቻለሁ ሁሉን መርምሬያለሁ
አለም ካንተ ሌላ እንደ ሌለ አውቃለሁ
እንደማይለወጥ አባትነትህ ወዳጅነትህ
ጠፍቼ ስመጣ አየሁት ልጅህ

የት ሄዳለሁ

የት እሄዳለሁ ጌታ የት ሄዳለሁ
አምላኬ ከፊትህ የት ደርሳለሁ
እንደንስር ወደላይ ብመጥቅም
በዚያም አለህ ከእጅህ አላመልጥም
ብኮበልል ብሸሽም እንኳን ከፊትህ
መች ቀነስ መቼሽ ተለየኝ ምህረትህ
አወጣኽኝ በቸርነትህ ከሸለቆ
ሰላሜ ነህ መኖር መልካም ነው አንተን አውቆ
ወሰን ገደብ የለውም ጌታ ላንተ ድንበር
መረገጫ ናትና ለእግርህ ይቺ ምድር
ማንም ሸሽቶ ማምለጥ አይችልም ከፊትህ
ይህን ዓለም አበጃጅተዋል እጆችህ
ወደኽኛል በማይሞት ፍቅርህ ለዘላለም
ካንተ ወዲያ በረከት ሰላም ከቶ የለም
አርፏል ዛሬ ተቅበዝባዥ ልጅህ ባንተ ጥላ
ስደት ይብቃኝ አልመለስም ወደ ኋላ
ጉም ጨለማ ፍዑም አይችልም ሊጋርድህ
አልፈኽኝ ነው አንተ ልጅህን በመውደድህ
ስንቴ ማርከኝ ስንቴስ አለፍከኝ በይቅርታ
ክበርልኝ መድኃኒቴ ሆይ የኔ ጌታ

የትናንትና ማንነቴን

የትናንትና ማንነቴን
ያደፈው ታሪክ መዛግብቴን
እዩት ጌታዬ ሲያድስልኝ
ተስፋ ሲሞላልኝ ሲራራልኝ

ብዙ መዝገብ አለው የፍቅር የምህረት
ኃጢአቴ ኃይል የለው ወድቋል ዙፋኑ ፊት
ንስሐ ስገባ አዲስ መዝገብ መዝዞ
ጽድቁን ይፅፈዋል በደሌን ሰርዞ/2/

በፍቅር የፈሰሰው ያ ደም ለማን ሆኖ
እንዴት ዝም ይለኛል ስጠፋ ጨክኖ
ምህረቱ ይበልጣል ከእጆቼ በደል
ጌታዬ ፍቅር ነው አልገባም ሲኦል/2/

ባይፈልገኝ ኖሮ ባይወደኝ ጌታዬ
አይቀርበኝም ነበር ስጠራው በእንባዬ
ፀሐይ ሳይበግረው በቅትር ይመጣል
እንስራዬን ጥሎ ፍቅር ያሸክመኛል/2/

ወድቆ ስላነሳኝ ንጹህ ደሙን ከፍሎ
ቁስሌን ስለሻረው በመከራ ቆስሎ
ብስት ብበድልም በለበስኩት ሥጋ
ሳለቅስ ሰምቶኛል ደጃፉን ሳይዘጋ/2/

የአንደበቴ ጣፋጭ ውዳሴ

የአንደበቴ ጣፋጭ ውዳሴ
የምፅናናብሽ ታላ ለነፍሴ
ከመቅደስሽ ፍቅርን ተምሬ
ማርያም (2) ይላል ከንፈሬ

ልመናዬን ሰምተሻል
በረድዔት ቀርበሻል
በፍቅርሽ ተሸልሜ
አረፍኩኝ ከሸክሜ (2)

ቃሌ ነው በእንተ ስሚ
ተማፅኖዬን ሳሰማ
ከዙፋኑ ቀኝ ሆነሽ
ድንግል ታስምሪኛለሽ (2)

ማግኘት ማጣት አይደለም
ልመናዬ በዓለም
አድይኝ ማስተዋሉን
እንድረዳው መስቀሉን (2)

አይመራኝም በትሬ
ድንግል ቆመሽ ከበሬ
ምርኩዜ ብዬሻለሁ
አንቺን እደገፋለሁ (2)

የአዳነኝን አውቀዋለሁ

የአዳነኝን አውቀዋለሁ የሞተልኝ ኢየሱስ ነው
ስሌለኝ የሚከፍለው ስጦታዬ ምስጋና ነው
ጨለማዬ አስወግዶ ያበራልኝን አውቃለሁ
ሙሉ ሰው ነኝ ከእንግዲህስ ስከተለው እኖራለሁ
የብርሃኔ ልዩ ውበት ፊት ለፊቴ ቆሞ አየሁት
ፍቅሩ ማርኮኝ በመቅደሱ ሰገድኩለት አመለኩት
ላመሰግነው (3) ፍቅሩ የማያልቅ ነው
አሳደረኝ በእቅፉ መጠውለጌን አለምልሞ
በመስቀል ላይ ተሰቀለ ዳንኩኝ እኔ እርሱ ታሞ
በማይዝለው ክንዶቹ ላይ እኔን በክብር እያኖረ
እንዲመቸኝ ዝቅ ብሎ በበረት ውስጥ እርሱ አደረ ...
ቅኔ ባፈስ ምን ይደንቃል ደሙን በመስቀል አፍስሶ
ስለልጁ መዳን ብሎ ነፍሱን ሳይቀር ለኔ ክሶ
ፍቅሬ ይዞት ከፀባኦት በትህትና መጥቶ ወርዶ
ተቀደስኩኝ በነጩ በግ ቀራንዮ ጌታ ታርዶ ...
አክሊለ ሶክ አጠለቀ ግርማ ክብሩን ሁሉን ትቶ
አሻገረኝ ወደ ክብሬ በቅዱስ ደም እኔን ዋጅቶ
አጎንብሶ ቀና አረገኝ ፊቴን በጽድቅ እያበራ
እኖራለሁ ለዘላለም ካከበረኝ ጌታ ጋራ ...

የክብርህ ጸዳል

የክብርህ ጸዳል ፊቴን መላ
ስላሳረፍከኝ ባንተ ጥላ
ጌታ ፍቅርህን ተመልክቻለሁ
እስከ ዘላለም አመልክሀለው
ባለ ማዕረግ ተሰኘሁ በትከሻህ አርፌ
ማዕበልና ሞገዱን በምህረትህ ቀዝፌ
አንተህ ነህ ከፍታዬ - የሞትክልኝ ጌታዬ
ትምክህትና ጉልበቴ - ኢየሱስ መድኃኒቴ
በለምለም አሳደርከኝ በዕረፍት ውሃ መራኸኝ
በገናዬን ሳነሣ በመንፈስህ ቃኘኸኝ
የልጅነት ጽናቴ - የእረኝነት ብርታቴ
አሸበሸበ ክንዴ - ላከበረኝ ለውዴ
በዮርዳኖስ ፊት ቆሜ እጆቼን አነሣለሁ
ባህሩን በበትሬ በስምህ እከፍላለሁ
ይኸው ጥልቁን አልፌ - ከሞት መዳፍ ተርፌ
በርስቴ ላይ ቆሜያለሁ - ያፌን ፍሬ ሰዋለሁ
ምልክትህ በፊቴ እንዳይጠፋ ተሣለ
ፍቅርህና መስቀልህ በልቤ ተተከለ
ዐይኖቼ ዕንባን ቢዘሩ - ተደፍቼ ከበሩ
ሌላ አይደለም ምክንያቴ - ተገሎልኝ ነው ሞቴ

የወደደኝ ጌታ

የወደደኝ ጌታ ምን አድርጌለት ነው
ብዘምርለትም ያንስበታል ይኸው
ከውድቀቴ አንስተህ ድካሜን ያገዘከኝ
ሰባራውን ድልድይ ገጥመህ ያሳለፍከኝ

በኢያሪኮ መንገድ ስለምን ቁጭ ብዬ
ብርሃን እጅግ ናፍቆኝ ከሰው ተገልዬ
የብርሃን ጌታ ወደ እኔ መጣና
ዓይኔን አበራልኝ በእጁ ዳሰሰና

ለብዙ ዘመናት አልጋ ላይ ተኝቼ
የሚረዳኝ አጣሁ ጠሉኝ ዘመዶቼ
የእኔ ጌታ አምላኬ ወደ እኔ መጣና
አልጋህን ተሸክም አለኝ ፈወሰና

አስራ ሁለት ዓመት ደም እየፈሰሰኝ
ምራቅ እየተፉ ሁሉም ቢያንቋሸሹኝ
የጌታዬን ልብሱን ጫፉን ብዳስሰው
ኃይልም ከእርሱ ወጣ ደሜን ቀጥ አረገው

ሰካራም ዘማዊ ወንበዴ ነበርኩኝ
ያመጸኞች መሪ ደምን ያፈሰስኩኝ
ዛሬ ግን ታሪኬን ጌታ ቀይሮታል
ለኃያሉ ጌታ ምስጋና ይገባል

የያሬድ ውብ ዜማ

የያሬድ ውብ ዜማ ድንግል እመቤቴ ስጦታዬ ነሽ
በምን አንደበቴ እንዴትስ ባለ ቃል ማርያም ልበልሽ

ምድርና ሰማዩ ታምርሽን ይንገሩ
ፍጥረታት በሙሉ ስላንቺ ይመስክሩ
ተነግሮ የማያልቅ ድንቅ ነው ሥራሽ
ድንግል ሆይ እናቴ አምሳያም የለሽ
ማርያም ድንግል ረዳቴ
የምትደርሽልኝ ነይ ስልሽ በጭንቀቴ
ተዓምርሽን በዓይኔ አይቻለሁ
ጽዮን ሆይ ስልሽ ድንግል ሆይ እጠግባለሁ

የእግዚአብሔር ጥበቡ ባንቺ ተገለጠ
የአዳም ዘር በሙሉ ከሞት አመለጠ
የመዳን ምክንያት ማርያም አንቺ ነሽ
ለፍጥረታት ሁሉ መሰላል የሆንሽ
ነገን ባላውቅ እኔንም ቢያስፈራኝም
አንቺ ካለሽኝ በፍጹም አልወድቅም
በፊትሽ እንድቆም ለምስጋና
ማርያም ልበልሽ በትህትና

ትውልድ በሙሉ ለምስጋና ይቁም
ባንቺ ስለሆነ የቀረልን መርገም
አዳም ከነልጁ በሰማይ በምድር
ማርያም ማርያም ይበል ተዓምርሽን ይናገር
ጨለማው ከፊቴ ተገፈፈ
ማርያም በምልጃሽ ልቤ አረፈ
ከጎኔ ነሽ ስልሽ እጽናናለሁ
እሳት ገደሉን ሁሉን አልፈዋለሁ

የግብጽን ከተሞች

የግብጽን ከተሞች ትተን ወጥተን
በበረሃ ስንሄድ ምድርን ሞልተን
ጫማና ልብሳችን አላለቀም
እርሱ እየቀደመ መድኃኒዓለም

ታላቁን ቀይ ባህር ሳንሻገር
አስጨንቆን ነበር ብዙ ነገር
ግን ሁሉም ቀለለ ከፊታችን
እርሱ እየቀደም አምላካችን

ከአለት ላይ ውሃ ጠጥተናል
የነሐሱም እባብ ፈውሶናል
የምድር ሰልፈኞች ቢነሱብን
ለሞት አሳልፎ መቼ ሰጠን

እስራኤል በክብር ፊቱን ሞልቷል
ሰባቱም ደመና ጋርደውታል
ነፃ ስለወጣ ክሱ ታጥፎ
ማንስ ይነካዋል ክንዱን አልፎ

ዓለም ብትገፋን ብትጨክን
አንተ ግን እንደሰው መቼ ጣልከን
ከእኛ ጋር ተዋግተህ ድል ለብሰናል
የበፍታ ኤፋዱም አምሮብናል

የጽድቅ በር ነሽ

የጽድቅ በር ነሽ የሙሴ ጽላት
አክሉለ ምዕራገ ጸሎት
የጌታዬ እናት ንጹሕ አክሉሊችን
ሐመልማለ ሲና እመቤታችን
እመቤታችን ለእኛ ምርኩዝ ነሽ
“ ከለሊ ሆንሽን
“ የእሳት ሙዳይ
“ እሳት ታቀፈሽ
“ በብርሃን ተከበሽ
“ ወርቅ ለብሰሽ
“ ከሴቶች ሁሉ
“ አብ መረጠሽ
እመቤታችን ድንግል ሆይ ልጆችሽ
“ ዘወትር ይጠሩሻል
“ ስምሽን ለልጅ ልጅ
“ ያሳስቡልሻል
“ በተሰጠሽ ጸጋ
“ በአማሊጅነትሽ
“ ምሕረትን አሰጭን
“ ከመሐሪው ልጅሽ
እመቤታችን ያልታረሰች እርሻ
“ ዘር ያልተዘራባት
“ የሕይወትን ፍሬ
“ ሰጠችን የኛ እናት
“ የተሰዋው መሲህ
“ እናቱን ወደዳት
“ በቀኙ ቆማለች
“ ድንግል እመቤት ናት

የፈራ ይመለስ

የፈራ ይመለስ ከገልዓድ ተራራ
እኛ ግን ቆመናል በፅናት ከጌድዮን ጋራ
በሦስት መቶ እንስራ ማይጠፋ ችቦ ለኩሰናል
የእግዚአብሔር እሳት ኃይላችን ጉልበታችን ሆኗል
ወደፊት እንጂ አንልም ወደ ኋላ
ሞፈር ተይዞ አይጠበቅም ጥላ
እንሮጣለን ስሙን ተሸክመን
ቃል ኪዳን አለን ሽንፈት ላያገኘን
ለድል ፍጠኑ ለወሬ ጊዜ የለንም
መኸሩ በዝቷል ሠራተኞች ቢያንሱንም
ነፍስ አልቀረለት ጠላታችን ደንግጧል
ቀፎው ተነክቶ ንቡ ክዳን ገልብጧል
ከማታ ተኩላ ጭካኔያቸው ቢገን
ከነብር ዝላይ ፈረሳቸው ቢፈጥን
እሣት እንዳየው የሸማኔ ፈትል
የአሕዛብ ጉልበት በስሙ ይቀልጣል
ብዛት አይሠራም የሚያስፈልገው ጥራት ነው
አንገቱን ደፍቶ የሚጠጣ ውሻ ነው
ቀና ብለናል ነጋሪቱ ሲመታ
በግራችን ኩቴ ጅማታቸው ተፈታ
ባሕር ሰልፍ ይዞ አጨበጨበልን
በውሃ መዝሙር በመካከል አለፍን
ገና ይሆናል ያልታየ ያልተሰማ
ሥለነገሠ አምላካችን በግርማ

የፍቅር እናት የሰላም

የፍቅር እናት የሰላም (2)
ይናፍቀኛል ስምሽን ሳልጠራው ስቀር ማርያም
በህይወቴ ውስጥ በኑሮዬ
ቅደሚ ከፊት ከኋላዬ
ተደላደለ ልቤ
አንቺ አለሽና ካጠገቤ
ምኞቴም ይስመር ድብቅ ህልሜ
ልለፍ ወጀቡን ተቋቁሜ
የጌታዬ እናት ነሽ
ኃይልን ያደርጋል ጸሎትሽ
እንዴት እቀራለሁ ከመንገድ
አደራ እናቴ አስቢኝ
ለሚያስጨንቀኝ ጠላት
ለሚያሳድደኝ አትስጭኝ
ትናንትም ዛሬም አመስጋኝ ነኝ
የለም ለነገ የሚያስፈራኝ
ሜዳ ይሆናል ተራራ
ልጅሽ ስላለ ከእኔ ጋራ

ያለ አንተ ክብር የለኝም

ያለ አንተ ክብር የለኝም
ላምልክህ ለዘለዓለም
ተባረክ ቸር ጌታዬ
ምንጭ ነህ ለደስታዬ (2)

የልቤን ጥማት ተካህ በሙላት
ላክብር ስምህን ላውራ ዝናህን
ሞገስ ግርማዬ ሀር ሽማዬ
አፍሯል ከሳሼ አንተን ለብሼ
ተባረክ ውዴ እውነት መንገዴ (2)

ልውጣ ማልጀ ተከፍቶ ደጀ
ወደ ናፍቆቴ አቅንቷል ፊቴ
ድካሜን ጥዬ እልፍ ብዬ
አግኝቼሃለሁ መች እለቅሃለሁ
ተባረክ ውዴ እውነት መንገዴ (2

ዘውዴን ላንሳልህ እጅ እንድነሳህ
ክብርስ ለአንተ ነው ሞቴን ለሞትከው
አልደራደር ባንተማ ነገር
ብኖር ብሞትም አንተን አልክድም
ተባረክ ውዴ እውነት መንገዴ (2

ብቆም ሰገነት በቤተ መንግሥት
አለቴ አንተ ነህ የምመካብህ
የነፍሴን አውታር ቃኝተህ በፍቅር
ባታሰልፈኝ ማን ሊያስታውሰኝ
ተባረክ ውዴ እውነት መንገዴ (2

አንደበቴም ያውጣ

አንደበቴም ያውጣ የምስጋና ቅኔ
የአምላኬን ማዳን አይቻለሁ በዐይኔ
በገባኦን ሰማይ ፀሐይን ያቆመ
ዛሬም ጎብኝቶኛል እየደጋገመ

ወጥመድ ተሰበረ እኔም አመለጥኩኝ
ከኃጢአት ፍላጻ ከሞት አፍ ተረፍኩኝ
የአናብስቱን አፍ በኃይሉ የዘጋ
የዳንኤል አምላክ ይኖራል ከእኔ ጋር

በዳዊት ምስጋና በያሬድ ዝማሬ
ከቅዱሳን ጋር ልዘምር አብሬ
እርሱን ሳመሰግን ሜልኮል ብትስቅብኝ
ለጌታዬ ክብር እዘምራለሁኝ

አስፈሪው ነበልባል እሳቱ ቢነድም
ለጣኦት እንድንሰግድ ነገስታት ቢያውጁም
ሁሉም ቢተወኝም ቢጠላኝም ዓለም
ጽናት ይሆነኛል ጌታ መድኃኒዓለም

ለማርያም

ለማርያም ለማርያም
እንዘምራለን ለዘለዓለም

እጅግ የበዛ ነው ለዘለዓለም ያለኝ ፍቅር ለዘለዓለም
አይወሰንም " አይነገርም "
በእርሷ ደስ ይለኛል " ሀሴት አደርጋለሁ "
ስሟን እየጠራሁ እዘምራለሁ

የተዘጋች ደጅ ለዘለዓለም ሕዝቅኤል ብሏል ለዘለዓለም
ንጽህት ናት በእውነት " በፍጹም ድንግል "
አብነት አርገን " እኛም እርሱን "
በፍጹም ፍቅር እንዘምራለን

የዋህት እርግብ ለዘለዓለም ሰላም አብሳሪ ለዘለዓለም
የጨለማ ሕይወቴን " ብርሃኔን አብሪ "
እማጸንሻለሁ " ድንግል ለነፍሴ "
አደራ ድንግል አንቺ ነሽ ዋሴ

ነይ ነይ ስላት ለዘለዓለም ቀንና ሌሊት ለዘለዓለም
አትለየኝም " ለእኔስ ቅርቤ ናት "
ፅጹብ ፅጹብ ብለው " አመሰገኗት "
ክብሯን ሊገልጹ ቢያጥራቸው ቃላት

ትህትናሽ ግሩም ነው

ትህትናሽ ግሩም ነው ደግነትሽም
እናቱ ሆነሻል ለመድኃኒዓለም

ንጽህት ስለሆንሽ እመቤቴ/2 እንከን የሌለብሽ እመቤቴ/2
የፍጥረታት ጌታ " ባንቺ ያደረብሽ "
የድንግል መመረጥ " ዜናዋ አስገረመኝ "
እሳቱን ታቀፈች " የማይቻለውን "

ምርኩዜ ልበልሽ እመቤቴ/2 ጥላ ከለላዬ እመቤቴ/2
ጋሻዬ ነሽ አንቺስ " ለእኔ መመኪያዬ "
በዓለም እንዳልጠፋ " ሕይወቴ መሮብኝ "
እንደወይን አጣፍጪው " ድንግል ድረሺልኝ "

የግሽኗ ንግሥት እመቤቴ የአምላክ እናት እመቤቴ/2
ሆና ተሰጥታለች " የሚመኩባት "
በልቼ ጠጥቼ " የምረካብሽ "
ጎጆ ማረፊያዬ " ማርያም አንቺው ነሽ "

ያስከበርከኝ

ያስከበርከኝ ክበርልኝ
ከፍ ያረከኝ ከፍ በልልኝ
ልቤ አቅንቷል ወደ ዙፋንህ
ጠዋት ማታ ሊያገለግልህ

ሞገስ ስለሆንከኝ ጉልበትና ክብሬ
ባንተ ያገኘሁትን አልዘልቀው ዘርዝሬ
ቤትህ አድጌአለሁ ስጠይቅ ስሰማ
ከፍ ብያለሁኝ ስምህ ሆኖኝ ማማ

ሳትሰስት ሳትቆጥብ ፀጋን ሰጥተኸኛል
የቀረብኝ የለም ፍቅርህ በዝቶልኛል
የልቤ ማጎደር ፅፎታል ስራህን
መቼም አትጥልም ያገለገለህን

እድፍ የሌለብህ ስህተት የማያውቅህ
እውነት የከበበው ፍርድና ችሎትህ
መልክና ቁመና በአንተ ፊት ባዶ ነው
ልቡናን አይተህ ነው የምትሾመው ምትሸረው

በኔ ሥራ ሳይሆን ጌታ በአንተ ፀጋ
ስለወደድከኝ ነው እንዲሁ ያለዋጋ
መቆሜ መኖሬ በፍቅርህ ነውና
ታሪኬ ነህ አንተ የኔ ሁለንተና

ያድናል እግዚአብሔር

ያድናል እግዚአብሔር ከመከራ
ጨለማውን በኃይሉ እያበራ
የገዳዩን ቀስቶች የሰበረ
ማነው እንደ እግዚአብሔር የከበረ

ሌሊቱን ለድል ብርሃን እያደረገ
በምድረበዳ ሕዝቡን የታደገ
በሙሴ በትረ ተአምራት የሰራ
አሸናፊ ነው ከብሩ የሚያስፈራ

ሞቱ ፈጠነ ጠላት ፍጻሜው
ከተራራ ላይ ጌታ ሲመታው
ላይመጣ ማለ ዳግመኛ ወደህዝቡ
ሽንፈት ለበሰ ሳይሞላ ሃሳቡ

ይበራል በክንፉ

ይበራል በክንፉ ምልጃውም ፈጣን ነው
የአምላክ ስም አለበት ስሙም ሚካኤል ነው
ያሳደገኝ መልአክ ዛሬም ከኔ ጋር ነው
ከፊቴ ቀደመ ደመናን ዘርግቶ
እንዳልደናቀፍ ጉድጓዶቼን ሞልቶ
ዛሬ ባለሁበት ብርቱ ጉልበት ሆነኝ
ሰው ለመባል በቃሁ ሚካኤል ደገፈኝ
በእናቴ እቅፍ ገብቼ መቅደሱ
አለሁ እስከዛሬ አጥሮኝ በመንፈሱ
የሕይወቴን ሰልፎች አለፍኩ ከርሱ ጋራ
ተጽፏል በልቤ የሚካኤል ሥራ
በዙሪያዬ ተክሎ የእሳት ምሰሶውን
ጽድቅ እየመገበ አሳደገኝ ልጁን
የአምላኬን ምስጋና ዘወትር እያስጠናኝ
እርሱ ነው ሚካኤል በመዝሙር የሞላኝ
ፊት ለፊት ተተክሎ ከታናሿ መንደር
ይሰማኝ ነበረ ቅኔው ሲደረደር
ይወስደኛል ደጁ እየቀሰቀሰ
ታላቁን በረከት በውስጤ አፈሰሰ
ሴኬምን እንዳላይ ክንፎቹን ጋረደ
መራኝ ወደ ሕይወት መዳኔን ወደደ
የሞአብን ቋንቋ ከአፌ ላይ አጥፍቶ
በፀጋው ቃል ቃኘኝ በበረከት ሞልቶ

ይታዘዛት ነበር

ይታዘዛት ነበር ያገለግላት
ኢየሱስ እናቱን በቀን በሌሊት/2/
በነፋሳት አስሮ በደመና ጭኖ
ያመጣላት ነበር እንጨት ከዱር ለቅሞ/2/
በትንሽ ትንሹ እንደ ሰው አደገ
የጠፋውን መንጋ መጣ እየፈለገ
ያልቆመ ሰው የለም በፍቅሩ ያልተሰራ
አማኑኤል በሉ እግዚአብሔር ሆነ ከእኛ ጋር
ጨረር ላይ ሲራመድ ማን እርሱን ይመስላል
በጭቃ እየሰራ አእዋፍን ያበራል
የሚያስገርም ሕፃን የሚያስገርም ጌታ
ድንቅ መካር ኃያል እረኛችን ይወደስ በእልልታ
ሥጋችንን ነሳ ሲሆን ሰማያዊ
የይሁዳ አንበሳ ቤተልሔማዊ
የእግዚአብሔር ልጅ እንጂ የዮሴፍ አይደለም
እንመሰክራለን ይህን እውነት ዛሬም ለዘላለም
በታላቁ መጽሐፍ ተጽፎ የሌለ
ጌታ ያደረገው ብዙ ተአምር አለ
እጅግ ብዙ ድንቆች ማለቂያ የሌለው
ሁሉን የፈጸመ እንደ ጌታ እንደ ኢየሱስ ማነው

ይነጋል ባንተ

ይነጋል ባንተ ሌሊቱ
ታምነው በፍቅር ለበረቱ (2)
ያልፋል ጨለማው በጊዜው
እግዚአብሔር አንተ ስታዘው (2)

ጎልማሳውን ሰው ያድሰዋል
ጉልበቱን ፈቶ ያቆመዋል
ዛሬም ለሚያምኑት በምህረቱ
ያው ነው እግዚአብሔር ቸርነቱ (2)

ለመካኒቱ ልጅ ይሰጣል
ጌታ ታሪኩን ይለውጣል
የሞትን አዋጅ እየሻረ
ሕዝቡን በዘመን አከበረ (2)

የዓሳ አንበሪው ሆድ ይከፈታል
ዮናስ ከጥፋት ይመለሳል
ተስፋ ነው ጌታ ለባሪያው
መቼም አይፈቅድም ሊረሳው (2)

ክፉ ቀን ቀንበር ቢሆንበት
ጌታ ታማኝ ነው ሊደርስለት
የላላው ጉልበት ይበረታል
ያመነ ሁሉ ያሸንፋል (2)

ይናፍቃል

ይናፍቃል ልቤ በብዙ
ሊገዛልህ ሊታዘዝህ ሊያገለግልህ

ኃጢአትም እንደ ሕግ ውስጤን ሲገዛኝ
በፍቅርህ ስታየኝ አነባለሁኝ
በውስጤ ይፈሳል ፍቅርህ እንደ ዘይት
እንዴት ልርሳው ቸርነትህ ከተለወጥኩበት

ለፍርድ አትቸኩልም በልጆችህ ላይ
ልቡናዬን ማርከሽዋል ከምንም በላይ
የእኔ አይደለምና የምድር ሰውነቱ
ላገልግልህ ባርያህ ሆኜ ቸር ነህ መድኃኒቱ

አመፅን ለመሥራት ስፈጥን ከመንገድ
ከአጠገቤ አይሃለሁ እብደቴን ስታግድ
እንደምን ወደድከኝ ምን እከፍልሃለሁ
ከሰው ምንም የማትወስድ መሆንህን አውቃለሁ

እንግዳ ነህ ለእኔ አዲስ ነህ ለቤቱ
ትልቁ ዘመዴ ለብቸኝነቱ
ዳር ሆነህ አታየኝ ሐዘን ሲገርፈኝ
ለጥያቄዎቼ መልስ የምትሆነኝ

ይኩነኒ

ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ (2)
አለች የኛ እናት በትህትና በሥጋም በነፍስም ንፅሕት ናትና
አለች የኛ እናት በትህትና ድንግል በክልኤ ንፅሕት ናትና
የአዳም ቃል ኪዳን መፈፀሚያው ሲደርስ
ላከው ገብርኤልን ወደ ቤተ መቅደስ
በእግዚአብሔር ጎሊና ተስላ የነበረች
ከሰማይ የመጣ ቃሉን ተቀበለች
ዳግሚት ሰማይ አርያም ሆነች
ይደረግ ብላ በትህትና ተቀበለች
ማርያም ሆይ አትፍሪ ብሎ እያረጋጋት
ካንቺ ሚወለደው መድኃኒት ነው አላት
ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል
ብላ ጠየቀችው ድንግልም ደንቋታል
ከሴቶች መሃል አንቺ ልዩ ነሽ
በሕግ ሳይሆን በድንግልና ትወልጃለሽ
ሕይወት ሊቀዳባት አድሯል በማሕፀኗ
አይኖርም ከእንግዲህ የሐዋን መርገሟ
በአዲሱ ኪዳን አዲስ ብስራታችን
ምክንያተ ድኅነት አለች እናታችን
ቃልህ ይፈፀም ይደረግ ብላ
ታምር ተሰማ ኢየሩሳላም ናዝሬት ገሊላ
እጅግ አስገረመኝ የገብርኤል ዜና
የነዘካርያስ ከቶ አይደለምና
የተመረጠችው የደረሰው ብስራት
ዓለምን ከመሞት ከመርገም አዳናት
ከሴቶች መሃል አንቺ ልዩ ነሽ
በሕግ ሳይሆን በድንግልና ትወልጃለሽ

ይኸው ተነሳ

ኃያል ነው እርሱ ዘለዓለማዊ የሁሉ ጌታ
ሞትን የዋጠው ድልን የዋጀ የማይረታ
ይኸው ተነሳ ደስ ይበለን/2/ ብርሃንን አየን

ይኸው ተነሳ ተነስቷል ጌታችን በእኩለ ሌሊት
“ “ ሞትን ድል አድርጐ አለ በሰማያት
“ “ የጨለማው ገዥ ስልጣኑ ተሻረ
“ “ ሞቶ የነበረው ክርስቶስ ከበረ

ይኸው ተነሳ የጠላት ሠራዊት ግብሩ ተገለጠ
“ “ የእዳ ጽህፈታችን እንደሰም ቀለጠ
“ “ ሲኦል ባዶ ቀረ መዝጊያው ፈራረሰ
“ “ ሲነሳ አምላካችን ኃይላችን ታደሰ

ይኸው ተነሳ በታላቅ ምስጋና በግሩም ውዳሴ
“ “ ትንሣዔውን አይታ ተማርካለች ነፍሴ
“ “ ብርቱ ነው ጠንካራ የተነገረለት
“ “ ከእንግዲህ በኋላ ምን ስልጣን አለው ሞት

ይኸው ተነሳ እኛም ከእሱ ጋት ከሞት ተነስተናል
“ “ በቤተ መቅደሱ ብርሃንን ለብሰናል
“ “ የአዳም ልጅ ሰንሰለት ቋጠሮው ተፈታ
“ “ እጃችሁን አንሱ ዘምሩ በእልልታ

ይዲዲያ

ይዲዲያ ነው ምስጋናችን
አምልኮታችን ዕልልታችን
ይቀበለዋል አምላካችን
ከተሻገርነው ኤርትራን በክንዱ
ማለፍ ከቻልን ቀንቶልን መንገዱ
ከበሮ አንስተን መዘመር ብቻ ነው
ለእሥራኤል ቅዱስ ሁሉ ለሚቻለው
የግብጽን ጭቃ ሸንኩርቱን ጥለናል
በገና ክራር መሰንቆም ይዘናል
በዙፋኑ ፊት እንንደዳለን
ምስጋናችንን ስለወደደልን
ቅርፊቱ ሰጥሞ ብረቱ ተንሳፏል
ማይሞተው ሞቶ ፍጥረት ነጻ ወጧል
ነጻነት አለን በደም የታተመ
እንዴት ይወድቃል ከእርሱ ጋር የቆመ
መንፈስ ያሸሸው የዳዊት በገና
ወህኒ ያፈረሰው የጳውሎስ ምስጋና
በኃይል ይሰራል ዛሬም እንደጥንቱ
ነክቶናልና የጸጋ እሳቱ

ድል አለ በስምህ

ድል አለ በስምህ ድል አለ በቃልህ
ተራራው ይናዳል አማኑኤል ስልህ
ባህር ይከፈላል መድኃኔዓለም ስልህ
ቃደሴን ታላቁን በረሃ
አለፈነው ሳንጠማ ውሃ
ፈርዖንን ከባህር የጣለው
ጌታዬ የጸና ስምህ ነው
በእልልታ ቢፈርስ ኢያሪኮ
ጠላትም ቢወድቅ ተማርኮ
ቢሰጠን ለኛ ከተማው
የሆነው ሁሉ ካንተ ነው
የቆምነው ዛሬ በሕይወት
ስምህን አርገን ነው ጉልበት
ከሜዳ ተጠርን ብንነግሥ
ሆነህ ነው ክብርና ሞገስ
ከክፋት ሁሉ ብናመልጥ
የማራ ውሃ ቢጣፍጥ
ብንበላ መና ከሰማይ
ስለሆንክ ነው አዶናይ
ስለሆንክ ነው ሁሉን ቻይ

ድንግል ፈጣሪዋን

ድንግል ፈጣሪዋን ወለደችው
በመጠቅለያም ጠቀለለችው
የለምና ሥፍራ በእንግዶች ማረፊያ
ግርግም አስተኛችው በከብቶች ማደሪያ

ጨነቃት ጠበባት የዳዊት ከተማ
የጌታ መወለድ ታአምሩ ሲሰማ
ወረደ መልአኩ ምስራች ሊያወራ
የሕፃኑም ክብር በምድር አበራ
ይህ ምስጢር ግሩም ነው ከቶ ማይነገር
ማርያምም በልቧ ትጠብቀው ነበር

ሰብአ ሰገል መጡ ከሩቅ ምስራቅ ሀገር
ወርቅ ዕጣን ከርቤውን ለእርሱ ለመገበር
በእናቱም እቅፍ አገኙት ሕፃኑን
ለዓለም ተናገሩ ንጉሥ መወለዱን
ይህ ምስጢር ...

የይሁዳ ምድር ምስጋና ተመላ
ንጉሥ መጥቷልና ከናዝሬት ገሊላ
ታአምሩን ትናገር ቤተልሔም ታውራ
ዝማሬ ሲውጣት ተረስቶ ቆጠራ
ይህ ምስጢር ...

የማይታይ ታየ ተዳሰሰ እንደ ሰው
በጠባቡ ደረት አዳምን መሰለው
ገረማት ጥበቡ ታናሺን ሙሽራ
ተዋሕዷልና ቃል ከሥጋ ጋራ
ይህ ምስጢር ...

ገና እንዘምራለን

ገና እንዘምራለን (4)
እንደ መላእክቱ ብርሃንን ለብሰን -
ገና እንዘምራለን

ወላዲተ አምላክን ከፊት አስቀድመን
በዳዊት በገና መሰንቆ ታጅበን
ለሥላሴ ክብር ገና እንዘምራለን -
ገና እንዘምራለን

በምስጋና ሥራ ከሰለጠኑት ጋር
ልብን የሚያስደስት መዝሙር እየዘመርን
ያልተሰማ ዜማ የልታየ ምስጋና
ይፈልቃል አይቀርም ከእኛ ልቦና - ገና እንዘምራለን

በትዕቢት ሳይሆን በታላቅ ትህትና
በልዩ ተመስጦ በፍቅር ልቦና
ሥራችን ይሆናል ለአምላክ ምስጋና -
ገና እንዘምራለን

ዳዊት በተመስጦ እርቃኑን ቢሆንም
ሜልኮል በዝማሬው ብትስቅበትም
አምላክ ከወደደ እንዲያመሰግነው
በደስታ እንዳይዘምር ከልካዩ ሰው ማን ነው -
ገና እንዘምራለን

ጌታ እኮ ነው

ጌታ እኮ ነው ይህን ያደረገው
አምላኬ ነው ለእኔ የታመነው
በዘመኔ ሁሉ ድንቅን የፈጸመው
ጌታ እኮ ነው ይህን ያደረገው
የጠላቴን ሴራ ያፈራረሰልኝ
ከድንጋይ መወገር እኔን የታደገኝ
የሞት አዋጅ ሽሮ ፅድቅን ያለበሰኝ
አምላኬ ብቻ ነው እኔን ያባበለኝ
ጌታ እኮ ነው ኃጢአቴን የሻረው " " በሰላም ሂድ ያለኝ
" " ልቤን የረጋጋው " " ስተክዝ የረዳኝ
ከወንበዴዎች እጅ የታደገኝ ፈጥኖ
ቁስሌን በዘይቱ ያበሰልኝ አዝኖ
ወዳጅ ሆኖ ቀርቦ ኃዘኔን ያስረሳኝ
ጌታዬ እርሱ ነው መጽናኛ የሆነኝ
ጌታ እኮ ነው በምህረቱ ያየኝ " " ከጠላቴ ያስጣለኝ
" " ሰላሜን ያወጀው
ባህሩን ተሻግሮ ወደ እኔ የመጣው
የሙታንን ኑሮ በሕይወት የቀየረው
ያሰረኝን ጠላት በስሙ ገስፆት
ነፃ አወጣኝ ጌታ ታሪኬን ለውጦት
ጌታ እኮ ነው ልቤን የመለሰው " " ልጁ ያደረገኝ
" " ጠላቴን የጣለው " " በቤቱ ያኖረኝ
በምስኪኑ ድንኳን ገብቶ የሚቀመጥ
በኃዘን ለተዋጠው መጽናናት የሚሰጥ
እጅግ ቸር ጌታ ነው ማዳኑን አይተናል
ስሙን አወድሱት እልልታ ይገባዋል
ጌታ እኮ ነው ከእስራት የፈታን " " ጥልቁን ያሻገረን
" " በሰልፍ ያበረታን " " ያከናወነልን

ጌታዬ መታመኛዬ

ጌታዬ መታመኛዬ/2/
ፍቅርህን እኔ አየሁት
ማዳንክን ተመለከትኩት/2/
መቃብሬን ናድከው ጌታ
ወጣሁ መግነዜም ተፈታ
አቀፍከኝ ይሸታል ሳትል
አነባህ ስለኔ ቁስል/2/
አብቅቷል በቃ ተብዬ
ገስግሰህ መጣህ ጌታዬ
አንከባለልከው ድንጋዩን
እዩት የጌታ ማዳኑን/2/
አራት ቀን ሞላው እሬሳው
ይሸታል አሉ አትጠጋው
አላዓዛር ተነሣ አልከኝ
ወጣሁ መግነዙ ሳይዘኝ/2/

ጌታዬ ሆነ

ጌታዬ ሆነ ደም ግባት አልባ
ጀርባው በጅራፍ ስለኔ ደማ
የእኔን መገረፍ እርሱ ተገርፎ
ክብር አለበሰኝ እርሱ ተገፎ (2)

በሐሰት ሸንጎ ወጥመድ ተጠምዶ
ጌታ ተያዘ ሕይወቱን ፈቅዶ
ክፉዎች ቢያዩት እንደ ወንበዴ
ለእኔ ግን ሆኗል መውጫ መንገዴ (2)
ታስረሃል ስለእኔ ኢየሱስ መድኅኔ

ሲዘብቱበት ምራቅ ሲተፉ
የማይደፈር ደፍረው ሲዘልፉ
በከበቡት ፊት ቃል ከለከለ
እኔ እንድናገር እርሱ ዝም አለ (2)
ተገፋህ ስለእኔ ኢየሱስ መድኅኔ

ሕይወት መንጭቷል ተወግቶ ጎኑ
ለከሳሾቹም ተርፏል ማዳኑ
እጅ እግሩን ሚስማር ሲቸንክረው
የሞትን እሾህ ከእኔ ነቀለው (2)
ተወጋ ስለእኔ ኢየሱስ መድኅኔ

እርቃኑን ሆኖ ፈተለው ልብሴን
እንዲሁ ወደኝ ጠጣ ሆምጣጤን
በምሕረቱ ጠል ነፍሴን አርክቶ
አለመለመኝ እርሱ ተጠምቶ (2)
ተጠማ ስለእኔ ኢየሱስ መድኅኔ

ግሩም ድንቅ ነህ

ግሩም ድንቅ ነህ አምላኬ ግሩም ድንቅ ነህ
ግሩም ድንቅ ነህ ጌታዬ ግሩም ድንቅ ነህ
ሰው የጣለውን ከምድር ከፍ ታደርጋለህ
የተረሳውን አምላኬ ታስታውሳለህ

ከቤተ ሳይዳ ያነሣል በአልጋ ያለውን
መጠመቅ ሸቶ ረዳት ወገን ያጣውን
ከኃጢአተኛ ቤት ይገባል እራት ሊበላ
በቀል አያውቅም ጌታዬ ከፍቅር ሌላ

እንደ አምላካችን ማንም የለም (2)
እንደ እግዚአብሔር ማንም የለም (2)
እንደ ፈጣሪ ማንም የለም (2)
እንደ አማኑኤሌ ማንም የለም (2)

የበደሉትን አይንቅም ያነሣል በእጁ
ፍጹም ይራራል በእውነት ጌታ ለልጁ
ከሳምራዊው ጋር ይውላል እንደ ጓደኛ
ሁሉን በፍቅር የሚስብ ታማኝ እረኛ

እንደ አምላካችን ...

ሰው የናቀው አንስቶ ሾሞ ያከብራል
ዘይት አፍስሶ ባርያውን በእጁ ይቀባል
አክሊል ይደፋል አንስቶ ላጎነበሰው
ክብርና ጋሻ መከታ ዝናር ሊሆነው

እንደ አምላካችን ...

ያዘነውን ሰው ያጽናናል ፍቅር እየዘራ
ያነሳለታል የጭንቁን ግዙፍ ተራራ
ዳግም አይኖርም በቤቱ የእስራት ቀንበር
እሱን ተማምኖ ለቆመ ከመስቀሉ ስር

እንደ አምላካችን ...

ጎሥዐ ልብየ

ጎሥዐ ልብየ ቃለ ሠናየ (2)
ወአነ አየድዕ ቅዳሴሃ ለማርያም /4/

እኴስ የማርያምን ውዳሴዋን እናገራለሁ
እንደ አባቴ ዳዊት በበገና እዘምራለሁ
ቀን ከሌሊት ሳልል ለምሥጋና እተጋለሁ
የኃጢአቴ ቁስል እንዲፈወስ እጮሃለሁ
ምርኩዜ ነሽና እመቤቴ በአንቺ እመካለሁ

አ እመቤቴ በእውነት እንወድሻለን
እውነትኛ መብልን ክርስቶስን ወለድሽልን
ምክንያተ ድሂን ሆይ ድንግል ማርያም የአምላክ መገኛ
በአማላጅነትሽ በመታመን እንጮሃለን እኛ
ምሕረትን አድይን ኪዳነምሕረት የዓለም መዳኛ

ስለቸርነትሽ እመቤቴ ለእኔ እናቴ ነሽ
ስለንግሥነትሽም እመቤቴ ነሽ
ዝናባት ሳያጠጡት አየራትም ሳያሳድጉት
ሰማያዊ እንጆራ የሰጠሽን ቤቴልሔማዊት
ቅድስተ ቅዱሳን የኖኃ መርከብ የእምላክ እናት

ቃና ዘገሊላ በሠርጉ ቤት በዚያ ተገኝተሽ ሳለሽ
ውኃውን ወደወይን በአንቺ ምልጃ እንዳስለውጥሽ
ዛሬም የእኔ ሕይወት ወይኑ አልቆ ባዶ ሆኗልና
አንቺ የአምላክ እናት ንጽህት ቅድስት ርህርት ህሊና
ሕይወቴና አድሰሽ ቀድሸው ሙይው በምስጋና

ፈተናው ወጀብ ቢበዛ

ፈተናው ወጀብ ቢበዛ
አይተናል ሕዝቡን ሲያበዛ
በሕይወት አንዴ ጠርቶናል
እግዚአብሔር መች ይተወናል

ፍቅር ነው የናርዶስ ሽቶ
ወደደን ተሰቅሎ ሞቶ
ነጎድጓድ መብረቅ ቢሆንም
በሕይወት አለን አሁንም

መኳንንት ደጁን ክፈቱ
የፀጋው ፈልቷል ዘይቱ
ተራግፏል ሸክማችን
ምህረቱ ቢፈስልን

ተጽናንቷል አርፏል ልባችን
በእሳት ታጥሯል ቅጥራችን
አንወድቅም አንሸነፍም
ይዞናል የአምላካችን ስም

ሕይወት ነህ የጽድቅ ጥላ
ያውቅሃል ቃል የተመላ
ነህ አንተ ጣፋጭ ምግባችን
እግዚአብሔር ቸሩ አምላካችን

ፍቅር ነህ አባቴ

ፍቅር ነህ አባቴ ፍቅር ነህ ፍቅር ነህ ጌታዬ
በሰላም እኖራለሁ አልፎልኝ ያሁሉ ስቃዬ

ከቁጥር በዝቶ ኃጢአቴ በደሌ ቢያስጨንቀኝም
ተስፋ ቆርጬ በራሴ ለማረፍ ሞቴን ብመኝም
አልተሟጠጠም ትዕግስትህ ለልጅህ ያለህ ፍቅር
አልነቀልከኝም ጨክነህ ሕይወቴ ስልህ ልኑር
እንዳንተ ያለ እረኛ እንዳንተ ያለ ወዳጅ
የትም አላገኝ ስፈልግ ዕድሜ ዘመኔን ብፈጅ

ገደቡን አልፎ ሐዘኔ ሲሰብረው ጽኑ ልቤን
ብቻዬን መሆን ፈለኩኝ መሸከም ከብዶኝ ስድቤን
እያቃሰትኩኝ ፈለግሁህ እየታመምኩኝ አባቴ
አሰተውያለሁ ፍቅርህን ተስለህብኝ ከፊቴ
እንዳንተ ያለ እረኛ እንዳንተ ያለ ወዳጅ
የትም አላገኝ ስፈልግ ዕድሜ ዘመኔን ብፈጅ

ምርጫዬ ስህተት አይደለም ማፍቀሬ አንተን ለይቼ
እመሰክራለሁ ስላንተ ሳላፍር አፌን ሞልቼ
ምክንያት አትሻም ስትወደኝ ባዶ ሆኜ ነው ያየኸኝ
በሸለቆ ውስጥ ተጥዬ ለዛሬው ክብር ያሰብከኝ
እንዳንተ ያለ እረኛ እንዳንተ ያለ ወዳጅ
የትም አላገኝ ስፈልግ ዕድሜ ዘመኔን ብፈጅ

ፍቅር ነህ ዘላለም


ፍቅር ነህ ዘላለም እንዳንተ የለም
ከሀሊ ነህ ጌታ የማትረታ
እጅግ ፈጠኑ ሰረገሎቹ
የእሳት ፍላፃ ይዟል በእጆቹ
አይሸነፍም አይወድቅም ከቶ
ዛሬም ይኖራል መቅደሱን ሞልቶ
ያጉረመርማል ጠቁሯል ሰማዩ
አለቆች ሸሹ ክብሩን እያዩ
የሚያስተጋባ መብረቅ ነው ድምጹ
የሲኦል ደጆች ተነዋወጹ
ዓይንህ እንዳየች አትፈርድም አንተ
ምርኮ አብዝተሃል ተሰቅለህ ሞተህ
አንደኤት ወደደድከኝ ብዬ አልልህም
ፍቅር ነህና ለዘለዓለም
በተዘጋው ቤት መግባት ታውቃለህ
ፍጥረት መነነ አንተን እያለ
የደስታ ምንጭ የእልልታ ቤቱ
ዘይተህ ነክቶኝ አብርቷል ፊቴ


ፍቅርን አስተምሩን


ፍቅርን አስተምሩን መተሳሰብን
ለሀገር ለሕዝባችን መልካም እንድንሆን
በእምነት አሳድጉን ታሪክ እንድንሰራ
ቅርሱን እንድንጠብቅ የእናንተን አደራ
ክርክርን ፀብን አስወግዱ
እንደቃሉ ፍፁም ተዋደዱ
የእናንተ ፍቅር እኛን ይገዛል
መልካም አርጎ ዘወትር ይቀርፀናል
መሳሪያ ነው የጽድቅ ፍፃሜ
ፍቅራችሁን እንዳይገታው እድሜ
ዛሬም ነገም አንድ ይሁን ልባችሁ
ጌታ እንዲከብር በመካከላችሁ
ገንዘብ አድርጉ መተማመንን
አታርክሱት መኝታችሁን
ሞትነው ትርፉ የኃጢአት ውጤት
አትጥፉብን ኑሩልን በህይወት
ሞልቶ ፈሷል የበደሏ ፅዋ
አቅም የላትም ዓለም ለብቻዋ
ተጠንቀቁ የእባቡን መርዝ
እንዳይጨልም የቤቱ መቅረዝ
ኃላፊነት ትልቅ አደራ ነው
ካልሰሩት ሥልጣንም ዕዳ ነው
ለህሊናችሁ ለእውነት ፍረዱ
መማለጃን ጉቦን አትውደዱ
አስቡለት ለመጭው ትውልድ
አታሳዩት የበቀል መንገድ
ዓላማችን ቢሰምርም ዛሬ ነው
አትመኩ ነገ ሌላ ቀን ነው


ፀምረ ጌዴዎን



ፀምረ ጌዴዎን ንጽህት አዳራሽ
በሥጋም በነፍስም መርገም ያልነካሽ
የበጉ ዙፋን ማርያም አንቺ ነሽ
የበጉ ዙፋን ድንግል አንቺ ነሽ
የሌሎች ሴቶች ልማድ ሳያውቅሽ
ዓለም እንዲድን አምላክ መረጠሽ
ከረጅም ጭንቀት ድንቅ ማረፊያ
ደሴት ሆነሻል መልህቅ መጣያ
የባርያይቱን መዋረድ አይቷል
አካላዊው ቃል ሥጋዋን ነስቷል
ድሃው ሥጋችን በእርሱ በልጽጓል
በእግዚአብሔር ዙፋን በቀኝ ተቀምጧል
ከሦስቱ አንዱ ወረደ ከሰማይ
ታላቅ ሥራውን አየን ባንቺ ላይ
የባርያይቱን ...
አምላክሽና መድኃኒትሽ
ለተዋሕዶ አንቺን መርጦሽ
እኛን መሰለ እኛን አከለ
ምክንያት ሆነሽን መርገም ተጣለ
የባርያይቱን ...
አምላክ ከእኛ ጋር ስለመሆኑ
ምልክት ሆንሽ ነጋልን ቀኑ
ሥፍራውን ለቆ ጠላት ሸሽቶናል
ሦስት መቶ ሆነን እልፉን መትተናል





















ማውጫ

ተ.ቁ		ገጽ	ተ.ቁ		ገጽ
1	ኃያል ነው እርሱ	87	39	በሃዘኔ በፍጅንቀቴ	25
2	ኃይልን በሚሰጠኝ	10	40	በልቤ ከተማ	26
3	ለማርያም	83	41	በማኅፀን ቅኔ	26
4	ለጥርሳቸው ንክሻ	9	42	በማንም	27
5	መልካም አደረገ	10	43	በምህረት በይቅርታ	27
6	መረቤን በዓሣ የሞላ	11	44	በምስጋናህ	28
7	መርከቤ	11	45	በምን ደስ ላሰኝህ	28
8	ሚካኤል ስለው	72	46	በሰማይ	29
9	ማረከኝ ምስጋናሽ	12	47	በበጎ ፈቃዱ	1
10	ማሪኝና ልሂድ	12	48	በቤተ መቅደስህ	30
11	ማራናታ	13	49	በንጹህ ደሙ	31
12	ማራኪው	13	50	በአንተ ነው ጌታ	36
13	ማን አለን	14	51	በዕፀ መስቀል	31
14	ምስጉን ነው	14	52	በከበረው ሰረገላ	2
15	ምስጋና ለድንግል	15	53	በዋጋ ገዝተኸኛልና	32
16	ምስጋና በመቅደስህ	15	54	በዘመናት የሸመገለ	32
17	ምስጋና በሰማይ	16	55	በዘባነ ኪሩብ	33
18	ምስጋናዬን	16	56	በድል ቆመናል	33
19	ሞገድ ሲመታኝ	17	57	በገና አንስተን	34
20	ሰላሜ ባንተ ነው	4	58	በጎ ስጦታዬ	34
21	ሰላምህ በዛልኝ	17	59	ባለውለታዬ	35
22	ሰረገላዎችህ	18	60	ባለፀጋ እመቤት	35
23	ሰዎች	18	61	ብርሃን የለበሰ	36
24	ስለማይነገር	19	62	ተመስገን ተመስገን	37
25	ስለምን ወደድከኝ	19	63	ተራሮችን ሁሉ	37
26	ስመሰክር ዓይኔን	20	64	ተናገር ባርያህ	38
27	ስሙ ከስም ሁሉ	20	65	ትህትና ልብስሽ	38
28	ስምሽን ለልጅ ልጅ	21	66	ትህትናሽ ግሩም ነው	83
29	ስምሽን ጠርቼ	21	67	ትላንትና ካንተ ጋር	39
30	ሥራህ ትክክል ነው	22	68	ትናንትናም ቅዱስ	39
31	ሮሆቦት እያልን	6	69	ትውልድ	40
32	ሺውን በአህያ	22	70	ችርነትህ ነው	40
33	ቀስተ ደመና	23	71	ኑ በእግዚአብሔር	1
34	ቀርንዮ	23	72	ናታኒም ነኝ	41
35	ቀኑ መሸቷል	24	73	አሁን ተረጋጋ	41
36	ቅዱስ ሚካኤል	5	74	አለ ለእኔ የተሻለ ነገር	42
37	ቅዱስ ነህ	24	75	አለልኝ አባቴ	42
38	ቋንቋዬ ነሽ	25	76	አለማመኔን እርዳው	43

ማውጫ

ተ.ቁ		ገጽ	ተ.ቁ		ገጽ
77	አለን አልጠፋንም	43	115	እንደምወድህ	59
78	አልፈራም	44	116	እንደኔ የረዳኸው	7
79	አምላካችን ገናና ነው	44	117	እንዴት ወጣሁ ብዬ	59
80	አምኜ ስወጣ	45	118	እንድንበዛ ጠራን	6
81	አሸነፍን	3	119	እኛ ግን የተሰቀለውን	60
82	አበረታኝ ፍቅርህ	29	120	እውነተኛ ሰላም	60
83	አቤቱ ላንተ	45	121	እውነት ስለሆነ	61
84	አቤቱ ጉልበቴ ሆይ	46	122	እግሩ ለቆመበት	61
85	አኑሮኛል ቸርነትህ	47	123	እግዚአብሔር ከኛ	62
86	አናቋርጥም	47	124	እግዚአብሔር	62
87	አንተ ሳታሻግረው	9	125	እጠበኝ ቆሸሻለሁ	63
88	አንተ ሳታሻግረው	48	126	እፁብ ድንቅ ነው	63
89	አንተ ብቻ ንጉሥ	48	127	አ እንዳንተ ያለ	64
90	አንደበቴም ያውጣ	82	128	ከጎሊና በላይ	64
91	አከብርሃለሁ	49	129	ከሞት እንድንድን	65
92	አየኋት በአይኔ	4	130	ከሰማዩ ከፍታ	65
93	አየኋት በአይኔ	49	131	ከራድዮን	66
94	አዳነኝ ጌታ	50	132	ከክርስቶስ ፍቅር	66
95	አጋጣሚ አይደለም	50	133	ከውለታ በላይ ነው	67
96	አጥቷል ጎሎበታል	46	134	ኪዳነ ምሕረት	68
97	ኤልሮኢ	51	135	ኪዳነ ምሕረት ለእኔ	67
98	ኤልሻዳይ ነህ	51	136	ካልባረከኝ አለቅህም	68
99	ኤፍታህ በለኝ	52	137	ካንተ የሆነው	69
100	እመቤታችን	52	138	ክብረ ቅዱሳን	30
101	እመቤቴ ስልሽ	53	139	ክንድህን እጠፍ	69
102	እመቤቴ የአምላክ	53	140	ኮከብ ሲወጣ አየሁ	7
103	እረ እንዳንተ ያለ	54	141	ወረት የሌለው	70
104	እርሱ ብቻ	54	142	ወድሰኒ	70
105	እቴ ሙሽራዬ	3	143	ውለታህን	71
106	እናመሰግንሃለን	55	144	ውለታሽ ጠርቶኝ	71
107	እኔ አላይም ካንተ	55	145	ውዴ በኔ ላይ	72
108	እኔስ አልፈራም	56	146	ዝናርህ በይቅርታ	73
109	እንሰዋለን ቅኔ	56	147	የለም ሌላ ስም	73
110	እንበረታለን ገና	2	148	የሉም ከሳሾቼ	74
111	እንዘምራለን	57	149	የመስቀሉ ፍቅር	74
112	እንደ ቅዱስ ዳዊት	57	150	የማይሽረሽር አለቴ	8
113	እንደ ባለማዕረግ	58	151	የማይሽረሽር አለቴ	75
114	እንደ እግዚአብሄር	58	152	የማይጠፋ ፋኖስ	75

ማውጫ

ተ.ቁ		ገጽ	ተ.ቁ		ገጽ
153	የተወደደ ቀን	76	191		
154	የት ሄዳለሁ	76	192		
155	የትናንትና ማንነቴን	77	193		
156	የአንደበቴ ጣፋጭ	77	194		
157	የአዳነኝን	78	195		
158	የክብርህ ጸዳል	78	196		
159	የወደደኝ ጌታ	79	197		
160	የያሬድ ውብ ዜማ	79	198		
161	የግብጽን ከተሞች	80	199		
162	የጽድቅ በር ነሽ	80	200		
163	የፈራ ይመለስ	81	201		
164	የፍቅር እናት የሰላም	81	202		
165	ያለ አንተ ክብር የለኝ	82	203		
166	ያስከበርከኝ	5	204		
167	ያስከበርከኝ	84	205		
168	ያንተን ያንተን	8	206		
169	ያድናል	84	207		
170	ይበራል በክንፉ	85	208		
171	ይታዘዛት ነበር	85	209		
172	ይነጋል ባንተ	86	210		
173	ይናፍቃል	86	211		
174	ይኩነኒ	87	212		
175	ይኸው ተነሳ	87	213		
176	ይዲዲያ	88	214		
177	ድል አለ በስምህ	88	215		
178	ድንግል ፈጣሪዋን	89	216		
179	ገና እንዘምራለን	89	217		
180	ጌታ እኮ ነው	90	218		
181	ጌታዬ ሆነ	91	219		
182	ጌታዬ መታመኛዬ	90	220		
183	ግሩም ድንቅ ነህ	91	221		
184	ጎሥዐ ልብየ	92	222		
185	ፀምረ ጌዴዎን	94	223		
186	ፈተናው ወጀብ ቢበዛ	92	224		
187	ፍቅር ነህ አባቴ	93	225		
188	ፍቅር ነህ ዘላለም	93	226		
189	ፍቅርን አስተምሩን	94	227		
190			228		